# 46

ስሚ ሁለት ክፍል ነው:: አንዲት ጠባብ ክፍል:: ደግሞ እንደገና የጠባብ ጠባብ ጓዳ ከኋላዋ ያዘለች:: የማማ ሸዋ ቤት:: ዋንኛዋ ክፍል የአጣና አልጋ ተዘርግቶባት የተረፈው ቦታ በአሮጌ ሳጥን፣ በበርጩማና በአንድ አነስተኛ እግዳሚ የተያዘ:: በሩ አጠገብ ፊት ለፊት ላስቲክ ተሸፍና ካስር የማይበልጡ ጣሳዎች የተሸከመች ትንሽ ጠረጴዛ:: ጓዳዋ ደግሞ በጠላ እንስራና በስም የለሽ የድሃ ኮተታ ኮተት የተጨናነቀች::

ዛሬ ጠላ ስላላቸው ጭራሹን ተጨናንቃለች:: ሳጥኑ ላይ የተቀመጡት ሰዎች አግዳሚዋ ላይ ከተቀመጡት ጋር ጉልበታቸው ሊነካካ መዳፍ ታክል ቢራራቁ ነው:: ከውጪ ወደ ውስጥ የሚያልፍ ሰው ቢኖር ግራና ቀኝ የተሰለፉትን ጉልበቶች በእግሩ መገጫጨት አለዚያም መተሻሸት የግዱ ነው::

መሸተኞቹ ከአሥር የማይበልጡ ቢሆኑም ጫጫታቸውና ሁካታቸው ብዙ ሰው ያለ ያስመስላል:: አንዳንዶቹ ካቲካላ ቀላቅለው ስለሚወስዱ ሞቅም ስክርም አድርጉአቸዋል:: ለዚህም ነው የሚጯጯሁት::

እማማ ሸዋ ጓዳዋ መግቢያ ላይ ካለችው በርጩማ ቁጭ አንዳንዴም ወደ ጓዳ ገባ እያሉ የጠጪዎቹን ትዕዛዝ ይጠባበቃሉ:: ከጫጫታውም ጆሮአቸው የፈቀደውን ሥራዬ ብለው ያዳምጣሉ::

"ይቅር ይበልህ! የት ያውቁታል ብለህ ነው? እነሱ ቡሄ ጨፋሪ እንጂ አዝማሪዎች አይደሉ:: ልጆቹ እኔ እንደሆን አልጋገርኩም፤ ለዛሬ አመት እንገናኝ" አሉ ተረፈ ጌሾ ቡሄ ጨፋሪዎቹን 'እንዲህ በሉ' እያለ ከመምጣታቸው ዝም ሲያሰኛቸው:: -ሰከሯል::

"ሂጅ! ም-ም-ምን አገ- ባሽ- አንቺ!" አለ በስካር እንደበት ፊደላቱን ምላሱ ላይ እየበታተነ::

"እምናም እኮ እንዲህ ነበር ያሉን" አለ ከቡሄ ጨፋሪዎቹ ልጆች አንደኛው::

እማማ ሸዋ እፍር ብለው እንዳልሰማ ዝም አሉ:: ልጁ እውነቱን ሊሆን



እንደሚችል ያውቃሉ:: ዓመት ቡሄ በመጣ ሆያሆዬ ብለው ለሚመጡባቸው ልጆች የሚሸነግሉበት የተለመደ ዘዴ ነው::

"ለከርሞ እንገናኝ -አሁን አልጋገርኩም:: -አድርሻለሁ::"

"ሳ -ን —ቲ- ም. . . አይደ -ለ -ም ትፈሊ- ገ —ው? ጭ- ጨ- ፍር" አለ ተረፈ ጌሾ ወደ ኋላው ተለጥጦ እጁን ከሱሪው ኪስ እያስገባ::

"ሆያ ሆዬ —ሆ!
ሆይ የኔ ጌታ -ሆ! . . ." ብለው ሲጀምሩ አቋረጣቸው::

"አያ -ያ —ያይ! እሱን አልፍ —ፈልግም"

ልጆቹ ትተውት ሄዱ::

"ፈ -ሳ —ም! ቀረ—ብህ? አለና ጉልበቱን እየደበደበ ራሱ መዝፈን ያዘ:: ምላሱን እያገመደ::

"ጠላ ፋይል ከፋች ጠጅ ጠበቃ ነው
ሸጋው ካቲካላ ህግ አስከባሪ ነው::
ካቲካላ ፊት"

ይኼን ጊዜ ጠጪዎቹ የየራሳቸውን ጨዋታ አቁመው በተረፈ ጌሾ ግጥም ተሳሳቁ:: ተረፈ ጌሾ በገባበት መጠጥ ቤት፣ ሞቅ ሲለው በየመንገዱ ሳይቀር መዝፈን ይወዳል::አብረውት የሚጠጡ ሁሉም ለሽካራ ድምጹና ለማይሰባበር ንግግር መሳይ ዜማው ሳይሆን ፊደል እየበጣጠሰ ለሚያወርዳቸው ግጥሞቹ ሲሉ ያዳምጡታል::መጀመሪያ ማን እንዳወጣለት ባይታወቅም በስሙ ላይ 'ጌሾ' የሚል ቅጽል ጨምረው የሚጠሩት ከሚያዘፍነው የመጠጥ ግፊት ጋር አያይዘው ሳይሆን እንደማይቀር ይገመታል:: ስም ማውጣት የማይሰለቻቸው ያራት ኪሎ ልጆች:: መሸተኞቹ በመጀመሪያው ግጥም ካውካኩ በኋላ ሁለተኛውን ለመስማት ቀዝቀዝ አሉ:: -ቀጠለ::

"አንድ ቀን ተስቶኝ ሞኝ አቅፌ ብገኝ
ጅል የጠፋው ሁላ መፈለጊያ አረገኝ::
ጅል!"
ሳቅ በሳቅ -ደሞ ሌላ

"ባላገር ሞኝ ነው አልችላትም ይላል
እንኳን ጠይምና ግራር ይሸከማል
ግራር ፊት!
ቅጂ አንቺ አሮጊት!"

"ይቅር ይበልህ! የትኛውን ልቅዳልህ?" አሉ እማማ ሸዋ ፈዝዘው እያደመጡት ስለነበር ድንገት ሲያዛቸው ደንገጥ ብለው:: ተረፈ ጌሾ ሲጠጣ የቆየው ጠላም ካቲካላም ነው::

"ጠላ ፋይል ከፋች ጠጅ ጠበቃ ነው
ሸጋው ካቲካላ ህግ አስከባሪ ነው" አለ የአረቄ መለኪያውን ብድግ አድርጉ::

"ወንድ እኩል ነው ያልሺኝ እንዴት
ወንድ እኩል ነው
ፋሽኮና ብርሌ ሥራው ለየቅል ነው::
ፋሽኮ ራስ!" . . . ቀጠለ ደሞ ሌላ::

ወይዘሮ ብዙነሽ የእማማ ሸዋ ጠባብ ቤት ይበልጥ ጠብባና በጫጫታ ተሞልታ ሲያዩ እንደ ድንገተኛ ውጋት የቀሰፈ ችግር ባይኖርባቸው መመለስ አሰኝቷቸው ነበር::

"እኔ ልምጣ?" አሉ እማማ ሸዋ ወይዘሮ ብዙ በየት ልለፍ እንደማለት ክበር ቆመው በዓይናቸው ሲማትሩ ጭንቀታቸው ገብቷቸው::

"ኧረ እኔ እመጣለሁ" አሉና ጠጭዎቹ እግሮቻቸውን ወደ ጐን ሰብሰብ ሲያደርጉላቸው ተጠንቅቀው ወደ ውስጥ ወደ ትንሿ ጓዳ አለፉ::
"ምነው ምን ሆነዋል?"
"እንደው ዛሬን ቅበሩኝ እማማ ሸዋ!"
"ምነው ምን ሆኑ?" አሉ ጭንቀታቸው ተጋብቶባቸው::
"ይቅበሩኝ!" አሉና እግራቸው ላይ ሊወድቁ ጐንበስ ሲሉ እማማ ሸዋ ትከሻቸውን ያዝ አድርገው ተከላከሉ::
"ይቅር ይበልሁ! ምንድነው ነገሩ ይንገሩኛ?" አሉ ግራ ገብቷቸው::
"በእመብርሃን በጭንቅ አማላጇ ይዤዎታለሁ::"
"ጭንቅ አማላጇን ይተውና ይልቅስ ጉዳዩን ይንገሩኝ:: እመብርሃን የት ታውቀኛለች:: ድንጋይ ናት እንጂ ውነት እሷ ታቦት ብትሆን እድሜ ልኬን ስለምናት እንደ እንጨት ደረቅ አርጋ አታስቀረኝም ነበር:: አንድዬ ይቅር ይበለኝ ብቻ" አሉ እማማ ሸዋ:: እመብርሃንን አይወዷትም:: ልጅ ለምነዋት ስለነሳቻቸው በርሷ ስም ለሚለምናቸው አንጀታቸው አይራራም::
"እሺ በአንድዬ! በፈጣሪ ይዤዎታለሁ ከጉድ ያውጡኝ:: መቼም አብሮ መብላት ለዚህ ቀን ነው::"
"የምን ጉድ ነው እሱ?"

ወይዘሮ ብዙ ወደ ጆሮአቸው ጠጋ አሉና ዳርምየለሽ ምጥ ይዟት እየተጨነቀች መሆኑን ሹክ አሏቸው:: እንዲያው የፍርሃታቸውን እንጂ የነሱ ድምጽ ከጠጪዎቹ ጫጫታ በላይ ሆኖ ሊሰማባቸው የሚችል አልነበረም::



"ቱ! ይቅር ይበልሁ አንቱ! ከምን አመጣችው በሉ! በዛሬ ዘመን እኮ የልጅ ጨዋ የለውም:: ለዚ ኖሯል ያን ጊዜ! ለመሆኑ መቼ መጣች?" ጆሮአቸውን ሊያምኑ አልቻሉም::
"ትናንት ማታ ነው የመጣችው" አሉ ወይዘሮ ብዙ ሃፍረት እና ጭንቀት እንዳሸማቀቃቸው::
"ታዲያ ምናለ! መጣኋ:: እንኳን ለሷ ለልጇ ቀርቶ አገርን ሳዋልድም አይደል የኖርኩት:: ለራሴ መውለድን ነፈገኝ እንጂ ጌታ!" አሉ እማማ ሸዋ ከርሳቸው ምን ፈልገው እንደመጡ ገብቷቸው:: እግረ መንገዳቸውንም የራሳቸውን ብሶት አንስተው ጌታቸውን እየወቀሱ::
"መጣሁ ምላጭና ክር ምናምን አዘጋጅተው ይጠብቁኝ:: በጣም አፋፍሟታል እንዴ?"
"እኔ እንጃ፣ ብቻ እያለቀሰች ትንቆራጠጣለች:: ሳትደርስ አትቀርም" አሉ አብረዋቸው ቢሄዱላቸው እየተመኙ::
"ወይ ልጄን! እንግዲያው አንዷን ልጅ ይላኩልኝና ትጠብቅልኝ:: እኔ እንኳን ሰዎቹ የያዙትን እስኪጨርሱ ጠብቄ ለመምጣት አስቤ ነበር" አሉ ባንድ ልባቸው የዳርምየለሽ ምጥ በሌላ ልባቸው ደግሞ የጠላቸው መዘጋት አሳስቧቸው::

ወይዘሮ ብዙ እንደሄዱ አስናቀችን ላኩላቸው:: እማማ ሸዋ እያንዳንዱ ጠጪ ላይ ያላቸውን ሂሳብ ነግረዋት ጠላ ማለቁን ራሳቸው አስታወቁላትና ጠጪዎቹ እንደወጡ ቆልፋ እንድትመጣ ቁልፍ ሰጥተዋት ሄዱ::

# 47

ሩ

“አይዞሽ ልጄ የሁላችንም አፈጣጠር አንድ ነው” አሉ እጃቸውን በቀሚሷ ሥር ሰደድ ሲያደርጉ ሽምቀቅ ስላለች አፍራ መሆኑ ገብቷቸው። መሬት ከተነጠፈላት ፍራሽ ላይ ተንጋላ ተኝታለች።

“በጭንቅ ተይዘሽም ታፍሪአለሽ! እንዲያው በምን ቀን ተሳሳትሽ ልጄ! አንቺስ ቀበጥባጣም አልነበርሽ” አሉ እየደባበሷት። ዳርምየለሽ መልስ አልሰጠቻቸውም። የምጡ ስሜት ከህፍረት ጋር ያሳደረባትን ስቃይ ለመቋቋም ከንፈሯን በጥርሷ ነክሳ እንባዋን ብቻ በጆሮ ግንዷ ታሽኳልላለች።

“እግዚአብሔር ሲረግመኝ ነው እንጂ ሲቀጣኝ። ለእርሷ ሳይሆን ለኔ የወረደ እርግማን ነው” አሉ ወ/ሮ ብዙ ቁጢጥ ብለው የተጨነቀች ልጃቸውን ዓይን ዓይኗን እያዩ። ኑኝሼም ማልቀሱን ተያይዛዋለች።

“ይቅር ይበልሁ! ኧረ ግፍ አትናገሩ! አሁን ምኑ ነው ቅጣቱ ምኑ ነው ርግማኑ? እንዳው መቼም ተሰርጋ በትዳር ቢሆን ያማረ ነበረ። እንጂ መውለድ ምን እርግማን አለው? ፀጋ ነው። ለእርሶም ቢሆን የልጅ ልጅ ማየቱ ያስደስታል” አሉ የወ/ሮ ብዙን ምሬት ገስፅ አድርገው።

“የዲቃላ ደስታስ ይቅርብኝ። የልጅ ልጅ ማየት የሚያኮራው በወግ በማዕረግ ድረው ኩለው ሲያገኙት እንጂ ልጅ ሆነው ልጅ ቢያመጡ አያኮራም።”

“እንዲህ አይበሉ። በዛሬ ጊዜ በየቤቷ ያልወለደች የለችም። ጊዜው ነው። ዘመኑ ያመጣውን ታዲያ ምን ይደረጋል። ይኸው የፋናዬ ልጅ በቀደምለታ ወለደች። እናቲቱ እንዲህ እንደርሶም አልተበሳጩ። ልጅቷም ብትሆን ሆዷን አንገፍጥጣ አራት ኪሎ ለአራት ኪሎ ስታስመርቅ ደንታ አልነበራትም” እማማ ሸዋ የፋናዬ ልጅ ያሉት ሳቢ ጋይድን ነው።

“እርሷማ ድሮውንም የታወቀች ዘልዛላ ናት። እናትየዋም ቢሆን መረን ለቀው የተዋትን ምን ይሰማቸዋል። ወንድ ይመስል ሱሪ ለብሳ ከማንም ዱርዬ ጋር ስትዛለል እስካሁንም መቆየቷ የሚገርም ነው።”

“ኧረ እሷማ እንደምትለው ልጃገረድ ነበረች። ያረገዘችው በደሟ ነው” አሉ ደባብሰዋት ስለበቃቸው እጃቸውን እያወጡ።

“ይኼ እንኳን የማይመስል ውሸት ነው። አሁን ማን ይሙት በእርሷ መንዘላዘል እስከ ዛሬ ልጃገረድ ሆና ነው?” አሉ ወ/ሮ ብዙ ባለማመን። “ውሃ ለእጃቸው አንቺ?”

“እሱስ እኔም አላመንኩም. . .። ይቅር ይበልሽ! የምን መነፋረቅ



ነው እሱ! ምን ትሆናለች!” አሉ ኑንሼን እየተቆጡ። እንባዋን እየጠረገች ውሃ ልታመጣ ወጣች።

“ገና ነው። እንደሱ እንዳለሽ ቆይ። ብዙም አታምጪ። አለጊዜው ቢያምጡት አይወጣም” አሏት እጃቸውን እየታጠቡ። “እርሶዎም እፊቷ ቁጭ ብለው ከሚያለቅሱ ቡና አፍሉና ፈጣሪዎትን ይለምኑ። የመጀመሪያዋ ስለሆነ አስጨነቃት እንጂ ደህና ናት” አሏቸው ወ/ሮ ብዙንም።

ወይዘሮ ብዙ በመጠኑ ልባቸው ተረጋግቶ ቡና ማፍላት ጀመሩ።

“ለመሆኑ አባቱ ተቀብሎታል?” ሲሉ ጠየቁ እማማ ሸዋ። ዳርምየለሽ አሁንም መልስ የላትም። ያስረገዛት ሰው ማርገዟን ሳይሰማ በመኪና አደጋ መሞቱን ወ/ሮ ብዙ ከዳርምየለሽ የሰሙትን ነገሩአቸው።

“ይቅር ይበልሁ! ገና ሳይወለድ! ምን ዕድለ ቢሱ ነው አንቱ”

“እኛም ዕድለ ቢስ ሆንን እንጂ። በህይወት ቢኖር እንኳን ጠቅልሏት የራሷ ጉዳይ ነበር።”

“ፈረደባት እንጂ ገና በልጅነቷ የሙት ልጅ ልታሳድግ።”

“ኧረ ምን ሊያደርግላት ታሳድጋለች!”

“እንግዲያውማ አትጥለው። መቼም ተፈጠሬ ያላት ነብስ አትቀርም” አሉ እማማ ሸዋ።

“በስሳም ትገላገልና ህይወቷ ይትረፍ እንጂ ልጁ እንኳን አስፈላጊ አይደለም።”

“ምን ያደርጉታል ታዲያ?”

ጉዲፈቻም ቢሆን እንደሚሰጡት ነገሩአቸው። እማማ ሸዋም ለሌላ ሰው አሳልፈው ከሚሰጡ ለእርሳቸው እንዲሰጧቸው እና ስሟን ሳይጠሩ ሌላ ሰው እንደሰጣቸው አድርገው እንደሚያሳድጉ ቃል እየገቡ ለመኗቸው።

ወይዘሮ ብዙ ግን ሚስጥራቸውን ገልፀው ያካፈሉአቸው በእርሳቸው ላይ እምነት ስላላቸው መሆኑን እና ለእርሳቸው መስጠትም የማይሆንና ምናልባት ልጁ ከፍ ሲል መልኩ እየለየ መሄዱ ስለማይቀር የእናቱን መልክ ይዞ ቢወጣ ከሃሜትና ከመንደር ትችት እንደማያመልጡ ገልጸው ሁለተኛ እንዳይለምኑአቸው በፈጣሪ ስም ተማጸኑአቸው።

“ካሉስ ይቅር። ለነገሩማ መጀመሪያውን አንድዬ የበደለኝን በስተርጅና የሰው ልጅ አሳድጌ ሊጠቅመኝ ነው?” አሉ እማማ ሸዋ የተለመደ ምሬታቸውን በአንድዬያቸው ላይ እያነሱ።

“እመብርሃን የአዳሜን ደም ስታሳፍሰኝ አንድ ቀን እንኳን ለኔ የሄዋንን ፍሬ ማሳቀፍ አቅቷት ለርጅና አበቃችኝ። ጥፋ እንኳን ይደገማል። መውለድ ምን እንደሁ ሳታሳየኝ በአንድ ጊዜ ውርጃ አንጉታ ነጠቀችኝ። ከእንግዲህማ

ምን ተስፋ አለኝ" አሉ ጨምዳዳ ፊታቸውን በሀዘን ይበልጥ አጨማድደው::

እማማ ሸዋ ካረጁ በኋላ ተስፋ ቆርጠው ተውት እንጂ ልጅ ለመውለድ ያልተሳሉት ታቦት፣ ያልሰገዱለት ቃልቻ፣ ያልወደቁለት ወንድ የለም:: ከጅምሩ በትዳራቸው ላይ አማግጦ ከቤት ያበረራቸው፤ አዲስ አበባም ከመጡ ከአንዱ ሳይረጉ ይይዝለታል የተባለውን ሁሉ እያሰዋወጡና ራሳቸውን እሳልፈው እየሰጡ የረባ ትዳር እንኳን ሳይኖራቸው እንዲህ ወድቀው ያስቀራቸው ልጅ ለመውለድ ያላቸው ጉጉትና ፍላጉት መሆኑን አዘውትረው በምሬትና በቁጭት የሚያነሱት ነው::

በተለይ እመብርሃናቸውን፣ ልመናቸውን ችላ ብላ የእናት ወጉን ስለነፈገቻቸው ዘወትር እንደረገሚትና እንዳወገዟት ይኖራሉ:: ማርያም የተባለች ቤተክርስቲያን ስትነግስ ብትውል አይስሙም:: የአጠገባቸውን ቅድስት ማርያም አልፈው ገብርኤልና ስላሴን ነው የሚስሙት:: ስለማርያም ለሚል ለማኝ አይመፀውቱም:: "ማርያም ትስጥህ!" ነው እየተቆናጠሩ የሚሰጡት መልስ:: ባጠቃላይ በማርያም ስም ምንም ነገር አያደርጉም:: ኩርፍ ናቸው:: እርሳቸውና ማርያም::

ቡናው ተፈልቶ አቦሉን እየጠጡ ሳለ ዳርምየለሽ የተለየና ጫን ያለ ጭንቀት ተሰማት:: እየጮኸች እጆቿን ስታወራጭ እማማ ሸዋ ስኒአቸውን አስቀምጠው ለአራተኛ ጊዜ ዳበሷት::

"አይዞሽ! አሁን ደርሷል:: አይዞሽ! እንደዛው እንዳለሽ ጫን ብለሽ አምጪ! ኑ! እርስዎ አንገቷ ሥር ደገፍ አርገው ያዟት!" አሉ እማማ ሸዋ ሥራቸውን እየሠሩ::

ወይዘሮ ብዙነሽ ቡናቸውን ትተው እንደታዘዙት ደግፈው ያዟት:: ኑንሺና የእማማ ሸዋን ቤት ዘግታ የመጣችው አስናቁ ተጨንቀው ቆመዋል::

"ሂጂ አንቺ የሰዎቹን እራት አሰናጂ:: አልጫ ትልቁ ብረትድስት ውስጥ ከምሳ የተረፈ አለ ይበቃል:: ቀይ ወጥ ዝም ብለሽ ሽሮ ሥሪ" አሏት:: አስናቀች ወጥታ ሄደች::

"ጫን! አዎ ጫን ብለሽ አምጭ" አሉ እማማ ሸዋ:: ዳርም የለሽ ጥርሷን ነክሳ ትንፋሿን አምቃ ባለ ሃይሏ አማጠች::

እማማ ሸዋ "የወርቅ ፍልቃቂ" ብለው ያደነቁት፣ ወይዘሮ ብዙነሽ እንደ እርም የፈሩትና የጠሉት፣ ዳርምየለሽ ነፍሷን አስጨንቆ የመጣ በመሆኑ የሳሳችለት አዲሱ ሰው ዘጠኝ ወር ከስድስት ቀናት ከቆየበት የእናቱ ማህፀን



ዕድሜው ይጠር ይርዘም ወደ ማያውቀው አዲስ ዓለም መምጣቱን አወጀ::

መፈጠሩን ጠልቶት ይሆን ወዶት የሚያውቅ የለም:: ሰው ገና ከእናቱ ማህፀን ሳይወጣ ሲወለድ የሚገጥመውን እጣ ፈንታ በማወቅ 'ቀፈፈኝ. .ባልወለድ ይሻለኛል' ማለት ቢችል ምንኛ ደግ ነበር::

"እድለቢስ!" አለች ዳርምየለሽ በልቧ ልጇ እንደርሷ አባት የሌለው መሆኑን አስባ:: ማርገዟን ጠልታና ኮንና ስታለቅስ የከረመችውን ያህል ካብራኳ ተከፍሎ ስታይ ሳሳችለት::

እማማ ሸዋ የማዋለድ ተግባራቸውን ሲጨርሱ ከእናቷ መኝታ ላይ ተዘጋጀላትና ተኛች::

"ግን ሲያድግ ምን ይሰማው ይሆን?"

እርሷ እንደናቷ አባቱን ደብቃ በመንፈስ እንዲሰቃይ አታደርገውም:: አባቱን ባደረሰባት በደልና ግፍ እስከዘለዓለም ብትጠላውም በርሱ ሳቢያ ልጇን የትም መጣልና መበደል ግን አትፈልግም:: አባት እንዳለው ትነግረዋለች:: ይህን አውቆና ተረድቶ ካደገ እንደርሷ 'አባቴ ማን ነው?' በሚል ጭንቀትና ሀፍረት የሚሳቀቅ አይሆንም:: ከአራት ዓመት ፍቅር በኋላ የተፀነሰ እንጂ ማንዘራሽ ዲቃላ አለመሆኑን ታስረዳዋለች:: ለእርሱ ስትልም ባል የሚባል አታገባም:: የእምላ ብር ሥራ ካገኘች የማንንም እርዳታ ሳትሻ ኮስተር ብላ ታሳድገዋለች:: ብትችል እንዳውም የማያውቋት ሠፈር ቀይራ ትኖራለች:: ሁሉን ግልጽልጽ አድርጋ በልጅነት ካስረዳችው 'ዲቃላ' ቢሉት እንኳን ምንም የማይሰማው መንፈስ ጠንካራ ይሆናል:: እናቷ እርሷን እንደዚያ አድርገው ቢያሳድጓት ኖሮ አሁን የሚሰማት የመንፈስ ረብሻና ችግር ባልገጠማት ነበር::

ዳርምየለሽ በዚህ ሁኔታ ህጻኑ ከመወለዱ ጋር ባደረባት አዲስ የእናትነት ስሜትና ልጇን ለሌላ አሳልፋ ላለመስጠት በልቧ ቃል እየገባች ስታሰላስል ወይዘሮ ብዙ በፊናቸው ምን እንደሚያደርጉ ሀሳብ ገብቷቸዋል:: እንግዴ ልጁን ሽንት ቤት ጨምረው እስኪመለሱ የሚያስቡት ስለህጻኑ ለቅሶ ነው:: ምን ቢያደርጉት ይሻላል?

ቀለብተኞቹ ለራት ሲመጡ እያለቀሰ እንዲቆይ አልፈለጉም:: ህጻኑ ደግሞ አምርሮ ያለቅሳል:: ከመረበሻቸው ብዛት አፉን ይዘው ቢያፍኑት ተመኙ:: ከሰው አፍ ሊከታቸው የመጣ እርግማን አድርገው ቆጠሩት:: እውቆ ያለቅስ ይመስልም ከፉኛ ተናደዱበት::

ደማቸውን አስቆጥተው ዓይኖቻቸውን በልጥጠው ተጠጉና አፈጠጡበት::

መሬት ለዳርምየለሽ መውለጃ ከተነጠፈው ላይ ነው የተኛው::

"ይቅር ይበልሁ! ውሃውን ቶሎ በሉና ይታጠባ! ምነው ፈዘው ቀሩሳ አጓጓዎት መሰለኝ" አሉአቸው እማማ ሸዋ::

"ኧረ ምን ያጓጓኛል:: አጉልናዘር" አሉና አሰናቀች ውሃውን አሙቃ እንደሁ ለማየት ወደ ማዕድ ቤት ሄዱ::

የሞቀውን ውሃ ይዘው ተመለሱናም በባልዲ በርዘው አዘጋጁ:: ወደ ልጁ ከመውሰዳቸው በፊት ግን አዲስ ሃሳብ መጣባቸው:: የማጠቢያ ሰሃኑንም ባልዲውንም እዚያው ዕቃ ቤት አስቀመጡና ወደ መኝታ ቤት ገቡ::

"እህ? አልደረሰም? ልጁ አልቅሶ መሞቱኮ ነው:: ይታጠብና ታጥባው" አሉ እማማ ሸዋ::
"ላጥበው ነው" አሉና ህጻኑን አቅፈው ወጡ::
"የት ሊወስዱት ነው ታዲያ እዚሁ አያጥቡትም እንዴ?" በማለት ጠየቋቸው እማማ ሸዋ::
"እዚያው እዘጋጅቻለሁ::"

ኑንሽ ተከተለቻቸው:: ተመለሽ አይሏት ነገር ውሃ እያፈሰሰችላቸው በጥንቃቄ ቢያጥቡትም ከአዲሱ ሃሳባቸው ጋር እየተሟገቱ ነበር::
"ሂጂ ቁልፉን ከፍራሹ ሥር ፈልጊና ቁምሳጥኑን ከፍተሽ ጋቢ አምጪ!" አሏት ቁልፉ በጉያቸው መሆኑን እያወቁ::

ልታመጣ እንደወጣች ልጁን ሰሃኑ ላይ የማስቀመጥ ያህል አስተኙትና ሲያለቅስ ሥራቸውን ቀጠሉ:: የባልዲውን ውሃ በጓሮው መውጫ በኩል ደፍተው በሩን ዘጉት:: ከውሃ እንሥራው ወደ ባልዲው ቀዝቃዛ ውሃ ቀዱ:: ልጃቸውን እንዳትመጣባቸው እየተጣደፉ:: የሚበቃቸውን ያህል ይዘው ወደ ልጁ ተጠጉ:: ሆዳቸውን ፍርሃት ፍርሃት እያላቸው:: ሰውነታቸው እየተንቀጠቀጠ::

ባልዲውን አስቀመጡና ልጁን ከሰሃኑ ላይ አነሱት:: ማልቀሱን እንደቀጠለ ነው:: ልባቸው እየተሸበረ ለቀቁትና ላለማየት ዓይናቸውን ጨፈኑ:: ድርጊታቸው ለራሳቸው ዘግንኗቸው:: ህፃኑ ባልዲው ውስጥ እርፎ ድምጹ ሲጠፋ ቶሎ ብለው አወጡና በመጀመሪያው ሁኔታ ያዙት:: ነብሱ አልወጣችም:: እያቃሰተ ሰውነቱ ይርገበገባል:: እስከመጨረሻው ለመጨከን ስሜታቸው ታገሉት::

"እማዬ ቁልፉ የለም!" አለች ኑንሼ ተመልሳ::
"በቃ ተይውና እሱ ሳጠራው ላይ ያለውን ነጠላ አምጪ! የሞተች!"



ሲሉ ተቆጡ:: በመቆየቷ ሳይሆን ሥራቸው እንዳይታወቅባቸው ያሉት ነው:: በነጠላ ጠቅልለው የነበረበት ሲያስተኙት ትንሿ ነብሱ ልትወጣ ታጣጥር ነበር:: ያለማቋረጥ::
"እ -እ -እ -እ . . ." እያለ::
"ምን ሆኖ ነው? ደሞ ማልቀሱን ተወና ማቃሰት ጀመረ!" አሉ እማማ ሸዋ እንደዋዛ::
"እኔ ምን አውቄ ሳጥበው እንደዚ ማቃሰት ጀመረ" አሉ ወይዘሮ ብዙ የውስጣቸውን የስሜት ረብሻ ታግለው::
"ጡትሽ ገና ነው መሰል? በመጀመሪያ ጊዜ እኮ ቶሎ አይፈስስም:: እስኪፈርጥላት ንጹህ ውሃ አፍሉና በጡጦ ነገር ይጥባ:: እርቦት ይሆናል:: በስኒም ቢሆን እንግተዋለን" አሉ እማማ ሸዋ::

ወይዘሮ ብዙ ለይስሙላ የእማማ ሸዋን ሀሳብ ተቀብለው ውሃ በስኒ ቢያሞቁም ህፃኑ ለመጥባትም ሆነ ለመጋት ዕድሜ አላገኘም::

"ውይ! ይቅር ይበልሁ! በስ -ማ -ም! አንቱ ሞቷል ማለት ነው? በስማም" አሉ እማማ ሸዋ እያማተቡ ወደኋላቸው አፈግፍገው:: ዝምታው የእንቅልፍ መስሏቸው ለማረጋገጥ ነበር የተጠጉት::
"ኧረ እባክሁ!" አሉ ወይዘሮ ብዙ እንዳዲስ ደንግጠው ወደ ልጁ እየተስፈነጠሩ:: ከመጠርጠር ግን አላመለጡም::

ዳርምየለሽ ከተኛችበት በድንጋጤ ቀና ብላ እናቷን በቅሬታ ተመለከተቻቸው:: የደነገጡ ቢመስሉም ልቧ ጠርጥሯቸዋል::

"ገደለችው" አለች በልቧ:: አፍ አውጥታ ለምን እንደገደሉት ብትጠይቃቸው በወደደች:: ነገር ግን እርሷ ለራሷ በርሳቸው ሥር የምትኖር ሸክም መሆኗ ተሰማትና ጥርሷን ነክሳ ስሜቷን ተቆጣጠረችው:: ክፉኛ ጠላቻቸው:: አረመኔ አድርጋም ከነነቻቸው:: ረገመቻቸው:: -በልቧ:: በብርድ ልብሱ ተከልላ ተንሰቀሰቀች::

"አይዞሽ ልጄ አታልቅሽ" አሏት እማማ ሸዋ ምንም እንኳን ብትሸፈን እያለቀሰች መሆኑን በሰውነቷ መርገፍገፍና በሚያመልጣት የሲቃ ድምጽ ተረድተው:: "አንድዬ እርሱው አመጣብሽ እርሱው ወሰደልሽ:: ባይሆን ለወደፊቱ ትምህርት ይሁንሽ:: ሁለተኛ እንዲህ ያለ ስህተት ላይ እንዳትወድቂ ራስሽን መጠበቅ ነው:: አንቺ እንኳን በሰላም ተገላገልሽ እንጂ ልጅ የራሱ ጉዳይ ነው:: ገና ልጅ ነሽ ደግሞ ለሁሉም ትደርሽበታለሽ:: አታልቅሺ!" አሉ:: እርሳቸውም ቢሆን እናትየው አውቀው እንደገደሉት ጠርጥረዋል::

"ምን ቢያደርጉት ነው ግን?" አሉና በልባቸው ራሳቸውን ጠየቁ::

"ጠቅጥቃት"
"ሰው በላ"
"ነብስ ገዳይ"
"ጠቅጥቃት" እየተባባሉ ተቀባበሏቸውና ወደ ገደሉ ገፈተሯቸው:: ዥው ብለው ነብሳቸውን በመሳት ወረዱ::

"ተመስገን አምላኬ!" አለች ዳርምየለሽ ጩኸታቸውን አቁመው ዓይናቸውን በርጋታ ሲገልጡ:: የተጐዳ ሰውነቷ በድንጋጤ እየተንቀጠቀጠ ከራስጌአቸው በኩል ተቀምጣ ትከሻቸውን በመነካካት ስታማትብ ነበር:: ሁለቱ እህቶቿና ወንድሟም ከየተኙበት ተሯሩጠው በእናታቸው አልጋ አጠገብ ተሰልፈዋል::

"እማዬ!"

"ወይ" አሉ ከስመመናቸው ሙሉ ለሙሉ ሳይላቀቁ:: ከቅዠታዊ ጭንቀታቸው መውጣታቸው ከሞት የመነሳት ያህል ቢሰማቸውም ፍርሃታቸው አሁንም አለ:: እንደውሃ የሚንጨፈጨፍ ቀዝቃዛ ላባቸው ከውስጥ ልብሳቸው አልፎ አንሶላውን አርጥቦታል:: ጭንቅላታቸው የሚፈርስ መስሎ እንደከበዳቸው ነው:: በልጆቻቸው ተከብበው የኤሌክትሪክ ብርሃን በሚበራበት የራሳቸው ቤት ተኝተው እንዳለ ቢያረጋግጡም የህሊናቸውን ፍርሃትና ድንጋጤ ግን ሊሸሹት አልቻሉም::

"ኡይ! ኡይ! አይ!" አሉና በብርድ ልብሱ ፊታቸውን ተከለሉ::

"እንዴ ምነው እማዬ?" አለች ዳርምየለሽ ጩኸታቸው ስቅጥጧት:: ሌሎቹም ግራ በመጋባት ተጠያየቁ::

"ምን ነካት?"

"ምን ሆንሽ እማዬ?"

ወይዘሮ ብዙ ድርጊታቸው ህሊናቸውን ሲያተራምሰውና ሲያጋጨው ትናንት ሌሊቱን እንቅልፍ የሚባል ነገር በዓይናቸው ሳይዞር ዛሬ ቀኑንም ሲጨነቁና ሲሳቀቁ ነው የዋሉት:: ፍርሃት ፍርሃት ጨሂ ጨሂ ይላቸዋል:: ደርሰው ድንግጥግጥ ርብትብት ይላሉ:: በተለይ የዕቃ ቤታቸውን እንደ አንድ ነገር ሲፈሩትና ሲሸሹት ነው የዋሉት:: የዛሬውንም ለሊት እርሳቸው እንደፈሩና እንደጮኹ፤ ልጆቻቸውም እንዳሰቡና እንደተጨነቁ ነጋ::

"ሁለታችሁ ሀኪም ቤት ይዛችኋት ሂዱ" አለች ዳርምየለሽ ራሷ መነሳት እንደማትችል አስባ:: ማቴዎስና አስናቀችን::

"ከሆነ እኔ ቀድሜ ወረፋ ልያዛ?" አለ ማቴዎስ በሀሳቧ ተስማምቶ::

"ይሻላል በቃ:: የካቲት አሥራ ሁለት ሆስፒታል ወረፋ ያዝ" አለች አስናቀችም በቅርብ ያለ ሆስፒታል በመሆኑ::

"የካቲት እንኳን ዝም ብሎ ልፋት ካልሆነ ምንም ሊረዷት የሚችሉ



አይመስለኝም" አለች ዳርምየለሽ የአዕምሮ ህክምና መኖሩን ተጠራጥራ:: "በሽታዋ የመንፈስ መረበሽ ስለሚመስል የአዕምሮ ህክምና ወዳለበት ሆስፒታል ብትሄድ ነው የሚሻላት:: ለማንኛውም ቆይ እስቲ" ወገቧ እየተንቀጠቀጠ ተነሳች:: በወንድሟ ድጋፍ ወደ ስልኩ ሄደችና ለሩቂያ ደወለችላት::

ሩቂያ ትናንት ልትጠይቃት ስትመጣ ወልዳ ልጁ ወዲያውኑ መሞቱን ስለሰማች እርሷም ለጤንነቷ የህክምና ማረጋገጫ እንደሚያስፈልጋት አሳስባት ነበር:: ዳርምየለሽ ግን ባንድ በኩል ስለልጁ አሟሟት በልቧ የያዘችው ጥርጣሬ ስላለ፣ በእርሷም ሆነ በሞተው ህፃን ላይ የወሊድ ጠንቅ እንዳልነበር እርግጠኛ ሆና፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከእናቷ ሁኔታውን የመደበቅ ፍላጐት ውጪ ላለመሆን ተከላከለቻት:: እማይቀር አደገኛ ህመም ከተሰማት ግን ልትደውልላትና ሩቂያ የወንድሟን ወይንም የአባቷን መኪና ለምና ሆስፒታል ልትወስዳት እንደምትችል ተነጋግረዋል:: ዳርምየለሽ ይኼን ዕድል ለእናቷ ችግር ልትጠቀምበት ስላሰበች ነው የምትደውልላት:: ወዲያውም አንዱ ወንድሟ ሀኪም በመሆኑ ለሩቂያ ሲል ባንዳንድ ነገር ሊረዳቸው ይችላል:: የት ሆስፒታል መውሰድ እንዳለባቸው ማወቅም አንድ ርዳታ ነው::

"ለእማማ ሸዋም መንገር አለብን" አለች ስልኩን ደውላ ከወዲያኛው ጫፍ መልስ እየጠበቀች:: ማቴዎስ በእሽታ ራሱን ነቀነቀ::

# 49

እማማ ሽዋ ዕለቱ አርብ መሆኑን ያስታወሱት ከጳውሎስ ሆስፒታል ቅጥር ግቢ እንደወጡ ነው::

"ጉዴ!" አሉ በድንጋጤ ቀጥ ብለው::

"ምነው እማማ?" አለቻቸው ሩቂያ:: የዳርምየለሽን እናት ሆስፒታል አስተኝተው መመለሳቸው ነው:: ወንድሟ በዚያው ሥራ ስለገባ በአውቶብስ ለመመለስ ወደ ፌርማታው በማምራት ላይ ናቸው:: ማቴዎስም አብሯቸው አለ::

"ምንም አይደል ልጄ! እንዲያው አንድ ነገር ትዝ አለኝና ነው" አሉ በደፈናው:: ሆዳቸው ግን ፈርቷል::

በአሥራ ዘጠኝ ቁጥር አውቶብስ ተሳፍረው ወደ ፒያሳ ሲገሰግሱ ሆዳቸውን ባር ባር አለው:: ክፉ ክፉ ሃሳብ እየመጣባቸው:: አውቶብሱ እንደዚያ መብረሩን አልወደዱትም:: ወንበር ስላላገኙ በቆሙበት እንደ ምስሶ ከተተከሉት ብረቶች አንደኛውን ሙጢኝ ብለው አሁን ካሁን ይዟቸው የሚጋጭ ወይንም የሚገለበጥ እየመሰላቸው ልባቸው ተንጠለጠለች:: ሾፌሩ ፍሬን በያዘ ቁጥር ሰውን እርስ በእርሱ ሲያጋፋና ሲያንባብረው እርሳቸው ብረቱን እንዳይነጥቃቸው እየታገሉ ነፍሳቸውን ለፈጣሪያቸው አደራ እየሰጡ ያማትባሉ::

ሌላ ጊዜ በአብዛኛው ለገበያ ወደ መርካቶ ወይንም ሌላ ቦታ ሲሄዱ የሚጠቀሙት በአውቶብስ ቢሆንም ሳይጨነቁና ሳይሰጉ ነው የሚጓዙት:: እንዲያውም መገልበጥና መጋጨት የሚባል ነገር በሀሳባቸው ሳይገባ ስለሚገዙት ሽቀጣሽቀጥና ስለቤት ጉዳያቸው እንዳሰላሰሉ ነው መንገዱ የሚያልቀው:: አርብ ቀን ግን የትም አይወጡም:: አርብ ለእርሳቸው ጣጠኛ ነው:: አዋቂ በነገራቸው መሠረት አርብ ዕኩይ ቀናቸው ነው:: መንገድ ቢሄዱ፣ አደባባይ ቢወጡ፣ ሥራ ቢሠሩ አይቀናቸውም:: እንዲያውም ተጠንቅቀውና ራሳቸውን ጠብቀው ከቤት ካልዋሉ መጥፎያቸው እንደሚሆን ጭምር ነግሯቸዋል:: አዋቂያቸው:: ለዚህም ነው አርብን ለዓመታት ሲፈሩትና ሲሸሹት የኖሩት:: ዛሬ ግን. . .

ጥዋት አስናቀች በራቸውን ቆርቁራ ከቀሰቀሰቻቸው በኋላ የእናቷን መታመም ስትነግራቸው ደንግጠው ቀኑ ማን መሆኑን አላሰቡም:: ተከትለዋት ሮጡ እንጂ:: እርሳቸው ሲደርሱ ወይዘሮ ብዙ ፊታቸውን በእጆቻቸው



እየከለሉና ሰውነታቸውን እየቧጠጡ 'አቃጠለኝ'. . . 'በላኝ'. . . 'ወጋኝ'. . . በማለት እየጮኹ እነሩቂያ ወደ መኪና እያስገቧቸው ነበር:: ልክፍት መሆኑን ተናግረው ጠበል ቢወስዷቸው እንደሚሻል ተከራክረው ሰሚ ስላላገኙ ወደ ሆስፒታል አብረው መጡ:: አርብ መሆኑን ረስተው::

"ኡፍ!" አሉና በረዥሙ ተነፈሱ ከአውቶብሱ እንደወረዱ:: በሰላም በመድረሳቸው አንድዬን አመሰገኑት:: ከዚያ ወዲያ ያለውን በእግር ነው የሚሄዱት::

በማዘጋጃ ቤትና በጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን መሃል የሚገኘውን የመጀመሪያ አስፋልት እግራቸውን ሳያምኑ ልባቸው ተንጠልጥላ ሲደናበሩ ተሻገሩ::

"ምነው እማማ መኪና ይፈራሉ?" አለቻቸው ሩቂያ እንደ መብረር እያደረጋቸው ሲሻገሩ መኪና እንዳይገጫቸው ፈርታ::

"ይቅር ይበልሽ! ስንት ዓመት አዲስአባ ኑሬ መኪና ልፍራ!" አሉአት በጊዮርጊስ አጥር ጥግ ጥጉን እየተራመዱ::

"ታዲያ ምን ሆነው ነው?" አላቸው ማቴዎስ የሚቀጥለውን አስፋልት ሲሻገሩ እጃቸውን ይዞ ለማሻገር አስቦ::

"ቀኑ ነዋ! ቀኑኮ አርብ ነው"

"አርብ ምንድነው?" አለ ምን ማለታቸው እንደሆነ ሩቂያን በጥያቄ እየቃኘት::

"ኧረ ዝምብዬ ነው ልጄ! ክፉን ያርቅ" አሉ በልባቸው ያሰቡትንና የፈሩትን ቢናገሩ የሚደርስ ስለመሰላቸው:: ሩቂያና ማቴዎስ ግራ በመጋባት ተያዩ::

"ይቅር ይበላችሁ! ኧረ ቀስ በሉ!" አሉ እማማ ሽዋ ልጆቹ በጊዮርጊስ አጥርና በድሮው ማዘጋጃ ቤት መሃል ያለውን የመኪና መንገድ ሲሻገሩ እርሳቸው ፈርተው ቀረት እያሉ:: ከርቀት ብቅ ያሉትን ሁሉ ጠብቀው እያሳለፉ ቆዩና ለጊዜው ጭር ሲልላቸው ሮጠው የጉዳናውን አንደኛውን መንገድ ተሻገሩ:: ሁለተኛውን መንገድ ለመሻገር ጐዳናው መሃል የእግረኛው ክልል ላይ ቆሙ:: ጭር እስኪልላቸው:: ማቴዎስና ሩቂያ ከወዲያኛው ጠርዝ ተሻግረው እማማ ሽዋን ይጠብቃሉ::

እማማ ሽዋ በፊትና በኋላቸው ሽው ሽው የሚሉትን መኪኖች በፍርሃትና በስጋት እየገለማመጡ ተገትረው ቀሩ:: አሁን ካሁን መኪኖቹ መንገዳቸውን ስተው በላያቸው የሄዱ እየመሰላቸው ሽብር ድንግጥ እያሉ ሳለ ከምኒልክ አደባባይ ተጠምዝዞ ከፊታቸው ያለውን ጐዳና በመያዝ ሲከንፍ አዩት:: ትልቅ የጭነት መኪና:: ከፊቱ የነበሩትን መኪኖች በስተግራቸው እየደረበ መጣ:: ፈሩት:: በጐዳናው ከሚያልፉት መኪኖች ሁሉ ያ ትልቁ የጭነት መኪና እርሳቸውን ሊገጭ ከእግዚአብሔር የተላከ ፍርጃ መሰሎ ተሰማቸው:: የቆሙበትን ሥፍራ ያድነኛል ብለው ሊያምኑት አልቻሉም:: ወደ

ግራ ሳት አድርጐ እንዳይገጫቸው ፈሩ:: ማን ያውቃል የዓርብን ሰበብ::

ከቅጽበታዊ ሀሳባቸው ሳይወጡ መኪናው አጠገባቸው ደረሰ:: . . . በመንገዱ ግራና ቀኝ የነበሩ ሁሉ ተፈ.ፈ.ሁ:: አንዳንዱ ራሱን ይዞ፣ አንዳንዱ ዓይኖቹን ጨፍኖ፣ ሌላውም እንደየ አደነጋገጥ ልምዱ::

"እንደፈራሁት!" አለች ሩቂያ በድንጋጤ እራሷን ይዛ እያለቀሰች ወደ ወደቁበት ተሻግራ:: ማቴዎስም እመዱ ቡን እንዳለ ተከተላት:: ሰው ከየቦታው ተሰባስቦ መንገዱን ስላጣበበው መኪኖች ዝግ ብለው ከሰው እየተሻሹ ለማለፍ ተገድደዋል::

እማማ ሸዋ ከትልቁ መኪና ለማምለጥ ሲሸሹ ነው ሳይታወቃቸው ከኋላቸው ባለው ተቃራኒ መንገድ ወደ ምኒልክ አደባባይ የምትበር የቤት መኪና ስር ጥልቅ ያሉት::

ትራፊክ እስኪመጣ የገጨቻቸው መኪና ባለችበት ቆማ አሽከርካሪው ታክሲ ተከራይቶ ተገጭዋን ወደ የካቲት አሥራ ሁለት ሆስፒታል ይዞ በረረ:: ሩቂያና ማቴዎስም በተጠሪነት አብረዋቸው ሄዱ::

መኪናው የግራ ታፋቸውን ሲገጫቸው በቀኝ ጐናቸው ካስፋልቱ ነው የተፈጠፈጡት:: ከጠቅላላው ጉዳታቸው ተመልካችን ሁሉ የዘገነነው ከጆሮ ግንዳቸው የሚንፎለፎለው ደም ነው::

የአርብ ጠንቅ::



# 50

"እንሳው" አለ አቶ ስምኦን ጨዋታውን አቋርጦ ከእንዳለ ጐን ያለው ስልክ ደጋግሞ ሲንጫረር::

"ሃሎ! ገሬስ"

"ሃሎ! እባክዎን አቶ እንዳለ ይኖራል?" አለ ከወዲያኛው ጫፍ የመጣ ቀጭን ድምጽ::

"እንዳለ ነኝ ምንፈለጉ እመቤት?" አለ አንዳንድ እንባቢዎች በስልክ አስተያየት ስለሚሰጡት አሁንም እንደዚያው ገምቶ::

"ሻይ ቡና ጌታዬ" አለች በፌዝ ድምጽ 'እመቤት' ላላት ምላሽ 'ጌታዬ' እያለችው::

እንዳለ የደዋይዋን ማንነት ባያውቅም ቀልደኛነቷ አስገርሞታል::

"ሻይ ቡናውን አዝዤልዎታለሁ፤ ግን ማን ልበል?" አለ እርሱም አፀፋውን እየቀለደ::

"እንቱታውን ተወውና ማን እመስልሃለሁ?"

"ማን እመስልሃለሁ!"

"ወይንም ማን ብሆን ደስ ይልሃል?"

"ማን ብትሆን ይሻለኛል?" አለና ህሊናውን ጠየቀ:: ብትሆን ደስ የምትለውንማ ከተለያት ከራርሟል::

"እኔ እንጃ" አለ ግራ መጋባቱን በሚገልጽ አነጋገር::

"እሺ! ማን ማን ይደውሉልሃል?"

"እንዴት?"

"ማለቴ ሃሎ የምትልህ ማን ናት?"

"ማንም ሃሎ የምትለኝ የለችኝም"

"እስቲ ወደ ደሴ ሄደህ ለትመለስ ፈልጋት" አለች ፍንጭ ልትሰጠው::

"እ! ተና-ኜ! ተናኜ ነሽ?"

"ትጠራጠራለህ?" አለችው እየሳቀች::

"እይ አሁንማ አወቅኩሽ:: እንጂ ከባድ ፈተና እኮ ነው የፈተንሽኝ::"

"ለማንኛውም አልፈሃል" አለችው እየሳቀች::

"ፈታኙ መልስ ነግሮኝ ነዋ!" አለ እርሱም እየሳቀ::

"ታዲያስ ባክህ?"

"አለና"

"ምኑን ኖራችሁት፤ አንዴ እንኳን ሳትደውል ቀደምኩህ"

"ሥራ በዛና ዛሬ ነገ እያልኩ አመቺ ጊዜ ስጠብቅ እንጂ መደወሌስ የማይቀር ነበር" አለ ቅጥፈቱን።

"ለምኑ ነው አመቺ ጊዜ ያጣኸው ስልክ ለመደወል?"

"ኖኖ! ለስልኩ ሳይሆን ቀጠሮ ይዘን የምንገናኝበት ጊዜ ስመርጥ ነበር።"

"ቀጠሮ ካልተያዘ በስተቀር ስልክ ደውሎ ሰላም መባባል አይቻልም?"

"እሱ ልክ ነሽ ለምን እንዳላሰብኩት እንጂ ይቻል ነበር" አለ በሰበብ እማይገፋ ጥያቄ ሆኖበት።

"እኔ ደግሞ ጋዜጠኞችን እንደሚጽፉትና እንደሚያወሩት ቁም ነገረኞች አድርጌ ነበር የማያቸው"

"እኔኮ ሁሉን አልወክልም። ስንት ቁም ነገረኞች አሉ መሰለሽ"

"ዛሬ አሥራ ስድስት አይደል ከገባን. . ." ብላ ስንት ቀን እንደሆናቸው ለማሰብ ዝም አለች።

"ነሐሴ ዘጠኝ ነው የገባነው ልክ ሳምንታችን" አለና እንዳለ ቀደማት።

"ሳምንት ብቻ! ብዙ ቀን የሆነን ነው የመሰለኝ። የክረምት ቀናት አይገፉም እባክህ። ይረዝማሉ መሰል" አለችው።

"ቀናቱ ረዝመው ሳይሆን ክረምቱ ስሜታችንን ስለሚቀፍፈውና ስለሚከብደው ነው"

"እሺ! ደህና ነህ"

"ደህና ነኝ። አንቺስ?"

"እኔማ . . . ደህና ሆኜ ይኸው ደወልኩልህ።"

"ታዲያ መቼ እንገናኝ?" አላት ሌላ የሚያወራው ጠፍቶት።

"እኔ በደወልኩት ልትቀጥረኝ?"

"ኖኖ እንደሱ አትተርጉሚው" አለ እንዳለ አፍሮና ደንግጦ።

"ይልቅ ትናንት አነበብኩልህ"

"ምኑን?"

"ጋዜጣህን ነዋ! ስለ ሲዳማ ብሔረሰብ ያወጣኸው ቆንጆ ነው።"

"አመሰግናለሁ!"

"በተለይ ሁለት ነገሮች በጣም ነው ያስደነቁኝ።"

"ምንና ምን?" አለ በጉጉት።

"ይኼ፣ አንድ የሲዳማ ሰው ሩቅ ቦታ ሄዶ 'ቤቶች' ለማለት በነሱ ምንድነው? . . ." አለች የሲዳምኛው ቃል ጠፍቷት።

"አይዴ ምን ማና" አለና እንዳለ አስታወሳት።

"አዎ! እንደሱ ካለ በኋላ የሠፈሩን ደህንነት እየጠየቀ እስከ አምስት ደቂቃ ለሚሆን ጊዜ እደጅ በመቆም የእንግዳ ተቀባዩ ቤት ሴቶች ቤታቸውን እንዲያስተካክሉና ዕቃዎቻቸውን ሥርዓት አስይዘው መቀመጫ ቦታ እስኪያሰናዱ ጊዜ የመስጠቱ ጉዳይ በጣም የሚያስገርም ነው።"

"አዎ እኔም ጽሑፉ ደርሶኝ እንዳየሁት በጣም ነው የተደነቅኩት"



"ታውቃለህ! ይሄኮ ስለጠንን በምንለው የከተማ ሰዎች እንኳን የለም። በጣም ስልጡን የሚያስኝ ባህል ነው።

"በትክክል።የኮባ ናፕኪናቸውስ?"አለ የሃሳቧን ትክክለኛነት ካረጋገጠላት በኋላ።

"ሁለተኛው ደግሞ እሱ ነው። እስብ እስቲ አውሮፓውያን በናፕኪን ሶፍት ኬክ እንደሚይዙ የኛዎቹ ሲዳማዎች ደግሞ በኮባ ቅጠል ቆጮ!"

"በቅቤ የራሰ ቆጮ 'ቡርሳሜ' ይሉታል። በባዶ እጃቸው ቢጠቀሙ ቅቤው እንዳይንጠባጠብባቸው፣ ውሃና ጊዜም ለመቆጠብ" አለና አድናቆቷን አጠናከረላት።

"ታዲያ ይኼ ግሩም ስልጣኔ አይደለም?"

"በጣም እንጂ!"

"እንዳለ ሙት!" በጣም ቆንጆ ነው። እኔ እንዲያውም ጋዜጣ ማንበብ አልወድም ነበር። አንተ ጋዜጠኛ መሆንህን ስለነገርከኝ ሥራዬ ብዬ ነው የትናንቱ ጋዜጣ ላይ የፈለግኩህ። ሌላ ጊዜ ጋዜጣ ለቢሮአችን ሲመጣ ተቀብዬ ለአለቃዬ ማስተላለፍ እንጂ ማንበብ ደስ አይለኝም ነበር።"

"አመሰግናለሁ! ታዲያ ለምን ሻይ ቡና አልልሽም?" አለ በድጋሚ ስለራሱ ጽሑፍ ሲወያዩ ካደረበት የመዝናናት ስሜት ሳይወጣ።

"መቼ?"

"ዛሬ ከሰዓት ሥራ የለም"

"ዛሬ ከሰዓት እንኳን የምሄድበት አለ"። አንተን ከተመቸህ ነገ።"

"እንግዲያው ነገ ምሳ ልጋብዝሽ?"

"ተቀብያለሁ።"

ሰዓቱንና የሚገናኙበትን ቦታ ነግሯት ተሰነባበቱ።

"ማን ናት ባክህ ይኼን ያህል የምታናዝዝህ?" አለው አቶ ስምኦን ከብዙ ጊዜ ወዲህ እንዳለ በዚያ መልክ ረዥም የስልክ ወሬ ይዞ እንዳላየው በማስታወስ።

"ዝም ብላ አንዷ ናት!" አለ በማቃለል።

"ተናግራማ ነው ይኼን ያህል ሰዓት ያናዘዘችህ።"

"ከፊልድ ስመለስ አውቶብስ ላይ ተዋውቄአት ነበር።"

♣ ♣ ♣

"ሲያስፈራ! ልክ ኤስ ቅርጽ እኮ ነው" አለች በስተግራ የሃረጎን ጠመዝማዛ መንገድ ከገደሉ አስፈሪነት ጋር ስታስተውል ቆየችና።

"በጣም አስደሳች የመሬት አቀማመጥ ነው" አለ እንዳለም በተመሳሳይ አቅጣጫ ያለውን መልክአ ምድር እያስተዋለ። የተቀመጡት በአውቶብሱ

የግራ መስመር መቀመጫ ላይ ጐን ለጐን ሲሆን እርሷ በጥግ በኩል ናት።

"በዚህ መንገድ ስትጓዥ የመጀመሪያሽ ነው?" አላት እራሷ በከፈተችው የመግባባት ዕድል በመጠቀም።

"ኧረ ብዙ ጊዜ እመላለሳለሁ፤ አልለምደውም እንጂ"

"ደሴ ነው የምትኖሪው?"

"አይ የምኖረው እንኳን አዲሳባ ነው። እዚህ ዘመዶች ስላሉኝ ብዙ ጊዜ ለእረፍት እመጣለሁ።"

"አሃ! ሠራተኛ ነሽ ማለት ነዋ?" አላት። ተዝናንታ ስለምታናግረው ተዝናንቶ።

"አዎ! የዓመት እረፍት ስወስድ ሁልጊዜ ደሴ ነው የማሳልፈው። በፊትም ተማሪ ሳለሁ ክረምት ክረምት እመጣ ነበር። ታዲያ ሁልጊዜ ይኼን መንገድ እፈራዋለሁ። በፊትማ ጭራሽ ፊቴን በጨርቅ እሸፍን ነበር።"

"ለምን!" አላት ሳይገባው ቀርቶ ሳይሆን ጨዋታውን ለማራዘም።

"ፈርቼ ነዋ! ታውቃለህ የሚገለበጥ የሚገለበጥ ይመስለኛል። እስቲ ይታይህ ከዚህ..." አለችና ዓይኗን ጨፈነች።

"ሞት ትፈሪአለሽ?"

"እንዴ! ለምን አልፈራም! ሞትን የሚፈልግ አለ እንዴ!"

"መፈለግ ሳይሆን መፍራት ደግሞ ጥሩ አይደለም"

"እንዴ ጥሩ ነው እንጂ! ሞት ያልተፈራ ምን ይፈራል!" አለች አሁንም በማጋነንና በመደነቅ ተውጣ።

"ስልሽ፣ በመፍራትሽ የምታመጪው ለውጥ ካለ ትክክል። እዚህ ላይ ግን መሪውን የጨበጠው ሌላ ሰው ነው። ለመገልበጡም በሰላም ለመጓዙም ወሳኙ የሾፌሩ ጥንቃቄና የአነዳድ ችሎታ ነው። አንቺ ምንም ማድረግ ስለማትችይ ከጭንቀትና ከፍርሃት ነፃ ሆኖ መጓዝ ብቻ ነው" አላት።

"እንዳልከው ህይወታችንን የያዘው ሹፌሩ ቢሆንም እስከዚያው መፍራትና መጨነቃችን ግን የማይቀር ነው። አንተ ግን ከምር አትፈራም ማለት ነው?"

"እኔማ ለምን እፈራለሁ?"

"ጨካኝ ነህ ማለት ነው!" አለች ጥላቻን ሳይሆን አድናቆትን በሚገለጽ የአነጋገር ስልት።

"ጭካኔ እንኳን አይደለም።"

"ታዲያ ምን ይባላል?"

"ብቃአ! ከመፍራት ምንም የሚገኝ ነገር ስለሌለ ገና በይሆናል አልጨነቅም። ፈርቼና ተጨንቄ በሰላም ሲያልፍ ፍርሃቴ ከንቱ ነው ማለት እኮ ነው።"

"አያርገውና ተገልብጦ ብትሞትስ?"

"ሞትኩኝ ነዋ! ከሞት በኋላ ቁጭት የለ ደስታ። ጥሩም መጥፎም የሌለበት አለመኖር እኮ ነው።"

"እኔስ ይቆጨኛል። ታውቃለህ ነፍሴን በጣም እወዳታለሁ።" አለች



ነፍሷን ትደብቅ ይመስል ደረቷን በእጇ ደግፋ።

"ከሞትሽ በኋላ ምንሽ ይቆጨዋል? አትስሚ አትለሚ። ነፍስሽን መውደድ የምትችይው እኮ መጀመሪያ ነብስ ሲኖርሽ ነው። በድን ከሆንሽ በኋላ እንደ ድንጋይና እንደ አፈሩ ራስሽን መግለጽና ማወቅ የማትችይ ግዑዝ ነገር ማለት ነሽ። ሲወገርና ሲፈለጥ የሚቆጨው ድንጋይ አይተሽ ታውቂያለሽ? እኛም ከሞትን እንደዚያ ነን።"

"ማን ያውቃል። ድንጋይ ስላልሆንን ድንጋይ ሲፈለጥ የሚሰማውን ህዘን ይሁን ደስታ እኛ ባለማወቃችን ወይንም ስሜቱ ስለማይገባንም ሊሆን ይችላል።"

እንዳለ በሃሳቧ ቢደነቅም መልስ አላጣላትም።

"ጥሩ! ድንጋይ ማዘንና መደሰት ከቻለማ እሱ ራሱ ሌላ ህይወት ነው። ሞት ማለትም ከህይወት ወደ ህይወት መተላለፍ ይሆናል። ስለዚህ ልንፈራ አይገባም። ዞሮ ዞሮ ሞት የሚያስፈራ መሆን የለበትም።"

"ታውቃለህ? አደገኛ ፈላስፋ ነህ" አለችው ተናኜ ራሷው ባመጣችው ሃሳብ ወደ ራሱ መነሻ ሃሳብ ሲወስዳት ተደንቃ።

"እንደሱ እንኳን አትስደቢኝ" አለ እንዳለ በፈገግታ እየቀለደ።

"ሙት ውነቴን እኮ ነው። ለመሆኑ ምንድን ነው ሥራህ?" አለች ካደረባት አድናቆት ሳትወጣ።

"ምን እመስላለሁ?"

"ፈላስፋ. . . ደራሲ. . . እንደዚ እንደዚ ነገር።" አለች ትኩር ብላ እያየችው።

"እንዴት?"

"እነሱ ናቸው ስለህይወትና ስለሞት ብዙ የሚፈላስፉት። አንዳንዶቹማኮ ህይወትን ባዶ ነው የሚያደርጊት።"

"አንባቢ ነሽ ማለት ነው?" ብሎ ጠየቃት የእርሷን ጥያቄ ሳይመልስ።

"ትንሽ ትንሽ" አለችና የልቦለድ መጻሕፍትን ማንበብ እንደምትወድ ነገረችው።

እንዲህ እንዲህ እያሉ ጨዋታ ጨዋታን ሲስብ በመግባባት መንፈስ መንገዱ ሳይታወቃቸው ደብረሲና ደረሱ።

"ከአሜን ወደ በስመአብ አይሁንብኝ እንጂ እንዳለ ተመስገን እባላለሁ። የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ባህል አምድ አዘጋጅ ነኝ። አለ ከአውቶብሱ ከመውረዳቸው በፊት።"

"ተናኜ ፀጋዬ አገር ውስጥ ገቢ መሥሪያ ቤት ሴክሬታሪ"

"ፈቃደኛ ከሆንሽ ምሳ እኔ ልጋብዝሽ" አለ በሌላ እንዳትገምተው እየሰጋ።

ተስማምተው ወረዱና ሙዝ፣ ብርቱካን፣ በቆሎ እሸትና ሌሎችም ፍራፍሬዎች በሳጠራ ከሚጋፋባት ጐስቋላዋ ደብረሲና ሆቴል ተብዬዎች መሃል ይሻል ወደ መሰላቸው ገቡ::-ለምሳ::

አዲስ አበባ ገብተው እርሷ ሠፈሯ ባምቢስ አካባቢ በመሆኑ ለትራንስፖርት እንዲያመቻት መገናኛ ስትወርድ እድራሻቸውን ተለዋውጠው ነበር የተለያዩት::



# 51

ዳምኖ የማለደው የነሐሴ ወር ሦስተኛው ሰንበት ረፋዱ ላይ ገለጥለጥ አድርጓል:: እንዳለ ገላውን ታጥቦ ስለበረደው ሙቀት ለማግኘት መተላለፊያም፣ በረንዳም ግቢም ሆና ከምታገለግለው ጠባብ ቦታ ላይ በሸርጥና በካኒተራ ቆሟል:: ፎጣ ትከሻው ላይ ጣል አድርጐ::

በጉጉትና በስጋት ተወጥሮ የሚያስላስለው ስለዛሬው ቀጠሮና ምን ምን እንደሚያደርግ ነው:: የት እንደሚጋብዛት ለመምረጥ ፒያሳና አካባቢዋን በሃሳቡ ማተረ:: ከደጐል አደባባይ ወደ ሲኒማ ኢትዮጵያ በኩል እስከ አራዳ ፖስታ ቤት ውስጣውስጡን ጨምሮ አንድም ጥሩ ምግብ ቤት ወይንም ሆቴል አልታይህ አለው:: ከምኒልክ አደባባይ ወደ ደጐል ወረደ:: በሃሳቡ:: የታወቁ ሆቴሎች አሉ:: ቢኖሩም አካባቢው ሰው ስለሚበዛበት የግል ጨዋታ ለመያዝ አመቺ አይደሉም:: ከደጐል አደባባይ በአድዋ ጐዳና ወደ ራስ መኰንን ድልድይ አሰበ:: ሲኒማ አምፔርን አለፍ ብሎ አንድ ጥሩ ምግብ ቤት አለ:: መቀመጫዎቹ በስተኋላቸው ከታዛቢ ነፃ ናቸው:: ከፊት ለፊት ብቻ በትይዩ ጠረጴዛውን የጋራ አድርጐ ሌላ ሁለት ሰው የሚያስቀምጥ ወንበር ይኖራል:: ሰው ካልበዛ በስተቀር አንደኛው ሲያዝ ከፊት ለፊት ባለው ወንበር የሚቀመጥ ተጠቃሚ አይኖርም:: -እዚያ ነው የሚጋብዛት::

ከዚያ በኋላስ?

ከዚያ በኋላ ደግሞ ቴአትር ወይንም ሲኒማ እርሷ የመረጠችውን ይጋብዛትና ጊዜአቸውን ያሳልፋሉ:: ሲኒማ ብትመርጥለት ደስታውን አይችለውም:: አምባሳደር ይዟት ገብቶ ወደጥግ ይቀመጡና እሚዝናና መስሎ እጁን ትከሻዋ ላይ ያሳርፋል:: መብራት ሲጨልም ወደ አንገቷ ጠጋ እያለ 'ተጫወች' ይላታል:: ድንገት ሳብ አድርጐም ይስማታል::

"ሲስማት ምን ትለው ይሆን?"
"ልክ አይደለህም:: ታውቃለህ እኔ እንደዚህ አልጠበኩም ነበር" ብትለውስ?
"ምን አለበት የኔ ቆንጆ? ወደድኩሽ እንጂ አልጠላሁሽ" ይላታል:: እንዲያውም ከምሯ መሆኑን ለማወቅ "አጠፋሁ?" ብሎ ሹክ ይላታል::

"እሱስ አላጠፋህም"

ከዚያ ያለፈ ልትለው አትችልም። ማን ተቀጣጠሪ አላት? ማንስ ይኼን ሳያስብ ምሳና ፊልም ይጋብዘኛል ብላ ትጠብቃለች። ሞኝ አለ እንዴ? ለምን እንደቀጠራት መቼም አውቃ ላለማወቅ ካልሆነ በቀር ይገባታል።

እንዴ ከንፈሯን ከደፈረው፣ በኋላማ ያለስጋት ጭምቅ እያደረገ ያቅፋታል። ምጥጥ አድርጐ ይስማታል። -ብሎለማው። . . .

"ትኩስ ቁርስ አዘጋጅቻለሁ ግባና እንብላ" አለችው ታናሽ እህቱ አስቴር። ሰዓቱን እየተመለከተ ገባ። መሄጃውም ሊደረስ ነው።

♣ ♣ ♣

"የት ልትሄድ ነው?" አለችው አስቴር ወንድሟ ከዳርም የለሽ መጣላቱን ከነገራት ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ አስተካክሎ ለብሶ ሊወጣ ሲዘገጃጅ ተገርማ። ያውም በእሁድ ቀን።

"ከሰው ጋር ቀጠሮ አለኝ" አለ ቢገባት ይግባት ብሎ።

አስቴር ከዚያ በላይ መጠየቅ አልፈለገችም። ብቻ የደስታ ስሜት ተሰምቷታል። ክፍት እንዳለው ብዙዎቹን እሁዶች ከእርሷ ጋር እቤት ተቀምጦ የከረመው አንድዬ ወንድሟ ገጽታ ላይ ገና ለቁርስ ስትጠራው ጀምሮ ያየችው ፍካት የእርሷንም የእህትነት ስሜት ሰላፈካው። ምንም ይሁን ምን የዛሬ ቀጠሮውን ወዳለታለች። የትም ከማንም ጋር ይሁን ብቻ ደስ ብሎት ይዋልላት። የዘወትር አለባበሱን ሳይቀይር በተለይ እሁድ እሁድ በሀሳብ ሲብሰከሰክና አንዳንዴም ሠፈር ለሠፈር ሲጠባ መዋሉን አልወደደችለትም ነበር።

"ቆይ ቆይ ከረባትህ ትንሽ ተዛንፏል" አለችና ሙሽራ እንደሚያስብስ ሚዜ ፊት ለፊት እያስተዋለች አስተካከለችለት።

ቡኒ መልክ ሱፍ ኮትና ሱሪ ከብሩህ ቢጫ ሸሚዝ ጋር በጥቁር ቀይ ክራቫት ነው የለበሰው። ቀጠን ባለ ሰውነቱ ልክክ ብሎ እላዩ ላይ የተሰፋ ይመስላል። ሙሉ ልብሱን ያሰፋው ከሁለት ዓመታት በፊት በዳርምየለሽ አሳሳቢነት ነው።

"ኮት ስለሚያምርብህ ሙሉ ልብስ ብታሰፋ ይበልጥ ያምርብሃል" አለችው አንድ ቀን እንደዋዛ። እርሷን ለማስደሰት ገንዘብ አጠራቅሞ አሰፋ። ከዚያ በኋላ ለዓመት በዓል ቀንና ለ'ነፃው እሁድ' ውሎአቸው ሲገናኙ የሚለብሰው የክት ልብሱ ነበር። ተናኜስ ትወድለት ይሆን?



"እንዴት ነው?" አላት እህቱን በወንድማዊ ፍቅርና ፈገግታ ቃኝት እያደረጋት።

"ሌላ ነው! መቼም ዛሬ መመለስህን እንጃ። ወንድሜ ባትሆን ይቆጨኝ ነበር" አለች ለሽንገላ ሳይሆን ከልቧ እያደነቀችለት። ከራሷ ይበልጥ ወንድሟ አምሮና ኮርቶ ማየት ያስደስታታል። -አለኝታዋ ነውና።

መስታወት ቢያይ ይወድ ነበር። ሆኖም የእህቱን ትእዝብት አፈረ። ለዚያውም ቢቸግር እንጂ አለባበስን የሚያሳይ መስታወት በቤቱ የለም። እርሷ ካየችለት ይበቃዋል።

ተሰናብቷት ወጣ።

# 52

ከማዘጋጃ ቤት ፖስተር መለጠፊያ ሥር እንደ ፊልም ማስታወቂያ ደምቃና ጉልታ ቆማለች:: የለበሰችው ሮዛማ ጉርድ ቀሚስ ጠርንቅ አድርጉ የዳሌዋንና የመቀመጫዋን ቅርጽ ከዓይን አግብቶታል:: ከላይ የለበሰችው ባለ ጉንጉን አበባ ሀ ቅርጽ አንገትጌ ነጭ ሸሚዝም ወገቧ ላይ ጠበብ ብሎ ከወደጡቷ በመወጠር የምትፈነዳ አለዚያም የወገቧ ቅጥነት ለውነቷን መሸከም አቅቶት ቅንጥስ የምትል አስመስሏታል:: -ቀይ ናት:: ከአንገት በላይ ያላት ውበት ቢኖር ቅላቷና የፊቷ ጥራት ብቻ ነው:: ቡተረፈ ዓይን ከጥርሷ የማይለይ፣ ገጽታ ሙሉ የደስደስ:: ፀጉሯ አጠር ያለ ሲሆን ዘወትር በማይለየው ተኩስ ዛሬም አምሯል::

“ሌላ መስላለች!” አለ ባድናቆት ከበስተግራዋ አጠገቧ እስኪደርስ ውበቷን ከአለባበሷ ጭምር ገምግሞ:: “እኔም ሌላ መስያለሁ!” አለ ራሱንም ከእርሷ ጋር አወዳድሮ በኩራት::

“መቼም ባታይኝ ላልፍሽ ነበር” አለ መለስ ስትል ስላየችው::
“ለምን?”
“ሌላ ሆነሻል!”
“ይልቅስ አንተ ሌላ መስለሃል::”

አስፋልቱን ተሻግረው በእንዳለ መሪነት ወደ ፒያሳ ወረዱ:: -ለምሳ::

“ፊልም ይሻለናል ወይንስ ቴአትር?”

ከምሳ በኋላ ትንሽ ተዝናንተው እንዳለ ለተናኜ ያቀረበላት ምርጫ ነው::

“ለፊልም እንኳን ግድ የለኝም ቴአትር ብንገባ ግን አልጠላም::”

ባለበው መሠረት ሲኒማ እንዲገቡ ለማግባባት አልሞከረም:: ከመልሷ ሁለቱንም አማራጭ የወደደችለት አልመሰለውም:: ከሁለት አንዱን መርጣ ቢሆን ‘ይኼኛው ደስ ይለኛል’ አለዚያም ‘ይኼኛው ቢሆን እመርጣለሁ!’ ትለው ነበር:: ‘ግድ የለኝም’ እና ‘አልጠላምን’ ምን አመጣው? ሊያስደስታት



የሚችለው ምን ቢጋብዛት ነበር?

ጭንቅ ቢለውም እንዴ ካፉ ወጥቷልና ባለመጥላት የተቀበለችውን ቴአትር ሊጋብዛት ወደ ሀገር ፍቅር ቴአትር አመሩ::

♣ ♣ ♣

እንዳለ ከልቡ አይደለም ቴአትሩን የሚከታተለው:: እንዲያውም አንዳንዴ ይረሳውና ሙሉ በሙሉ በራሱ ሀሳብ ይሰምጣል::

“እርሷስ ስለምን ታስብ ይሆን?” አለ በሃሳቡ የጐሪጥ ሰረቅ አድርጐ እየተመለከታት::

“አሁን እውነት ከልቧ እየተከታተለች ነው? ሴቶች ሲባሉኮ ረቂቅ ፍጥረቶች ናቸው:: ቅድም ልጋብዝሽ ስላት ይኼን ያህል የምትመስለው ሲትዮ አሁን ተመስጣ አንዴ እንኳን ዓይኗን ከመድረኩ ያለመንቀሏ የሚገርም ነው:: አቤት ሴቶች! ስሜታቸውን ማመቅና መደበቅ ሲችሉ ሌላ ናቸው:: እኔ ምነው ተቁነጠነጥኩ! ታውቅብኝ ይሆን? ትወቃ! ይኼኔ እሷም ብትሆን በቴአትሩ የተማረከች መስላ የምታስበው ስለኔ ሊሆን ይችላል:: ‘የማነው ገሪባ!’ እያለች:: ማለት ይገባታል:: ሁሉም ነገር ከወንድ ሲመጣ ያምራል:: እስቲ ሰው ቆንጆ ልጅ ቴአትር ጋብዞ እጇን ትከሻዋ ላይ ጣል ለማድረግ ይፈራል? ባቅፋት ምን አለበት? መቼም ይኼ ሁሉ ትውውቅና ግብዣ ለምን መሆኑን አታውቅም ማለት የማይመስል ነገር ነው:: ሊያቅፋት ያስብና አካባቢውን ገልመጥ ሲያደርግ የሁሉም ትኩረት ወደ መድረኩ ነው:: ከፋቱ ከመድረክ የሚንፀባረቀው ብርሃን እንዲህ ዓይነቱን እንቅስቃሴ ለማጋለጥ በቂ ነው:: ያ ሁሉ ሰው በተመስጦ ከቴአትሩ ጋር ልቡ እንደተሰቀለ እርሱ ለማቀፍ እጁን ማንቀሳቀሱ እንደ ነውር ከበደው:: የእጁ እንቅስቃሴ ተመስጦአቸውን የሚረብሽና የሚታዘቡት መሰለው::ፈራናም ሀሳቡን እርግፍ አድርጐ ቴአትሩን ከልቡ ለመከታተል ሞከረ:: አልቻለም:: ከፊት ለፊቱ የቴአትሩን ታዳሚዎች በአድናቆት አስተዋለ:: በተለይ ወንድና ሴት ሆነው የተቀመጡትን:: በእርሱ ግምት አስቀድመው ተስማምተውና መፋቀራቸውን አውቀው የገቡ በመሆናቸው ቀናባቸው:: አንዳንዶቹ ያለምንም ጭንቀት ተቃቅፈው ከልብ ይመለከታሉ:: ማንም ቢያያቸው ግድ ያላቸው አይመስሉም:: እርሱ ግን ትወድለት አትወድለት ርግጠኛ ሳይሆን ቢያቅፋት ውጤቱ ፍቅር ሳይሆን ‘ትዕዝብት ለእፍረት’ ቢሆንስ?

“እንዴ? ተው እንጂ ምን መሆንህ ነው!” ብላ እጁን ከትከሻዋ ላይ በማንሳት ወደ ጐን ብታስቀምጥለትስ? -አቤት ቅሌት! ከኋለኛው ረድፍም ሆነ ከጐናቸው የተቀመጡ ተመልካቾች ምን ይሉታል?

ከብዙ ፍርሃትና ጭንቀት በኋላ የመድረኩ መብራት ከታሪኩ ጋር

ወደ ኋላው መለሰ፡፡ ሀብቴ በሩን ከኋላው ዘግቶ ተደግፎት ቆሟል፡፡ ፊት ለፊት ተፋጠጡ፡፡

እንዳለ የሀብቴን ቁልምጫ ትርጉሙ አልገባህ ብሎት በሀሊናው ማማጊቶ ቃሉን እየደገመ ከፊት ለፊቱ ፈዞና ነፍዞ ከቆመው በድን ጋር አዛምዶ ለመረዳት ሞከረ፡፡ ሁኔቷው የፀብ አይመስልም፡፡ ደግሞም እርሱ እስከሚያውቀው ለፀብ የሚያደርስ ግጭት የላቸውም፡፡ የስካር እንዳይለው ሀብቴን እስከሚያውቀው ዛሬ ከጠጡት በላይም ሲጠጣ ሰክሮ አያውቅም፡፡ የሚቀጥል እንቅስቃሴውንም ሆነ ንግግር ለማወቅ ቸኮለ፡፡

ሀብቴ በበኩሉ አዕምሮውን ሲያስጨንቀው የከረመው ሁለት ዓይነት ፍላጐቱ ተሳከረበት፡፡ እርሱ እንዳለን ያጠመደበት ምክንያት የጥላቻ ነው ወይስ. . .? አሁንስ የትኛው ፍላጐቱ ነው ተከትሎት እንዲንደረደር የገፋፋው? በሀሳብ ፈዝዞ አስተዋለው፡፡

አብረው አይተዋት ቀድሞ ሲያናግራት፣ እርሱን ሽቅርቅሩንና መልከ መልካሙን አመናጭቃ በሸሸችው ልጃገረድ የተመረጠና ልቧ እስኪጠፋ የተፈቀረው እንዳለ፤ ለሴትም ሆነ ለአለባበሱ ግድ የሌለው በእርሱ ዓይን 'ጭጎጊት ፊቱ' እንዳለ፤ ቀድሞት የተቀጠረውና ባለዲግሪው እርሱ እያለ የዩኒቨርስቲን አጥር ሳይነካ ከኋላው ተቀጥሮ በአለቆቹ የሚደነቀው እንዳለ፤ ሀሊናውን እንደ እሾህ እየቆጠቆጠ ባየው ቁጥር በበታችነት የሚያኮሰምነው እንዳለ፤ የመንፈሱ ጠላት ነው፡፡ ሲያየው ቀርቶ ስለእርሱ ሲያስብ ያመዋል፡፡ ጥርሱ ቢሰቅለትም፡፡ ጦር ሰብቆ ጋሻ ነቅንቆ ያልመጣበት፣ ቾል እያለና የዘረጋለትን ገመድ እንደዋዛ እየበጣጠሰ ውስጣዊ ሰብዕናውን የሚያኮስምን ብርቱ ጠላት፡፡ ሲጠሉት ባለማወቅ ወዶ፣ ሲርቁት ባለማወቅ ቀርቦ፣ ሲከዱት ታምኖ ራስን የሚያስጠላ ከራስ ጋር የሚያጣላ በቀል የማይገኝለት ጠላት፡፡ ሳይከታተል ሳያጠቃ ከእግሩ ሥር የሚወድቁለት ጠላት፡፡ እንዲህ ነው እንዳለ ለሀብቴ፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በሁለት ምክንያቶች ወንድነቱን ሲመኘና ሲያጠምደው ቆይቷል፡፡ አንድም የጤና ይሁን የበሽታ፣ የስቃይ ይሁን የእርካታ እየተምታታበት አዕምሮውን ሲረብሸውና ውስጠ ስሜቱን ባልተለመደ መልኩ እያመሰ ሲያፍተለትለው የከረመውን እኩይ ፍላጐት እንዲያስታግስለት፡፡ አንድም ለራሱ ያጣውን ተፈጥሮአዊ የስሜት ፀጋ እንዳለንም አሳጥቶ የደረሰበትን የህይወት ግፍና በደል ሊያጋባበት፡፡

ለሁሉም በአንድ መንገድ ይፈልገዋል፡፡ ይበቀለዋል፡፡ ይኼ መንገድ፣ ይኼ ምስጢራዊ ወጥመድ የስሜቱ ማስታገሻ የጥላቻውም መጨረሻ ነው፡፡ አስተማማኝ የጊዜና የቦታ አጋጣሚ የሚጠይቅ፡፡



የጉዳዩን ክብደት ሲያስበው አሁን ያለበት አጋጣሚ እመችነት አጠራጠረው፡፡ ከዚህ በተሻለ ሌላ አጋጣሚም ሊያገኘው እንደማይችል አሰበ፡፡ ከቢሮ በስተቀር አብሮት ላለመሆን ሲሸሸው እንደቆየ ያውቃል፡፡ ይህንንም አጋጣሚ ሊያገኝ የቻለው ረቡዕ ዕለት ከሥራ እንደወጣ ወዴት እንደሚሄድ ተከታትሎት ነው፡፡ የመጀመሪያው ዕለት በአጋጣሚ የተገናኙ ቢያስመስልም ከዛሬ ጋር ሦስቱን ቀናት ከቢሮ አብሮት ነው የመጣው፡፡ ጨዋታቸው ከአንገት በላይ ቢሆንም፡፡

እቀባብሎ ምላጭ ከተሳበ በኋላ ጥይቱን ለማስቀረት መሞከር ዲላማን ስቶ ራስን ለአደጋ ከማጋለጥ በቀር ከወንጀለኛነት አያድንም፡፡ ሀብቴም ሲያልም የከረመውን ዲላማ በቅጽበታዊ ስሜት እቀባብሎ ምላጩን ስቦታል፡፡ ያሰበው እንዳይታወቅበት ምንም ዓይነት ምክንያት ሊያቀርብ እንደማይችል ታየው፡፡ በጥያቄና በመደነቅ ያፈጠጡበት ድፍርስ ዓይኖች አስፈሩት፡፡

"ስሞክ" አለ ግራ እጁን በእንዳለ ትከሻ ላይ እንዳሳረፈ ቀኝ እጁን በለበሰው ኮት የውስጥ ግራ ኪስ ሰዶ፡፡ ሲጋራ እንደሚያወጣ ሰው፡፡

እንዳለ ከዓይኑ የገባውንም ሆነ የሰማውን ማመን አልቻለም፡፡

"ቀጥ ብለህ ቁም!" ነበር ያለው ከመቅጽበት ወደ አውሬነት ተለውጦ፡፡

"ምንም ዐይነት የጥቃት ሙከራ ብታደርግ ውጤቱ ያልተጠበቀ ይሆናል" አለ ሀብቴ ድምጹን ዝቅ አድርጐ፡፡ አነስተኛ ስለታም ሰንጢ በእንዳለ ጉሮሮ ሥር ሰያፍ ደቅኖበታል፡፡

እንዳለ ድንጋጤና መገረም እንደወረረው ደርቆ ቀርቷል፡፡ ምንም ዐይነት እንቅስቃሴም ሆነ ንግግር ለማድረግ አልሞከረም፡፡ ግራና ቀኝ በኮቱ ኪስ ውስጥ የሸጐራቸው እጆቹን በገዛ ራሱ እንዳሰራቸው በቁጭት አሰበ፡፡

"መጥፎ ልማድ!"

ሌላው ቀርቶ ፊቱ ላይ ያረፋትን የምራቅ ፍንጣቂዎች ለመጥረግ ቢሞክር ከርሱ ይልቅ የሀብቴ ሰንጢ እንደሚቀድም ገምቶ ጥቂት ፋታ የሚያገኝበትን የማዘናጊያ መንገድ አሰላሰለ፡፡ ምን ቢለው ነው ሊያዘናጋው የሚችለው? ፍላጐቱ ምን እንደሆነና ሰንጢ የደገነበት ለምን እንደሆነ አያውቅም፡፡ ለሰንጢ መምዘዝ ቀርቶ ለኩርፊያ እሚያደርስ ፀብ የላቸውም፡፡ በበኩሉ የሚርቀው ህብቴን በህብቴነቱ ሳይሆን ከዳርምየለሽ ጋር እያይዞ ከጠላቸው አራት ኪሎና አካባቢው ባልተለየ ስሜት ነው፡፡ ስለዳርምየለሽ ያየውንና የሰማውን እያነሳ መንፈሱን እንዳይረብሸው፡፡ በሥራም ቢሆን

የየራሳቸውን ድርሻ ከመወጣት ባሻገር አንደኛው በሌላው ላይ ጣልቃ ገብተውም ሆነ በጋራ የቢሮ አጠቃቀም አለመግባባት ፈጥረው አያውቁም:: ከዚህ በላይ በህሳቡ የመጣለት ነገር የለም::

"ምንድነው ፍላጐትህ?"

"ምንም" አለና ቅልስልስ ኮስተርተር በሚል ድብልቅ ስሜት ቀጠለ::

"ካንተ እምፈልገውና አንተን የሚጐዳ ምንም ነገር የለም:: ልዘርፍህ ወይንም ልገድልህ አይደለም ያስገደድኩህ:: እንዲያውም ማስገደድ አይባልም::"

"ታዲያ ምንድነው እሚባለው ሳላስብና ሳልጠብቅ በጓደኝነት ስም ሰንጢ መወደርህ ፍቅር መሆኑ ነው?" አለ እንዳለ እስካልተንቀሳቀሰ ምንም እንደማይደርስበት ስለተረዳ ተረጋግቶ::

"ተቸግሬ ነዋ! ምናልባት እምቢ ብትለኝስ?"

"ምኑን?" አለ እንዳለ ያልያዘውን የሌለውን ነገር አምጣ እንዳይለው ሰግቶ::

"እጆችህን ከኪስህ እንዳታወጣ! ድምጽህን ደሞ ቀንስ!" አለ ኮስተር ብሎ በማስጠንቀቅ::

"እንዴ! ለክሬል ማለት ነው ወይስ አብዷል?" አለ በልቡ ከደቂቃ በፊት የሚያውቀው ሀብቴ መሆኑን ተጠራጥሮ::

የሚያደርገው ጠፍቶት በፍርሃትና በጀብደኝነት ስሜቶች መሃል ተወጥሮ ሲጨነቅ ሀብቴ በዓይኑም በእጁም በሁለመናው እንቅስቃሴ ጭምር አንድ ነገር ጠየቀው:: ምን እንዳለው ቢገባውም የተጠየቀውን ከመፈፀም እንደምንም ተናንቆት እድሉን ለመሞከር ቆረጠ:: ነገር ግን ጉሮሮው ሥር ተስተካክሎ የተወደረው ሰንጢ የቆረጠ ሀሞቱን አቀዘቀዘውና የጭንቀት ላብ አስመጠው::

"ከዚያ በኋላ ግን ሌላ ከኔ የምትፈልገው ነገር የለም?" ሀብቴ ጭንቅላቱን ግራና ቀኝ ነቀነቀ:: የለም ለማለት:: ከዚያ በኋላም የሚፈልገው ነገር መኖሩን ልቦናው እያወቀ::

"እሺ ቶሎ በላ! ሁለታችን ባንድ ሽንት ቤት ለንቆይ ሰው ምን ይለናል?"

"የፈለገውን ይበል። አንድ ዐይነት ተንኮል አስባለሁ ብትል በዚ ሰንጢ የመጨረሻ ቀንህ ይሆናል" አለና ሰንጢውን ከእንዳለ ጉሮሮ ስር አንስቶ መሰናዶ ጀመረ::

"እሺ እኔ በምኔ አንትን ልበል?" አለ ኪሱ አንደገባ የታሰረ እጁን እያሳየው "ማውጣት ትችላለህ" አለው ሰንጢውን በጥንቃቄ ጨብጦ::

እንዳለ ሀብቴ ሊያሠራው የፈለገውን ድራማ ሲያስበው ዘገነነው::



እጁን ከኪሱ ለማውጣት በተሰጠው ፈቃድ አስታክኮ ድራማውን ለመቀየር በቅጽበት ወሰነ:: እናም ከኪሱ የወጡት ሁለቱም እጆቹ ወደ ሀብቴ ሰንጢ የያዘ ቀኝ እጅ ተወረወሩ::

ሀብቴ ያ እንዳይሆን ተጠንቅቆ ቢቆይም ለሆድ የሰነዘረው በእንዳለ ግራ እጅ ላይ አረፈና ተያዘ:: ከዚያ በኋላ ወደ ጉልበቱ የወረደ ሱሪው እግሮቹን እንደልብ ለማንቀሳቀስ አላመቸውም:: በግራ እጁ እርዳታ የተያዘ ቀኝ እጁን ለማስለቀቅ ታገለ:: እንዳለ ገፋ አድርጐ በመሳብ ራሱን ወደ ጐን አገለለና ከመዝጊያው ጋር አላተመው:: በዚያው እንቅስቃሴም ከስር በእግሩ ጠረበው:: ከዚያ በኋላ ሀብቴ ሚዛኑን ጠብቆ ራሱን መከላከል ስላልቻለ ሰንጢውን ተቀማ:: እንዳለም እንደነጠቀው በእልህና በንዴት ተውጦ መቀመጫው ላይ ሰካበት::-ሰንጢውን::

ሀብቴ ደመነብሱን እየተፈራገጠ ሲጮኽ እንዳለ ከተጐዳው የግራ እጁ አመልካች መሃል ጣቶች የሚፈስሰውን ደም በመሃረብ እየጠረገ ስለሚሰማው ጥዝጣዜ ሳይሆን እንዴት እንደሚያመልጥ ያስባል::

የቆርቆሮው መዝጊያ በሀይል እየተደበደበ ነው:: ለመፀዳጃ ቤቱ ራቅ እንዳለ የንቦች ሁካታ ይሰማ የነበረው የቡና ቤቱ ጫጫታ ቀረበው::

"ክፈት!"

"ምንድነው እሱ?"

"እንሰበረው እንጂ!"

"ፖሊስ ይጠራ"

# 54

፯

ሦስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ታስሮ አደረና እሁድ ጠዋት በዶክተር አብደላ ዋስትና ተፈታ:: "መጀመሪያ እነርሱን አድርሰን ወደ እኔ ቤት ብንሄድስ?" አለ ዶክተር ከፖሊስ ጣቢያው ወጥተው በበላይ ዘለቀ መንገድ ቁልቁል መኪናውን እያሽከረከረ::

እንዳለ መልስ ለመስጠት አመነታ:: ከተናኜ ጋር ለዛሬ የያዘው ቀጠሮ እንዳይስተጓጎልበት ሌሊቱን ሲያስብ ነው ያደረው:: መቅረት እንደሌለበት ይሰማዋል::

"ይሻልሃል እንድዬ" አለች አስቴር የእንዳለ ዝምታ እንድትናገር ገፋፍቷት:: ትናንት ማታ ወንድሟ መታሠሩን የማታውቀው ዶክተር በስልክ ሲነግራት በጣም ደንግጣ ነበር:: እድሜ ልኳን የምታየው ስላልመሰላት ለሊቱን ቁጭ ብላ ስታለቅስና ስትተክዝ ነው ያደረችው:: ወፍ ሳይንጫጫ ከአባቷ ጋር ፖሊስ ጣቢያው በር ላይ መንቆራጠጥ ጀመሩ::

አሁን ታዲያ ከእርሷ ጋር እንዲውል ብትመኝም ወንድሟን ያስፈታላት የዶክተር አብደላ ባለውለታነት ስለተሰማት ነው ጥያቄውን እንዲቀበል የፈለገችው:: ወዲያውም ዶክተር አብደላን ከመሰለ ቁምነገረኛና ትሁት ምሁር ጋር አብሮ መዋሉ የወንድሟን ትልቅነት የሚያሳይ ስለመሰላት:: እንዲህ አይነት ጓደኛ እንዳለው እስከዛሬ እንዴት እንዳልነገራትም ሲገርማት ነው ያረፈደው::

"ፕሮግራምህን እንደሁ የሰረዝከው መስሎኝ ነው" አለ ዶክተር የእንዳለ ዝምታ ለምን እንደሆነ ገብቶት::

እንዳለ መንገድ ከጀመሩ ለሦስተኛ ጊዜ ሰዓቱን ተመለከተ:: ሦስት ሰዓት ተኩል:: ለቀጠሮው የቀረው ግማሽ ሰዓት ብቻ ነው:: በግማሽ ሰዓት ቤቱ ደርሶ፣ ገላውን ታጥቦ፣ ልብሱን ቀይሮ ሊመለስ እንደማይችል አሰበ::

"ከእንግዲህ እንኳን አልደርስም"

"መደበኛ ፕሮግራምህ ከቀረ በቃ እኔ ቤት እንሂድ::"



እሺታውን ገለፀለት:: ከይሉኝታው እየተሟገተ:: ቀጠሮ ማፍረሱ ተሰምቶታል:: ለዛሬ ደግሶት የነበረው የፍቅር ውሎ መቅረቱም ቆጭቶታል:: ምንም ሊያደርግ አይችልም:: በስልክ አጋጣሚውን ገልጾ ይቅርታ ሊጠይቃትና ሌላ ቀጠሮ ሊያስይዛት ወሰነ:: ከዚያ የሚሻል አማራጭ የለውም::

እሁኑኑ ደውሎ ቅሪ እንዳይላት የሰጠችው ስልክ የቢሮ ነው:: በዚሁ ቀጠሮው ቦታ ተገኝቶ ሊነግራትም አሰቦ ነበር:: እንደዚያ ቢያደርግ ደግሞ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ መኖሩን እንጂ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር እንዳጋጠመው የሚገልጽ መንገድ አልመሰለሁ አለው:: አብሯት ለመዋልም አልተዘጋጀም:: ያልተበጠረው ፀጉሩና ሳምንቱን ሙሉ የለበሰው የዘወትር ልብሱ እርሷ ሆና ትመጣለች ብሎ ከገመተው አንፃር የአሸከርና እመቤት ያህል እንደሚያለያየው ተሰምቶታል::

የጊዮርጊስን አጥር ተታክከው በማዘጋጃ ቤት መርካቶ ሲታጠፉ ሳምንት እርሱን ስትጠብቅ ቆማበት የነበረውን አካባቢ በአይኑ ቃኝት አደረገ:: ቅር እያለው::

"እዚህ ሠፈር ነው ያደግከው?" አለ ዶክተር የእንዳለ አባትና እህት ከመኪናው ወርደው በምዕራብ ሆቴል ቁልቁል ሲወርዱ እያስተዋለ::

"አዎ! ከሊስትሮ ጋር ልጅነቴን ያሳለፍኩት እዚያች ስር ነው" አለ ከሆቴሉ ጥግ ሱቅ በደረቴና ሊስትሮዎች ወደተኮለኮሉበት እያመለከተው::

"አይ መርካቶ!" አለ ዶክተር በመደነቅ "በቃ እሁድ የለ ቅዳሜ ውር ውር ባይ አይጠፋም!"

"እንዴት ይጠፋል! በሺዎች የሚቆጠሩ ጉሮሮዎች መከደኛ እኮ ነው:: እንደ ትላልቆቹ አዳራሾችና ሱቆች ትናንሾቹም ዳር እስከዳር ቢዘጉና መደቦች ሁሉ ቢነሱ እሁድ እሁድ የሰንት ድሃ ወስፋት እንደሚጮኽ ያድር ነበር::"

"መቼም በእንዲህ ያለ አካባቢ ማደግ ጠንካራ ሰብዕናን የሚቀርጽ ይመስለኛል" አለ ዶክተር መኪናውን እያስነሳ::

"እንዴት?"

"ህይወትን በየፈርጁ ታያታለሃ! መርካቶ የሌለ ህይወት የለም:: ድህነት፣ ሃብት፣ ሌብነት፣ ሥራ፣ ልመና፣ ችሮታ፣ ማጭበርበር፣ መታመን፣ እብደት፣ ጤንነት ባጠቃላይ ጉስቁልናና ምቾት ተወሳስበውና ተቀላቅለው የሚገኙት መርካቶ ነው:: በእነኚህ መሃል ተወልዶ ማደግ ደግሞ ጠንካራ ሰብዕና እንዲኖርህ ያደርጋል ባይ ነኝ" አለ ዶክተር::

"መወለድና ማደጉ ምን ትርጉም አለው ብለህ ነው? በበኩሌ ጠንካራ ሰብዕና የሚቀረፀው ከተፈጥሮ ባህርይ ጋር በተያያዘ መልኩ እንጂ ተወልደው የሚያድጉበት አካባቢ ብቻውን ወሳኝነት ያለው አይመስለኝም" አለ እንዳለ::

"አለው እንጂ፤ ወሳኝ ነው ባይባልም ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው:: አየህ ለሰብዕናህ ጥንካሬ በአካባቢህ ያለው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ በአንተ አስተውሎትና ግንዛቤ ላይ ትልቅ ተጽዕኖ አለው::"

“በበኩሌ የጠቀስከው ነጥብ ለሰብዕና ጥንካሬ ብቻ ሳይሆን ለሰብዕና መላላትና መልፈስፈስም አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል ነው የምለው” አለ እንዳለ ብዙ ለመከራከር ዝግጁ በሆነ ስሜት::

“ምን ለማለት እንደፈለግክ አልገባኝም” አለ ዶክተር ዝግ ብሎ በሲኒማ ራስ ወደ ተክለሃይማኖት አቅጣጫ እያሽከረከረ::

“ማለት የፈለግኩትማ ጉዳትና ጥቅም ሁልጊዜም ተመዛዛኝ ናቸው ነው:: በአካባቢህ ላይ ጥልቅ ግንዛቤና አስተውሎት እንደሚኖርህ ሁሉ ላይኖርህም ይችላል:: ለምሳሌ አሁን ባነሳነው መርካቶ አካባቢ ማደግ ጠንካራ ሰብዕናን ሊቀርጽ የመቻሉን ያህል ደካማ ሰብዕናንም ሊፈጥር ይችላል ነው:: መቼም ጠንካራ ሰብዕና ስትል ችግርን በየፈርጁና በያመጣጡ ተቋቁሞ ሊወጣ የሚችል ማለትህ መሰለኝ” አለና ዶክተርን በጥያቄ አስተዋለው:: ዶክተር ጭንቅላቱን በአዎንታ ነቅንቆ አረጋገጠለት::

“መቋቋም ተስኖት ራሱን ጥሎ ሰብዕናውን አኮስምኖ የሚኖርስ የለም? አሁን መርካቶ ያደገ ሁሉ ጠንካራ ሰብዕና ያለው ነው ብለህ ታስባለህ? በርግጥ እንዳልከው የሌለ ህይወት የለም:: ያ ማለት ግን እዚያ ያደገ ሁሉ ሁሉንም ዓይነት ህይወት ይገነዘባል ማለት አይደለም:: አጠገቡ ያለው ለማኝ ለምን እንደሚለምን፣ ሀብታሙም ለምን ሀብታም እንደሆነ፣ ሌባው ለምን እንደሚሠርቅ ለሰከንድ እንኳን የማያስብ ወይንም ማሰብ የማይፈልግ ሞልቷል:: ከየአቅጣጫው በጥልቀት ቢያስብና ቢያገናዝብም እንኳ በሰብዕናው ከሚጠነክር ይልቅ ህይወትን ለመጥላትና ለመናቅ፣ አልፎ ተርፎም ለተስፋ መቁረጥና ለመውደቅ የሚደርስም አለ:: ደግሞም አንድ ነገር ልጠይቅህና ሰብዕናን ደካማና ጠንካራ አድርጉ ለመቅረጽ ተለይተው የተወሰኑ አካባቢዎች አሉ?”

“እንደዛ እንኳን ማለቴ ሳይሆን ለምሳሌ በአዲስ አበባ ከሌሎቹ ይልቅ የመርካቶ አካባቢ ምስቅልቅል የኑሮ ውጣ ውረድና ገጽታ ስላለው ህይወትን በቀላሉና በቅርብ ለመገንዘብ ይረዳል፤ በሚል መነሻ ነው” አለ ዶክተር የእንዳለ ጥያቄ በቀጥተኛ አሉታም ሆነ አወንታ ለመመለስ አስቸጋሪ ሆኖበት::

ሠንጋተራ ሲደርሱ ዶክተር መኪናውን አቆመና ቁርስ ሊበሉ ወረዱ:: ምን ጊዜም ቢሆን የተለያየ ሃሳብ ይዘው ሲከራከሩ ከቆዩ የሚያቆሙት በአመን አላምንም ደረቅ ሙግት ሳይሆን ከሁለት አንደኛቸው በዘዴ በሚያመጡት ሌላ ሃሳብና ምክንያት ተቋርጦ ነው:: በዚህ ሁለቱም ስለተግባቡ ዳግመኛ አያነሱትም::

“ምናልባት አየህ፣ እቤት አስቀድሜ ስላልነገርኳቸው እስኪሠራ ትጉዳለህ ብዬ ነው” አለ ክራቫት ባያስርም ደረቱ ላይ የሸሚዙን ጠርዝ እየነካካ::

“እኔ እንኳን መዋልም እችል ነበር” አለ እንዳለ ቢግደረደር:: ማታ ራቱን ስላልበላ ሳይነጋ ነው የሞረሞረው:: እህቱም ብትሆን ከመደንገጧ ብዛት ዓይኑን ማየቷን እንጂ የሚበላ እንደሚያስፈልገው አለማሰቧን ጥዋት ስትመጣ ምንም ነገር ካለመያዟ ተረድቷል::

“ባገር ሰላም ለምን ጾምህን ትውላለህ! እኔም ብሆን ቁርሴን አልበላሁም:: ቀማምሰን ብንገባ አይጎዳንም::”



# 55

ዶክተር አብደላ ከወላጆቹ ጋር ነው የሚኖረው:: በስፋት ከተንጣለለው ባለ አንድ ደርብ የወላጆቹ ቪላ በብሩህ ሰማያዊ የግድግዳ ቀለም የተዋበው ሰፊ ክፍል የእርሱ ነው:: መኝታውም ማረፊያውም::

የላሊበላና አክሱም ሀውልቶች፣ የዐባይ ፏፏቴ፣ የአፄ ቴዎድሮስ ፎቶ ግራፍ፣ ቱርኤፌል ፣ አርክ ደ ትሪዮምፍ፣ ሻንዝ-ኤሊዜ . . . በግድግዳው ዙሪያ ራቅ ራቅ ብለው ተሰቅለዋል:: በክፍሉ መሃል ለመሃል አራት ምቹ ወንበሮች ባጀቧት ድንክዬ የመስታወት ጠረጴዛ ሙሉ የውጪ ሃገር ጋዜጦችና መጽሔቶች:: በባለ ሦስት ተካፋች ረዥም ቁምሳጥን ውስጥ በአራት ደረጃ ጢም ያሉ ወፋፍራም መጻህፍት:: እነኚህ ናቸው የዶክተርን የተቀናጣ ህይወት ከሚያሳዩ ሌሎች ውድ ነገሮች ሁሉ ልቀውና ደምቀው እንደገባ የእንዳለን ዓይን የሳቡት:: እንኳን ለፖስተር በጋዜጣ ለማላመር ሙቅ እንደልሰን መርጉልኝ የሚል የቤቱ ግድግዳ፤ አለው ለመባል የሚበቁ ከሆኑ ያሉትን ጥቂት መጻህፍት የጠፈረባቸው ካርቶኖች ከአልጋው ስር እንዳሉ፤ በዕድሜ የምትበልጠውን ክንድ በክንድ ጭቅቅታም የመጻፊያ ጠረጴዛ፣በልቡ አሰባቸውና በዶክተር አብደላ ላይ መንፈሳዊ ቅናት አደረበት::

“ባንተ ከደረሰው መጥፎ አጋጣሚ በመለስ አብረን የምንውልበት ሁኔታ በመፈጠሩ በጣም ነው ደስ ያለኝ” አለ ዶክተር አብደላ ጥቂት አረፍ እንዳሉ::

“ያ ልክስክስ ጉድ ሊያደርገኝ ነበር፤ ዋጋውን ሰጠሁት” አለ እንዳለ በልቡ የሀብቴ ዝናቡን የትናንት ማታ ሙከራ በንዴት እያስታወሰ:: መንገድ ላይ ለዶክተር እየነገረው ነው ከቤት የደረሱት::

“ሴ ኖርማል! አውሮፖ ውስጥ በተለይም ምዕራብ አውሮፖ ካልተጠነቀቅክ በቀር በየጊዜው የሚያጋጥም ነገር ነው” አለ ዶክተር::

“ከየት አባቱ እንደተማረው ይገርማል! ለአንድ ኢትዮጵያዊ እንኳን መፈፀም ድርጊቱ እንዳለ ማወቁም ይቀፍፋል::”

“ለማንም ቢሆን ጤነኛ አዕምሮ ካለው ይዘገንናል:: ይኼ እኮ ከባህል ሳይሆን ከተፈጥሮም ሥርዓት ውጪ ነው:: አንድ ጊዜ ፖሪስ ውስጥ ምን ሆን መሰለህ . . .” አለ ዶክተር ፈረንሳይ ሀገር እያለ ያጋጠመውን በፈገግታ አስታውሶ:: እንዳለ በጉጉት ጆሮውን ሰጥቶ ጠበቀው:: መቼም የዶክተር

ሳያዩአቸው ቀርተው ይመስልሃል?"

ዶክተር አብደላ ለአውሮፖና አሜሪካ ፈጣን ሥልጣኔ አድናቆት እንዳለው ሁሉ ማህበራዊ ድቀቱን በተለይም በሀብታሞችና በድሆች መካከል ያለውን የሰማይና መሬት ልዩነት፣ ከራሳቸው አገር አልፈው ታላላቅ የሚባሉት መንግሥታት በታዳጊ አገሮች ላይ የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ ሲያስብ ያንገሸግሸዋል። ሥልጣኔአቸው ሳይሆን የጹር አውሬ ዓይነት ገናናነታቸው ነው የሚታየው። በዚህም የተነሳ "የምዕራቡ ዓለም ዲሞክራሲ፣ ሀብታሞች የድሆችን የመኖር ነፃነት ቀምተው ለበላይነታቸው ዋስትና የሚጨብጡበት የረቀቀ መሳሪያ ነው" የሚል አመለካከት አለው።

እንዳለ ሸንቱ ስለመጣበት ውይይታቸው ጋብ ሲል ጠብቆ መፀዳጃ ቤቱን ጠየቀው። በኮሪደሩ መጨረሻ ፊት ለፊት እንደሚገኝ ነገረው።

በሩን ከፍቶ ወጣና በቆመበት ደርቆ ቀረ። እርሷም አንድ ዓይነት ተናካሽ አውሬ የመጣባት ይመስል ሰውነቷ ተቆጥቶ ፀጉሯ ቆመ። ወደኋላዋ መሸሽ አሰኛት። እግሮቿ አልታዘዙላትም እንጂ። -ተፋጠጡ።

እንዳለ ወደ ግቢው ሲገባ በተለይ ያስተዋላቸው የአረንጓዴው በርና የቀዩ ቶዮታ መኪና ሚስጥር አሁን ገባው። ትንኮለኛው ህብቴ ዝናቡ ተርጉሞ የነገረውን አስታወሰ። አረንጓዴው በርም ሆነ ቀይዋ ቶዮታ የእነ ሩቂያ መሆናቸውንና በርግጥም ዳርምየለሽ ወደቦሌ ትመጣ የነበረው ጓደኛዋ ጋር እንደነበር አገናዘበ። ይሁን እንጂ ዳርምየለሽን የተዋት በህብቴ ዝናቡ ወሬ ሳይሆን ራሱ ባገኘባት ተጨባጭ ጥፋት በመሆኑ ራሱን ለመውቀስ አልደረሰም።

"ታዲያስ!" አላት። ከዳርም የለሽ ከተለየ አግኝቷት ባያውቅም ከእርሷ ጋር ፀብ የለውም።

"ምን ትሠራለህ አንተ ርኩስ!" አለችና ድንገት አምባረቀችበት። ከዚያ ወዲያ ከአፏ የሚወጡትን የስድብና የውግዘት ቃላት መምረጥና መቆጣጠር አልቻለችም። ለቀቀቻቸው።

"አንተ ጨካኝ! አረመኔ! ከሃዲ! . . ."

እንዳለ በሁኔታዋ ተደናግጦና እፍረት አሸማቅቆት ስድቡን እየጠጣ ዝም አለ። ሲሰርቅ እንደተያዘ ሰው ሹክክ ብሎ ምን ማድረግ እንዳለበት ሲጨነቅ የሩቂያን ስድብ እና ጩኸት የሰማው ዶክተር አብደላ ብቅ አለ። እንዳለ ከሩቂያ ስድብ ይልቅ የዶክተር መስማት አሳፈረው።

"ይቅርታ ዶክተር!" አለ የሚለው ጠፍቶትና ተጨንቆ።



"ምንዲየ! ምንድነው ነገሩ!?" አለ ዶክተር ሁለቱንም በጥያቄ እያስተዋለ።

"ይቅርታ ጋሼ! ይኼን አውሬ ከዚ ቤት አስወጣልኝ" አለች ሩቂያ የምትሰድበው የወንድሟን እንግዳ መሆኑ ለመጀመሪያ ጊዜ ተሰምቷት።

"ለምን? ምን አደረገሽ ሩቂያ? ደሞ ድምጽሽን ቀንሽ አባባ እንዳይሰማ"

"ከሃዲ ነው! አረመኔ አስወጣው!" አለች አባትና እናቷ በመኪና ሲወጡ ብታይም የወንድሟን ትዕዛዝ ለማክበር ድምጿን ቀንሳ።

"በምን ተገናኛችሁ?" አለ ዶክተር እርሱ እማያውቀው ከአሁን በፊት በሁለቱ መሃል የተፈጠረ ታሪክ እንዳለ ገምቶ።

"ምን አውቄ!" አለ እንዳለ ግራ እንደገባው። ጓደኛዋን አፍቅሮ ስለጠላ የእርሷ እንደዚህ መሆን ከምን የመጣ እንደሆነ ሊገባው አልቻለም።

"ምን አውቄ ይላል ደሞ! ልጅቷን ሲያታልላት ኖሮ ለመከራ አጋልጦ እንዳልሸሻት። አረመኔ!"

ዶክተር የእህቱ ንዴትና ስድብ ሊበርድ እንዳልቻለ ተገንዝቦ እንዳለን ይቅርታ ጠየቀና እርሱ ክፍል ገብቶ እንዲጠብቀው በማድረግ ሩቂያን ወደ ራሷ ክፍል ይዟት ገባ።

"ልክ አይደለሽም ሩቂ! እኔን ወንድምሽን እንዳዋረድሽ ቁጠሪ። ካንቺ የሚጠበቅ አይደለም። የዩኒቨርስቲ ትምህርቷን ልታጠናቅቅ አንድ ዓመት ከቀራት የነገ ምሁር ይሄን አይነት ባህሪ አይጠበቅም። ረጋ በይና ሁሉንም ነገር ንገሪኝ" አላት ተግሳፅም ማግባባትም በሆነ የአነጋገር ስልት።

"ይቅርታ ጋሼ! ባንተ በኩል ጥፋቴ ይሰማኛል። እርሱ ግን የአንተ እንግዳ መሆን የሚችል አይደለም" አለችው አሁንም እልኳ እየተናነቃት።

"ሳ ሴ ሞን ፕሮብለም! እሱን ለኔ ተይውና ያጣላችሁን ምክንያት ብቻ ንገሪኝ። የማናት ልጅ ለመከራ የዳረጋት?" አለ ዶክተር የራሷን ፍንጭ መነሻ አድርጐ።

"የኔ ጓደኛ። በቀደም አልነገርኩህም? መኪና ለምኜህ ጳውሎስ ሆስፒታል ያደረስካቸው ሴትዮ"

"እዎ! ልጃቸው ጓደኛሽ መሆኗን ነግረሽኛል" አለ ዶክተር ከሳምንት በፊት በሩቂያ ጠያቂነት ሆስፒታል ያደረሳቸውንና አልጋ ይዘው እንዲታከሙ የረዳቸውን በማስታወስ። ሰሞኑንም ለእህቱ ሲል ጤንነታቸውን ሲከታተል ነው የሰነበተው።

"እሷም እኛ ቤት ትመጣ ነበር። አንተ ከፈረንሳይ ልትመለስ ሰሞን ጀምሮ ይኺው ጨካኝ ባደረሰባት በደል የተነሳ ጤንነቷ ታውኮና በችግር ተይዛ ከቤት መውጣት ስላቆመች አላየሃትም እንጂ እነእማማ በደንብ ያውቋታል።"

"እሺ?!" አለ በቀጥታ ወደ ጉዳዩ እንድትገባ ፈልጐ።

ጓደኛዋ የእንዳለ ፍቅረኛ እንደነበረችና በእርሱ ፍቅር የተነሳ በትምህርቷ ቀንሳ ከእርሷ የተሻለ የማትሪክ ውጤት ታመጣለች ተብላ ስትጠበቅ ለኮሌጅ መግቢያ እንኳን ማጣቷን፣እውነተኛ አፍቃሪ መስሏትም ከእርሱ ጋር ሙጭጭ ብላ እንደኖረች፣ዘንድሮ በጥቅምትና ህዳር ወር አካባቢም በገጠማት ቤተሰባዊ ችግር የአዕምሮ ጭንቀት ደርሶባት ከቤት በመዋሏ ሊያገኛት ስላልቻለ እንዳኮረፋት፣ እርሷም መሃላቸው ገብታ እንዴት እንዳስታረቀቻቸው፣ ከታረቁ በኋላም ሦስት ወር እንኳን ሳይቆዩ አስረግዞ እንደከዳት፣ በዚህም የተነሳ ጓደኛዋ ቤተሰብ አውቆባት ሰው እንዳያያት ተደብቃ ያሳለፈችውን ችግር፣ እናትየውም በቀደም እንዳያቸው ለመንፈስ ጭንቀትና አዕምሮ በሽታ የተዳረጉት በዚሁ ተደራራቢ ችግር ሳቢያ መሆኑን. . . የምታውቀውን ሁሉ አንድ በአንድ ነገረችው::

"ጥፋተኛዋ እኔ ነኝ! ለዚህ ሁሉ ችግርና ጉዳት ያጋለጥኳት:: ይዋደዳሉ መስሎኝ" አለች ፋቂያ በስተመጨረሻ ራሷን እየወቀሰች:: በመጀመሪያው የእንዳለ ኩርፊያ መሃል ገብታ ባታስታርቃቸው ኖሮ በዳርምየለሽ ላይ የደረሰው ችግር አይደርስም እንደነበር በማሰብ ራሷን ስትወቅስ ነው የከረመችው::

ዶክተር አብደላ እህቱ በነገረችው ታሪክ ልቡ በሀዘን ቢነካም እንዳለን ጥፋተኛ ለማለት ግን አልቸኮለም::

"እንደነገርሺኝ ከሆነ ጓደኛሽ የምታሳዝን ናት:: ሆኖም ለደረሰባት ችግር እንዳለን በዳይ ከማድረግ በፊት የእርሱንም ችግር መረዳት ያስፈልጋል::"

"ምንም ችግር የለበትም!" አለች ወንድሟ በማያውቀው ጉዳይ ሊከራከራት መስሏት ስውነቷ ተቆጥቶ:: ስለ እንዳለ ጥሩነት ወይንም ችግር የሚሰማ ጆሮ የላትም::

"ማሌቴ ደረሰብኝ የሚለውን ማመሃኛም ቢሆን ማወቁ የግድ ይመስለኛል:: ሚዛናዊ ለመሆን:: አንቺም ብትሆኚ ማድረግ የሚገባሽን ነው ያደረግሽው:: እንኳንስ ይዋደዳሉ ብለሽ የምታምኚባቸውን ፍቅረኞች ሌሎችም ቢሆኑ ማስታረቁ ጥፋት ሆኖ ራስን ለመውቀስ አያደርስም" አለና ከንዴቷ ሊያቀዘቅዛት ሞከረ::

"በበኩሌ ስለእርሱ ምንም ማወቅም መስማትም አልፈልግም::"

"ረጋ በይ ፋቂ! እኔ አነጋግረዋለሁ:: ሁለቱ በራሳቸው ምክንያት ቢጣሉም አንቺን ለጓደኛሽ ተደራቢ አድርጌ ከእንዳለ ጋር የሚያጣላሽ ጉዳይ ያለ አይመስለኝም:: ጓደኛሽ ስለተቸገረች ብቻ ትክክለኛ አድርገሽ በማየት የእንዳለን ምክንያትና ችግር ሳታውቂ ልትወቅሺውና ልታዋርጅው አይገባም:: ያውም በቤትሽ:: በባህላችን ሊጋጨው ካልመጣ በቀር ማንም ሰው እቤቱ የመጣን እንግዳ መስደብ ቀርቶ ማኩረፍ ነውር ነው:: 'በቤቱ የሚኮራ ውሻ ነው' ይባል የለም" አለ ዶክተር ተስፋ ሳይቆርጥ እያግባባት::

"ጓደኛዬ ምንም ጥፋት የለባትም:: የርሷ ጥፋት ማፍቀሯ ነው:: ማመኗ"



"እንዴት አወቅሽ?"

"የጓደኛዬን ፀባይም ሆነ ለርሱ የነበራትን ፍቅር በደንብ ነው የማውቀው::"

"እንደዛ ማለት እንኳን አትችይም ፋቂ! ምንም በትምህርትሽ እየበሰልሽ ቢሆን በዚ በዚህ ጉዳይ ያለሽ ግንዛቤ እንደ እድሜሽ ልጅ ይመስለኛል:: አንድ ሰው ከራሱ በስተቀር ስለማንም አውቃለሁ ብሎ መናገር አይችልም:: በርግጥ አንዱ ሌላውን በድርጊትና በንግግሩ እንደ ቅርበቱ መጠንና ዓይነት ሊያውቀውና ሊገምተው ይችላል:: ያ ማለት ግን ፍጹም ሆኖ ስለዚያ ሰው ውስጣዊ ሰብዕና ያውቃል ማለት አይደለም:: ሰው ማለት ደግሞ ተፈትቶ የማያልቅ ረቂቅ ሚስጥር ነው:: እንኳንስ አንዱ ሌላውን እያንዳንዱ ሰው ራሱን የሚያውቀው በተወሰነ ደረጃ ነው:: አንቺም ታዲያ በጓደኛሽ ህሊና ውስጥ ያለውን ሚስጥር ሁሉ አውቃለሁ ብለሽ እንደማትከራከሪኝ ርግጠኛ ነኝ::"

"ከኔ የምትደብቀው ምንም ሚስጠር የላትማ:: ደግሞም እርሷ በነገረችኝ ሳይሆን ያደረሰባትን በደል ራሴ ባይኔ ያየሁት ነው::"

"እ! ፋቂ ያልተረዳሽልኝ ነገር አለ" አላት ዶክተር እንደ ትንሽ ልጅ ጉንጯን ቆንጠጥ አድርጎ:: በርግጥም ለእርሱ ትንሽ ናት:: እርሱ የመጀመሪያ እርሷ የመጨረሻ ልጅ በመሆናቸው በመሀላቸው ራቅ ራቅ ብለው የተወለዱት ሶስት ወንድሞቻቸው የፈጠሩትን ልዩነት ያህል ይበላለጣሉ:: ለዚህም ነው ዶክተር በትምህርት ችሎታዋ ዐዋቂ አድርጎ የሚያያትን ያህል በታላቅነት አቀራረቡ ደግሞ እንደ ትንሽ ልጅ የሚመለከታት::

"ማንም ሰው እኛ ከምናውቀው ሌላ የየራሱ ድብቅ ሰብዕናና ህይወት አለው:: ለዚህም ነው ስለሰው ልጅ ባህሪይና አፈጣጠር ማጥናት በዓለም ላይ ካሉት ሳይንሶች ሁሉ እጅግ ከባድና አስቸጋሪ ነው የሚባለው:: ጓደኛሽ ከዚህ ውጪ ልትሆን አትችልም:: የምታውቂውን ያህል ተናገርሽ እንጂ ጓደኛሽ ሌላ ህይወት ሌላ ሚስጥር ሊኖራት አይችልም ብለሽ መሟገት አትችይም" አለና ለምን እንደተለያዩ ማወቅ የሚችሉት ሁለቱ ተፋቃሪዎች ራሳቸው መሆናቸውንና ምክንያት ብለው ለየራሳቸው የሚያወሩት እውነት ሊሆንም ላይሆንም እንደሚችል አስረዳት::

ፋቂያም እንዳለ በዳርምየለሽ ላይ ካደረሰው በደል አንፃር ይቅርታ የማይገባው ጥፋተኛ መሆኑን ብታምንም ለምን እንደዛ እንዳደረገ ግን በርግጥም ዳርምየለሽ ከነገረቻት በስተቀር የእርሱን ምክንያት አለማወቋ የወንድሟን ሃሳብ እንድትቀበል አስገደዳት::

ዶክተር አብደላ እህቱን ካረጋጋ በኋላ ወደውጭ እንደማትሄድ አረጋገጠና ወደ እንዳለ ተመለሰ:: አጠቃላይ የታሪኩን ሚስጥር ለማወቅ ጓጉቷል::

# 56

"ይቅርታ እንዳለ ብቻህን አስቀመጥኩህ። ለተፈጠረው ችግር በጣም አዝናለሁ።"

"ምንም አይደል ዶክተር! ባንተ ስህተትና ፍላጐት የመጣ አይደለም" አለ በምንይለኝ ሲጨነቅ ቢቆይም የዶክተር ቅንነትና ትህትና እያስገረመው።

ዶክተር መጥሪያውን ተጭኖ ሠራተኛዋ ስትመጣ ቢራ ከግሮሰሪ ገዝታ እንድትመጣ አዘዛት። "ታዲያ ጠንቀቅ ብለሽ" አለ ከቤተሰብ ደብቃ ማስገባቱን የለመደችው ቢሆንም እያስጠነቀቃት።

"ሲጋራ ማጨስ ሳያስፈልግህ አልቀረም?" አለ ቢራው እስኪመጣ ሳይተርና ሲጋራ እያቀረበ። እንዳለ ተቀብሎ ለኰሰ።

"አንዳንድ አጫሾች ማጨስ ከንዴትና ጭንቀት ይገላግለናል ይላሉ" አለ ዶክተር ለራሱም ለኩሶ በተዝናና ሁኔታ። ጨዋታውን ለወጥ አድርጎ እንዳለን ለማዝናናት እንጂ ልቡን ያቆመውና መነጋገር የሚፈልገው ጉዳይ ሌላ ነው።

"አዎ! እንደሱ እሚሉ አሉ" አለ እንዳለ ከሀሳቡ ሳይወጣ።

"አንተ እንደሱ ከሚሉት ውጪ ነህ ማለት ነው!"

"አ – ዎ!" አለ እንዳለ ባሁኑ ስሜቱ ስለሲጋራ አጫጫስ የመወያየት ፍላጐት ባይኖረውም ለጥያቄው መልስ መስጠት ስላለበት።

"ብቻ በትክክል ምክንያቱን ላላውቀውም ማለት ሳይሻለኝ አይቀርም። ብናደድም ብደሰትም አጨሳለሁ። ባይሆን ስናደድ አሳሳቤ ለየት ይላል።"

"እንዴት?" አለ ዶክተር እንዳለ ሀሳቡን እንዲያስረዝም ፈልጎ። ማንም ሰው ቢሆን በውይይት መልክ ረዘም ላለ ጊዜ ከተናገረ እና በጽሞና ካዳመጡት የድብርት ስሜቱ እየተፍታታና እየተዝናና እንደሚሄድ ያምናል።

"ስናደድ ርቦት እንደሚበላ ሰው ቶሎ ቶሎ በላይ በላዩ ተስገብግቤ ነው የምስበው። ሲጋራ አይጠቅመኝም። ከንዴቴ ግን አይመልሰኝም። እንዲያውም ስስበው ፀብና ቁጭቴ ከሲጋራው ጋር ነው የሚመስለኝ። ያን ያህልም አጭሼ ታዲያ አንዳችም የስሜት መዝናናት አይሰማኝም።"

"በርግጥም የአንተ ለየት ሳይል አይቀርም። እኔ ደግሞ ለመዝናናት ብዬ ነው የማጨሰው ሱስ የለብኝም። ስፈልግ አጨሳለሁ ሳልፈልግ አላጨስም



ደስ ሲለኝ ብቻ።"

"ያንተ ጥሩ ምክንያት ነው ዶክተር! ብዙ አጫሾች ይሄን ሲሉ አትሰማም። የማጨሰው ስለምበሳጭ ነው፣ ለጭንቀቴ ማቃለያ ነው፣ ሌላም ሌላም ይሉሃል። እንጂ ስለሚያስደስተኝ አጨሳለሁ የሚልህ አታገኝም። እኔ በርግጥ የጀመርኩት ልጅ ሆኜ ሲስትሮ ስጠርግ ነው። ለቁንጥ ብዬ ጀመርኩ ስለምደው ጣመኝ። ከዚያ በኋላ ተበሳጨሁ አልተበሳጨሁ መተው የማልፈልገው ሱስ ሆነብኝ።"

"በነገራችን ላይ ቿሌት ተጠቀምክ ወይስ?" ብሎ ጠየቀው ዶክተር ድንገት ትዝ ብሎት።

"አልተጠቀምኩም" አለ ከመደንገጡ ብዛት ሸንቱ መጥቶበት እንደነበረ ረስቶት ቆይቶ አሁን ስላስታወሰው እየመጣበት።

"ምን-ዲየ! ታዲያ እስካሁን እንዴት ቻልከው በጣም ይቅርታ! አዘናጋሁህ። ሂድና ና!" አለ ዶክተር በይሉኝታ ሲጨነቅ እንደቆየ ተሰምቶት።

እንዳለ እየተሳቀቀ ወደ መፀዳጃ ቤት ሄደ።

"ከልጅቷ ጋር በምን ተጣላችሁ?" አለው እንዳለ ከመፀዳጃ ቤት ከተመለሰ በኋላ ጥቂት በዝምታ ቆዩና።

"የቷ ልጅ?" እንዳለ ያልገባው መሰሎ።

"ገርል ፍሬይንድህ?"

ቶሎ መልስ አልሰጠውም። በመልሱ ላይ ጥያቄ እያነሳበት ነገሩ እንዳይራዘም ስለፈለገ ምክንያቶቹን አሰባስቦ ባጭሩ ለመቁረጥ።

"ይቅርታ ግን በማያገባኝ ገብቼ ካስቸገርኩህ!" አለ ዶክተር የፊቱን መኮማተር አስተውሎ። እንግድነት ጋብዞት እንዳሰበው ሊያስደስተው እና ሊያዝናናው አለመቻሉ ተሰምቶታል። ሆኖም እህቱና እንዳለ በፈጠሩት እርሱ ያላሰበው ግጭት ምክንያት ጉዳዩ በመነሳቱ ዛሬውኑ ሁሉን አፍረጥርጦ ለማወቅና በሌላ ቀን አዝናኝ መስተንግዶ አዘጋጅቶ ሊክሰው አስቧል።

"እወዳት ነበር" አለ ዓይኖቹን ከዶክተር ጀርባ ወደ ግድግዳው ቀስቶ ራዕይ እንደሚመለከት ሁሉ ዳርምየለሽን ከህሳቡ የትዝታ ፊልም እያስተዋለ። ከዚህ በኋላ መሸፋፈኑ ዋጋ እንደሌለው ገብቶታል።

"እወዳት ነበር።" ከእርሷ በፊት ማፍቀር ቀርቶ ሴት ልጅ ትክ ብዬ ማየት እፈራ ነበር። እርሷን ካፈቀርኩ በኋላም ማንም ትሁን ማን ሴት የተባለች ካይኔ እንድትገባ አልፈቅድም ነበር። ቆንጆ ተብላ አገር የሚያደንቃት ሴት ላይኔ ሞልታ ቅንጣት ስሜቴን አትኮረኩረውም። ይልቁንም በምስለ ሄዋን የምትንቀሳቀስ ቆንጆም ትሁን ቆንጋ ባየሁ ቁጥር ከዓይኔ ድቅን የሚልብኝ

የእርሷ ምስል ነበር:: ምን ብዬ ልንገርህ! ዓይኖቼ ከእርሷ በስተቀር ሌሎችን ለማየት ታውረው ነበር:: ፍቅር፣ የይስሙላ ሳይሆን እውነተኛ ፍቅር አድሮብኝ:: እርሷም ታዲያ እንደኔ ትመስለኝ ነበር:: ለአራት ዓመታት ያለምንም እንከን ተፋቀርን:: ተፋቀርን ልበል እንጂ!"

አዲስ ሲጋራ ለኩሶ ሳብ ሳብ አደረገና ትኩረቱን እንደገና ወደ ግድግዳው መልሶ ንግግሩን ቀጠለ:: ዶክተር በአንክሮ ጆሮውን ሰጥቶት ትረካውን ያዳምጣል::

"አዎ!" በወቅቱ እርሷም ታፈቅረኛለች የሚል እምነት ነበረኝ:: ሳንተያይ የምናድርባቸው ቀናት ቢኖሩ በጣም ጥቂት ነበሩ፤ ለዚያውም ቢያንስ ስልክ ተደዋውለን::

"በተገናኘን ቁጥር ልባዊ ፍቅራችንን ከመግላለጽ አልፈን ስለ ዘለዓለማዊው ህይወታችን ቁርኝትና ስለሚኖረን የወደፊት አኗኗር በጋራ ያልተመኘነው በጐ ነገር የለም:: ምን ያደርጋል፤ እርሷ ለካ ውስጥ ውስጡን ሌላ መንገድ ይዛ እኔን ስታሞኝኝና እውነተኛ አፍቃሪ መስላ ስትደልለኝ ኖሯል:: የኋላ ኋላ ድብቅ ክህደቷን ተግባሯ እያጋለጠው መጣ:: እኔም . . ."

"ይቅርታ ላቋርጥህና ይኼ ውስጥ ውስጡን ያልከው መንገድ አልገባኝም" አለ ዶክተር ጠፍቶት ሳይሆን ከራሱ ለመስማት ፈልጐ::

"ባጭሩ ከኔ ሌላ ሰው ታውቅ ነበር::"

"ክርክር አታርግብኝና በምን እወቅክ?"

"በብዙ መንገዶች:: መጀመሪያማ በእምነት የተደፈነ ጆሮዬ የሰማውን እንጥሮ እየመለሰ ፍቅራችንን ስከላከልና የወሬ ንፋስ እንዳይገባን ስጠነቀቅ ቆይቻለሁ:: ስለ እርሷ ጥሩነት እንጂ መጥፎዋን ለሚያነሱ ቦታ አልሰጥም ነበር:: እያደር ጉዱ እያፈጠጠ መጣ እንጂ::"

"ምንድነው ጉዱ?" አለ ዶክተር እህቱ ካስረዳችው ሌላ ታሪክ መኖሩን ገምቶ::

"በጥቅምት ወር አካባቢ ነው:: በየቀኑ ካልተያየን ናፍቆትህን አልችለውም ትለኝ እንዳልነበር አሥራ አምስት ቀን ሙሉ ራቀችኝ:: እኔ ስልክ ደውዬ ሳነጋግራትም መልሷ ሁሉ ቁርጥ ያለ የመሰለቸት የሚመስል:: ለመገናኘት ቀጠሮ ስሰጣት ታመምኩ እያለች አለመቀበል፤ ተቀብላም መቅረት:: በቃ ምን ልበልህ አፍ አውጥታ አልፈልግህም ማለት ነበር የቀራት:: እኔ ሞኙ እውነት መስሎኝ በየቀኑ ስልክ እየደወልኩ ስወተውታትና በናፍቆት ስብሰለሰል ለካስ እጅሬዋ እሰወርዳ ተኝታ ነው::"

"እንዴት ልታውቅ ቻልክ?" አለ ዶክተር::

"ሰማሁእ! አስወርዳ መተኛቷን፣ ከማን እንዳስወረደች ሳይቀር የሠፈሯ ከሆነች ልጅ ሰማሁ" አለ ያን ጊዜ ማስወረዷን ሰምቶ እንደገና ማመኑና መታለሉ እንዳዲስ እያናደደው::



ዶክተር፣ እንዳለ በጠቀሰው ጊዜ ዳርምየለሽ መታመሟን እንጂ ማስወረዷን ከሩቂያ ስላልሰማ አስቀድሞ እንደገመተው በሁለቱ መሃል ብቻ የቀረ ምስጢር ስለመኖሩ ርግጠኛነት ተሰማው:: ቢሆንም አጣርቶ ለመረዳት የእንዳለን ምክንያት በቀጥታ አልተቀበለውም::

"ይቅርታ አድርግልኝና የሰሙት ሁሉኮ እውነት አይደለም:: ሰማሁ ብሎ ፍቅርን ያህል ትልቅ ነገር ማፍረስ ተገቢ አይደለም:: ፍቅር በተዘጋ ቤት ውስጥ እንደሚያንዱት ሻማ ነው:: በርና መስኮት ሲከፈት ሻማው ለንፋስ እንደሚጋለጥ ሁሉ ዓይንና ጆሮ ሲከፈት ደግሞ ፍቅር ለወሬኞች ይጋለጣል:: ታምናት እንደነበር ነግረኸኛል:: በትክክል ካፈቀርካት አለመገናኘታችሁንና ከሰው የሰማኸውን አሉባልታ ምክንያት አድርገህ እምነትህን ማፍረስ አልነበረብህም:: ለእምነት ከማመን በቀር ምንም ማረጋገጫ መንገድ የለውም:: በእምነትህ ላይ ጥያቄ እንስተህ መልሱን ከሌሎች ከጠበክ ጥርጣሬ ላይ ነህ:: ጥርጣሬ ደግሞ ጠንካራ ካልሆነ እምነት የሚያቆጠቁጥ የህሊና ረብሻ ነው:: እኔ አንተን ብሆን . . ." ብሎ ዶክተር በወቅቱ ይወስድ የነበረውን ርምጃ ሲናገር ሲል እንዳለ አቋረጠው::

"ዶክተር ያልገባህ ነገር አለ:: እኔ ይኼንን ብቻ መነሻ አድርጌ አልተጣላኋትም:: በርግጥ ለጊዜው ተስፋ ቆርጬ ለመተው ወስኜ ነበር:: በኋላ ግን በሩቂያ አማካኝነት እንደገና ተገናኝተን ሁኔታዋንና የሰውነቷን ጉዳት ስመለከት ጥርጣሬዬ በፍቅሬ ተሸንፎ የሰማሁትን ሁሉ እንዳልሰማ ሠርዤ ግንኙነታችንን ቀጠልን:: ይህንንም ሳደርግ አንተ እንዳልከው ከመተማመን በስተቀር ጥርጣሬዬንና የሰማሁትን ሁሉ አንስቼ መወያየቱ ለፍቅራችን እንቅፋት መፍጠር ስለመሰለኝ አንድም ነገር አልተነፈስኩም::ባለመገናኘታችንና እየቀጠረችኝ በመቅረቷ ብቻ ተቀይሜአት እንደነበር ገልጬላት ታምማ እንደነበር የሰጠችኝን ምክንያት ተቀብዬ በደፈናው ተውኩት::ስተወውም ያለሃጢአቷ በመጠርጠሬ ፀፀት እየተሰማኝ ነበር:: ጥርጣሬዬም ሆነ የሰማሁት ልክ እንደነበር በድጋሚ እንዳምን ያደረገኝ እና መታለሌን ግልጽ አድርጐ ያሳየኝ ግን ሁለተኛው ጥፋቷ ነው:: ያ ደግሞ ከሰው የሰማሁት ወይንም ከጥርጣሬ የመጣ አይደለም:: በተጨባጭ ራሴ በማውቀውና በደረስኩበት ማስረጃ ነው" አለና እንዴት አድርጐ እንደሚነግረው ጥቂት በዝምታ አሰላሰለ:: ዶክተርም ታሪኩን እስኪጨርስ ጣልቃ ላለመግባት በዝምታ ጠበቀው::

እንዳለ፣ እርሱና ዳርምየለሽ ከሦስት ዓመት በላይ ለወሲባዊ ግንኙነት የተጠቀሙበትን የተፈጥሮ የእርግዝና መከላከያ ዘዴ፣ በዚህ ዘዴ ሲጠቀሙም አንድም ጊዜ ችግር ገጥሟቸው እንደማያውቅ እና የዘዴውን አስተማማኝነት ከንባብ ባሻገር በሦስቱ ዓመት ልምዳቸው አረጋግጦ ሳለ ማርገዟ የውስጥ ለውስጥ ክህደቷን እንዳጋለጠው በዝርዝር ነገረው::

"ከዚህ በላይ ታዲያ ምን ማስረጃ ምን ነጋሪ ያስፈልጋል? የመጀመሪያው መታለሌ የልብ ልብ ስለሰጣት ዓይን ያወጣውን ድፍረት አመጣችው:: ከሌላ

የቋጠረችውን ዘር እንደፊተኛው ደብቃና ፈርታ ማስወረድ ሲያቅታት ዓይኗን በጨው አጥባ የእኔ ዕጻ ልታደርገው ሞከረች::"

"ያልገባኝ ነገር እንደገና ከተገናኛችሁ በኋላ አልወጣችሁም?" አለና ጠየቀው::

"አንድ ጊዜ ብቻ! እርሱንም ቢሆን እንደወትሮው ተጠንቅቀን:: ማለቴ ቀን ቆጥረን የወር አበባዋ ሊመጣ ሰባት ቀን ገደማ ሲቀረው::"

"ታዲያ አረገዝኩ ያለችህ ከስንት ጊዜ በኋላ ነው?"

"ህዳር ስድስት መሰለኝ:: አዎ! በደንብ አስታውሳለሁ:: የወጣነው ህዳር ስድስት ሆኖ የገና ዕለት ነው፣ የሰባት ሳምንት ቅሪት መሆኗን የሚገልጽ የሀኪም ማስረጃ ያሳየችኝ::"

"ያንተ ላለመሆኑና ከሌላ ለማርገዟ ማስረጃ አድርገህ የወሰድከው ታዲያ ምኑን ነው?"

"እህ!" አለ እንዳለ ሲገልጽለት ውሉ የዶክተር እንደ አዲስ መጠየቅ አስገርሞት::

"ማርገዟን ነዋ! እኔ ተጠንቅቄና ጊዜያዊ ስሜቴን ተቆጣጥሬ እስተማማኝ በሆነ ቀን እስከወጣን ያረገዘችው ከኔ ነው ብዬ ላምንም ሆነ ልቀበላት አልችልም:: ከእኔ ጋር ያላት ግንኙነት በዚህ የመከላከያ መንገድ እስከሆነ ደግሞ ከሌላ ለማርገዟ ምንም የሚያጠራጥር ነገር የለም:: ከሌላ ማርገዟ ደግም ከኔ ሌላ ሰው ታውቅ እንደነበር በፊት ሰምቼ ለናቅኩት ወሬ ሁሉ ማረጋገጫ ነው:: ከዚህ በላይ ምን ማስረጃ አለ?"

"ይኼ ብቻ ነው? የአራት ዓመት ፍቅራችሁን አፍርሳችሁ ለመለያየት ያበቃችሁ ምክንያት ይኼ ብቻ ነው?" አለ ዶክተር ከዚያ በላይ ምክንያት እንዳይኖረው እየተመኘ::

"ቀላል አይደለም ዶክተር:: የአራት ዓመት ፍቅር ሳይሆን የአራት ዓመት ድብብቆሽ የተፈታበት የበደል መጨረሻ ነው" አለ እንዳለ ከዶክተር አነጋገሩና ገጽታ ጉዳዩን ያቀለለበት ስለመሰለው::

"ሌላ ምክንያት ግን የለህም?" ጠየቀ ዶክተር በማዳገም:: የራሱን ሃሳብ ከመሰንዘሩ በፊት የእንዳለን ተበደልኩ ባይነት እስከ መጨረሻው ለማውጣጣት::

"ሌላ ምንም ምክንያት የለኝም"

እንዳለ የዶክተር ማዳገም የትዕዝብት ስለመሰለው በምን ሊለኝ ነው ሰጋት ተወጠረ:: በርሱ በኩል ጥፋት ሊባል የሚችል ነገር እንዳለ ለማስታወስ የእርሱንና የዳርምየለሽን ግንኙነት በህሳቡ ከለሰ:: ምንም ጥፋት የለበትም::

"ዝ ረግሬት! አዝናለሁ!" አለ ዶክተር ከእህቱ የሰማውን እንዳለ ከነገረው ጋር አገናዝቦ አጠቃላይ ታሪኩን በመረዳት::

"አዝናለሁ እንዳለ! የማንኛችሁ ጥፋት እንደሆነ መፍረድ ቢያዳግተኝም በተለይ በልጅቷና በቤተሰቧ ላይ በደረሰው ሁሉ አዝናለሁ::"



"እንዴት!?" አለ መገረምም ድንጋጤም ባዘለ ስሜት:: አዘኔታው ከምን ሊመጣ እንደሚችል መገመት ተሳነው:: ዶክተር እስኪነግረው ስንቱን ስንቱን አሰበ::

"ምን የሚያሳዝን ነገር መጣ? ምን ደርሶባት ይሆን? በተለይ በልጅቷና በቤተሰቧ? ቤተሰቧ ደግሞ ከኔ ጋር ምን አገናኛቸው? ተፋቀርን ተለያየን:: ከማንም ይሁን ከማ ዲቃላ ወለደች:: መውለድ ደዌ አይደለም:: ታዲያ ዶክተር ይኼን ያህል ምን አሳዘነው? ጥፋቱ የራሷ መሆኑን እየነገርኩት! ነው ወይስ . . ." አለና መጥፎ መጥፎ ህሳቦች መጡበት:: ምንም ብትበድለው ለእርሷ የማይመኛቸው:: በፍቅር አብረው ሳሉ የምትለው ትዝ አለው::

"ለመጀመሪያም ለመጨረሻም ያፈቀርኩት አንተን ነው:: . . . ከአንተ ተለይቼ ከምኖር ህይወቴን ባጠፋ ይሻለኛል:: . . . ህይወት የሚወዱትን አግኝቶ መኖር ነው:: አንተን ካጣሁ ምን ሊያስደስተኝ እኖራለሁ:: ራሴን ነው የማጠፋው. . ." ትለው ነበር:: ታዲያ ይኼን የምትለው "አሁን እኔ ብሞት ምን ታደርጊአለሽ?" ሲላት ነበር:: በህይወት እያሉ ስለመለያየት ሁለቱም አንስተው አያውቁም:: የፈራውን መጥፎ ወሬ ላለመስማት በልቡ አማተበላት::

ዶክተርም በበኩሉ ለሁለቱ ተፋቃሪዎች መለያየት ምክንያት የሆነውን ጉዳይ ስለተረዳ እንዳለ የወሰደው ርምጃ ትክክል አለመሆኑን በምን መንገድ ሊያሳምነው እንደሚችል በዝምታ ያሰላስላል:: ርምጃው ትክክል ባይሆንም እንኳ ጥፋተኛ አላደረገውም::

"ጥፋተኛ ማን ነው? እንዳለ ያነበባቸው መጻህፍት? ወይንስ የእንዳለ ስለጉዳዩ በጥልቀት ያለማወቅ? ወይንስ ተፈጥሮ? -መልሱ ውስብስብ ነው:: ዞሮ ዞሮ ግን ሦስቱም በዳርምየለሽ ላይ ለወረደው ችግር አውቀውም ቢሆን ሳያውቁ ተረዳድተዋል:: ተረባርበዋል:: የአንዲት ንጽህትና ምንም የማታውቅ ሰብአዊ ፍጡር ህይወት እንዲበላሽና በእርሷም ሆነ በቤተሰቧ ላይ የሥነልቦና ቀውስ እንዲደርስ አድርገዋል:: ሳይንስ-እንዳለና ተፈጥሮ::"

ዶክተር በሃሳቡ መሃል አንድ ዘዴ ስለመጣለት ለተንጠለጠለው የእንዳለ ጥያቄ መልስ ሳይሰጥ መጻህፍት መደርደሪያው ላይ መፈለግ ያዘ::

"ይኼ ሰውዬ ምን ነካው! ማዘን መጽሐፍ ያስነብባል እንዴ? ነው ወይስ በሰለጠነ ዘዴ 'ውጣልኝ' ማለቱ ነው? ምን አደረግክ ሊለኝ ነው? ነው ወይንስ ከኔ ይልቅ እህቱ የነገረችውን አምኖ ውሸታም አደረገኝ? ምን ብላ ነግራው ይሆን? ብቻ በሱ አላዝንም:: ከእኔ ይልቅ እህቱ ስለምትቀርበው ቢያምናት አያስደንቅም::"

ለመውጣት ወስኖ በምን መልኩ እንደሚለናበተው ሲጨነቅ "ይቅርታ!" አለው ዶክተር ሦስት የእንግሊዘኛ መጻህፍት መርጦ በመመለስ::

"ምንም አይደል! እንዲያውም ሥራ ካለብህ እኔም ብሄድ ይሻላል" አለ መከፋቱ እንዳይታወቅበት ካነጋገሩ ለስለስ እያለ::

"ኖኖ! ውይይታችንን እንጨርስ እንጂ፣ ለጥቂት ደቂቃዎች ታገሰኝ:: መነጋገሪያ የሚሆን ነጥብ እየፈለግኩኝ ነው:: ይቅርታ ብቸኝነት እንዳይሰማህ!" አለው::

"ምንም አይደል" አለና ከፊቱ በክቡ ጠረጴዛ ላይ ካሉት የፈረንሳይኛና እንግሊዝኛ መጽሔቶች አንዱን የእንግሊዝኛ አነሳ:: የተረጋጋ ለመምሰል እንጂ ስዕል ስዕሉን እየመረጠ እንደሚያይ መሃይም ገጾቹን ቶሎ ቶሎ ከመግለጥ በቀር አንድም የሚያስተውለው ነገር አልነበረም:: ልቡናው እዚያው ግራ መጋባቱ ላይ ነው::

ዶክተር አብደላ ፒ ኤች ዲውን ያገኘው በተለይ በልብ ህክምና ቢሆንም በሌሎች የህክምና ዘርፎችም ላይ ያለው ዕውቀት በቀላሉ የሚገመት አይደለም:: በተለይ ፈረንሳይ አገር በቆየባቸው የትምህርት ዓመታት ከራሱ የጥናት ዘርፍ ውጪ ሌሎችንም ባለው ጊዜና አቅም ሁሉ ከላይብረሪ፣ ከመምህራንና ከሌሎችም የዕውቀት ምንጮች ደህና አድርጐ ቀስሟል:: አዲስ አበባ ከተመለሰም ከፖሪስ ይዟቸው ከመጣቸው ጋር በየአንዳንዱ የህክምና ዘርፍ ላይ ያተኮሩ በርካታ መጻህፍትን ገዝቶ መደርደሪያውን ሞልቷል:: እናም ከሥራና ከማህበራዊ ኑሮ የተረፈውን ጊዜ የሚያሳልፈው ከነዚሁ መጻህፍቱ ጋር ነው:: ከሙያ ባልደረቦቹም ሆነ ከአንዳንድ ህሙማን ስለማንኛውም ዓይነት የጤና ችግር ከተወያየ ወይንም ራሱ ትዝ ካለው እቤት እንደገባ የሚመለከተውን መጽሐፍ ያገላብጣል::ከሁሉም በላይ ደግሞ የሥነ-አዕምሮ ህክምና ላይ ማተኮር ይወዳል:: በርካታ የሳይኮሎጂና የሳይኪያትሪ መፃሕፍትም አሉት:: ይኸው ዝንባሌና ትኩረቱ ሳይሆን አይቀርም ሁልጊዜም የሰዎችን ውስጣዊ ችግር ጠለቅ ብሎ እንዲያውቅና ካወቀም በኋላ ለመርዳት የሚገፋፋው:: አሁንም በጣም የሚወደው ምግብ ሲቀርብ አይቶ ለመብላት እንደቸኮለ ሰው በጉጉት ተወጥሯል::

ሁለቱ ፍቅረኞች የተጣሉበትን ሚስጥር ለራሱ ቢረዳውም እንዳለ መቶ በመቶ እውነት ብሎ ያኖረውን እምነት ከጭንቅላቱ በፍጥነት ጠራርጐ በማውጣት ትክክለኛውን ሁኔታ ባጭሩ ሊያሳምንለት የሚችለው አንዳንድ ነጥቦችን ከመጻህፍት እየመረጠ ቢያስነብበው መሆኑን አምኖበታል:: ያለዚያማ በንግግር ብቻ የእንዳለን ጥያቄዎች መመለሱ ከባድ ነው:: ከሦስቱም መጻህፍት በየማውጫቸው መሠረት የሚፈልጋቸው ነጥቦች ያሉባቸውን ገጾች ጠርዝ አጠፍ እያደረገ ምልክት ከያዘ በኋላ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጣቸው::

"ይቅርታ እንዳለ፣ ለምጠይቅህ ጥያቄዎች ያለቅሬታ መልስ ስጠኝ?



አታውቅም ብዬ ሳይሆን ውይይታችንን ቀላል ስለሚያደርገው ነው"

እንዳለ ጭንቅላቱን በመነቅነቅ እሺታውን ገለፀለት::

"እስቲ በቅድሚያ ስለተፈጥሮ የወሊድ መከላከያ ዘዴዎች የምታውቀውን ንገረኝ፤ ማለቴ የሚረገዝባቸውና የማይረገዝባቸውን ቀናት ለይተህ" አለና መልስ ከማግኘቱ በፊት ባዶ ወረቀት ከእስክሪፕቶ ጋር አቀረበለት:: "እዚህ ላይ በግራፍ መልክ ብታስቀምጠው ይቀልሃል::"

እንዳለ እስክሪፕቶውን በእሺታ ቢቀበልም የሚነጋገረው ከሐኪም ጋር መሆኑን አሰበና በጉዳዩ ላይ ያለውን እውቀት ለመጀመሪያ ጊዜ ተጠራጠረ:: ይሁን እንጂ አንዴ ማወቁን ስለተናገረ የሚያውቀውን ማሳየት እንዳለበት ተሰማው:: እናም እጆቹ እየተንቀጠቀጡ ከወረቀቱ ግራ ጠርዝ ወደ ቀኝ ቀጥታ መስመር አሰመረ:: በመስመሩ መሃል ላይ አሥራ አራት ቁጥርን፣ መጀመሪያው ጫፍ አንድ ቁጥርን፣ በመጨረሻው ጫፍ ሃያ ስምንትን ጻፈ ቀጥሎም አምስትን፣ አሥራ አንድን፣ አሥራ ሰባትን በየግምት በታቸው ላይ አሰፈረ:: ቀናት መሆናቸው ነው::

"ከአንደኛው እስከ አምስተኛው ቀን ሜኑስትሬሽን ፔሬድ ነው" አለ ዶክተርን በጥርጣሬ እያስተዋለው:: ዶክተር ግን ተቃውሞም ድጋፍም ሳያሳይ እንዲቀጥል ጠበቀው:: "ባነበብኩት መሠረት የማስታውሰውን ያህል ነው" አለና ቀጠለ:: -እንዳለ::

"ከመጀመሪያው ቀን እስከ አሥረኛው ቀን ነፃ ቀናት ሲሆኑ ከአሥራ አንደኛው እስከ አሥራ ሰባተኛው ቀን የሚረገዝባቸው ቀናት ናቸው:: ከአሥራ ስምንተኛው እስከሚቀጥለው የወር አበባ መምጫ ያሉት ቀናት ደግሞ ነፃና የማይረገዝባቸው:: እኛ ስንጠቀም የነበረውም መጥቶ ከሄደ በኋላ /የእርሷ ሶስት ቀን ብቻ ነው የሚቆየው/ በሚቀጥሉት ሰባት ቀናት እና ይመጣል ብለን ከምንጠብቅበት ሰባት ወይንም ስምንት ቀናት ውስጥ በሚኖረው እሑድ ነው:: ይኼ ደግሞ ከመጽሐፉም ይበልጥ አስተማማኝ ይመስለኛል::"

"እሺ?" አለ ዶክተር አሁንም እንዲቀጥል በማድመጡ ተወስኖ::

"በቃ እስከዚህ ድረስ ነው የማውቀው::"

"ሌ ዞትር፣ ማለት ሌሎቹን የጽንስ መከላከያ መንገዶች አታውቃቸውም?"

"ክኒን፣ መርፌ . . ." ብሎ መዘርዘር ሲጀምር አቋረጠው ዶክተር::

"ኖኖ! እነሱን አይደለም:: የተፈጥሮ መከላከያ መንገዶች::"

"ሌላ አላውቅም!" አለ ባጭሩ::

"ያነበብከውን መጽሐፍ ታስታውሳለህ?"

እንዳለ ለማስታወስ ጥቂት አሰላሰለና "'Obstetrics and Gyneachology' መሠለኝ ካልተሳሳትኩ:: ቆይቷል::" አለ ስለ መጽሐፉ ዝርዝር ይዘት እንዳይጠይቀው ለግቶ::

"በሙሉ ነው ያነበብከው?"

እንዳለ መጽሐፉ በሕክምና ቋንቋ የተጻፈ በመሆኑ ስለከበደው በሙሉ ሊያነበው አለመቻሉን እና በወር አበባ ዑደት የቀን አቆጣጠር ላይ የተመሠረተውንም የመቆጣጠሪያ ዘዴ የተረዳው በቻርት የተደገፈ ስለነበር መሆኑን ነገረው::

ዶክተር ሌሎችንም እንዳለ ስለተፈጥሮ የእርግዝና መከላከያ መንገዶች ያለውን እውቀት የሚመዝኑ ጥያቄዎች ካነሳ በኋላ ነው የራሱን ማብራሪያ የጀመረው::

በቅድሚያ "Human Reproduction" ከሚል መጽሐፍ ላይ 'ሴቴ የመራቢያ ዘዴ' በሚል ርዕስ ሥር ስለወር አበባ ዑደት፣ ስለ የሴት ዕንቁላል መፈልፈል፣ ፅንሰት እና የፅንስ እድገት የመጀመሪያ ደረጃዎች የሚያስረዳውን በስዕል የተደገፈ ጽሑፍ ለእንዳለ ይከብዱታል ብሎ ያሰባቸውን የባዮሎጂ ቃላት ከአናታቸው ተቀራራቢ የአማርኛ ፍቺያቸውን በእርሳስ ጽፎ እንዲያነብ ሰጠው::

"በቅድሚያ ሲስተሙን እንድታውቀው ነው::"

'በማንኛዋም ሴት አካል ላይ ከኩላሊት በታች ከሆድ የኋለኛው ግድግዳ ግራና ቀኝ ተያይዘው የሚገኙና 'አቫሪ'የሚባሉ ሁለት የሴቴ እንቁላል መፈልፈያ እጢዎች መኖራቸውን፤ እነርሱም አንዲት ሴት፣ ልጅ ከመወለዷ በፊት ተፀንሳ እያለች ማደግ እንደሚጀምሩና ከተወለደች በኋላ አዲስ የሚፈጠር እንቁላል እንደሌለ:: በእንቁላል እጢዎች አማካኝነት ይዛቸው ከምትፈጠረው በብዙ መቶ ሺ የሚቆጠሩ በየራሳቸው የሚያድጉ እንቁላሎችም አብዛኞቹ ተፈረካክሰው ሲቀሩ የተረፉት ቀስ በቀስ እድገታቸውን እያሟሉ ልጅቷ ለጾታዊ ብስለት ወይንም ኩርድና ዕድሜ ስትደርስ፤ ከአሥራ አንድ እስከ አሥራ አምስት ዓመት ባለው ጊዜ እንቁላሎቹ ከሁለቱ መፈልፈያዎቻቸው በየተራ አንድ በአንድ እየሆኑ መውጣት እንደሚጀምሩ:: ይኼም አንድ በአንድ ከእንቁላል እጢዎች የሚለቀቁበት ሂደት አቭዩሌሽን ማለትም የእንቁላል መፈልፈል ሂደት እንደሚባል:: አንዲት ሴት ከኩርድና ጊዜ እስከ እርጣት ወይንም የእንቁላል መፈልፈል እስከሚቆምበት ሃምሳ ዓመት ዕድሜ ገደማ ድረስ አምስት መቶ ያህል እንቁላሎችን ወደ ማህፀኗ አቪደከት በተሰኘው የማህፀን ቧንቧ በኩል እንደምትለቅ:: የወር አበባ ዑደት የምንለውም በነዚህ ጊዜ አት የሚኖረውን መደበኛና ወርሃዊ የሴቴ መራቢያ ዘዴ ተደጋጋሚ ክንውን መሆኑን:: ይህ ተደጋጋሚ ክንውንም ከእንቁላል ዕጢዎች እና አንጎል ውስጥ ከሚገኘው ፒቱታሪ ግላንድ የተሰኘ ዕጢ በሚመነጩ ሆርሞኖች የተወሰኑ የማነቃቂያ ኬሚካሎች ቁጥጥር የሚካሄድ ስለመሆኑ፤ ወንዴው ዘር ሴቴውን



እንቁላል አጥቅቶ ሲዋሃድ ፅንሰት ተካሄደ እንደሚባል:: ከዚያም ደረጃ በደረጃ ወደ ቀዳማይ ፅንስነት አድጐ ሙሉ ለሙሉ በማህፀን እስኪፀድቅ የሚኖረው የመዳበር ሂደት የመጀመሪያ ደረጃ የፅንስ እድገት እንደሚባል:: በስዕላዊ መግለጫውና በዶክተር ማብራሪያ እየታገዘ አነበበ::

ዶክተር አብደላ እንዳለ ለመረዳት የቸገረውን ሲጠይቀው ባጭሩ ከማብራራት በስተቀር ከእንዳለና ፍቅረኛው መለያየት አኳያ ያለውን ግንኙነት ላለማንሳት እየተጠነቀቀ ነው:: እንዳለም ለመጠየቅ አልቻከለም:: ሲያነብ አልገባ ያሉትን ቃላትና ዐረፍተ ነገሮች ብቻ ነው የሚጠይቀው:: ቀጠለ ንባቡን::

በወር አበባ ዑደት ውስጥ ከአሥራ ሦስት እስከ አሥራ አምስተኛው ቀን በማንኛውም ጊዜ የእንቁላል መፈልፈል ሊካሄድ እንደሚችልና የተፈለፈለው እንቁላልም ለሰላሳ ስድስት ሰዓታት ያህል ለመጠቃት ዝግጁ ሆኖ እንደሚቆይ:: የወንዴው ዘርም ከተረጨ እስከ ሦስት ቀን በሴቷ ማህፀን ውስጥ ሳይሞት ወይንም ለማጥቃት ዝግጁ ሆኖ መቆየት እንደሚችል:: ከዚህ በመነሳትም ከአማካዩ የእንቁላል መፈልፈያ ማለትም አሥራ አራተኛው ቀን፣ ሦስት ወደኋላ እና ሦስት ወደፊት በድምሩ ስድስት ተከታታይ ቀናት በፅንሰት ጊዜ እንደሚታቀፉ በዝርዝር አነበበ::

ስለወር አበባ ዑደት የሚያስረዳው ሠንጠረዥም ካሁን ቀደም ከሚያውቀው ጋር ተመሳሳይ ነው:: የመፀነሻ ጊዜ ተብሎ የተቀመጠው ከአሥራ አንደኛው እስከ አሥራ ሰባተኛው ቀን ያለው ሲሆን ከዚያ በፊትና በኋላ ያሉት ነፃ ቀናት ናቸው::

ምን አስቦ እንደሚያስነብበው ሊገባው ባይችልም በእርሳስ ምልክት አድርጐ የሰጠውን ሁሉ አንብቦ መጨረሱን ገለፀለት::

"ስዕሎቹንና ሠንጠረዦቹንም በደንብ አየሃቸው?"

እንዳለ በአዎንታ ራሱን ነቀነቀ:: ዶክተር መጽሐፉን ተቀበለውና "Essentials of Family Planning" የሚለውን መጽሐፍ አንስቶ The Rhythm of Ovulation Method ከሚለው ምዕራፍ በእርሳስ ምልክት ያደረገባቸውን አንቀጾች እንዲያነብ ሰጠው::

የመጀመሪያው ርዕስ የእንቁላል መፈልፈያ ጊዜን ስለማስላት ነው:: የወር አበባ በትክክል መደበኛ ሆኖ የሚመጣ ከሆነ በአንደኛውና በተከታዩ ፔሬድ መካከል ያለው ልዩነት ከሁለት ወይንም ሦስት ቀናት ሊበልጥ እንደማይችል እና ይህንኑ መሠረት በማድረግም ከረዥም ጊዜ ክትትል በኋላ

የወር አበባ ሂደት መግለጫ ማዘጋጀት እንደሚቻል። የእንቁላል መፈልፈያ ጊዜም የሚቀጥለው የወር አበባ ይመጣል ተብሎ ከሚጠበቅበት አሥራ አራት ቀን ቀደም ተደርጐ እንደሚሰላ ይገልፃል። የእርግዝናና የማይረገዝባቸውን ቀናትም ከመጀመሪያው መጽሐፍ ጋር በተመሳሳይ ቀናት ያስቀምጣል። ሆኖም በዚያ ብቻ የሚያልቅ ሳይሆን ሌሎችንም ከወር አበባ ጋር የተያያዙ የእርግዝናና የማይረገዝባቸው ቀናት መለያ መንገዶች ይገልጻል። የሰውነት ሙቀትን ለክሊኒክ አገልግሎት በሚውል ቴርሞሜትር በመለካትና ከማህፀን የሚወጣውን ንፍጥ መሰል ፈሳሽ መጠንና ባህሪ በመከታተል እንዲሁም በእንቁላል መፈልፈያ ወቅት ተደጋግመው የሚመጡ የህመም ስሜቶችን በማጤን ለምሳሌ በታችኛው የሆድ ክፍል ወይንም በሽንጥ አካባቢ እንደውጋትና ቁርጠት ያሉ ህመሞችን፣ የጡት ህመምና ሌሎችንም በመከታተል እርግዝናን መከላከል እንደሚቻል። . . .

በማብራሪያው ማጠቃለያ ገደማም ከላይ በተዘረዘሩት ከወር አበባ ዑደት ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ ለውጦችንና የጊዜ አቆጣጠር ዘዴን በአንድነት ተቆጣጥረው ከሚጠቀሙት ጤናማ ሴቶች መካከል በዓመት ከአሥራ አምስት እስከ ሃያ አምስት በመቶ የሚደርሱት እርግዝና እንደሚያጋጥማቸውና ለዚህም ምክንያት የሚሆነው የእንቁላል መፈልፈያ ጊዜአቸው ልዩነት ሲኖረውና ምናልባትም ይኸው ጊዜ ከስድስት ቀናት ሊበልጥ ስለሚችል መሆኑን ይገልጻል።

በመቀጠልም ዘዴውን ለመጠቀም የማያስችሉ ችግሮችን ያስረዳል። በዚህም የእንቁላል መፈልፈል ወቅትን በትክክል ለመገመት የማያስችሉ የተለያዩ ምክንያቶች ሊኖሩ እንደሚችሉና ከነዚህም ውስጥ ብዙ ሴቶች በየጊዜው ወይንም አልፎ አልፎ የሚመጣ የእንቁላል መፈልፈል እማይካሄድበት ዑደት ስለሚኖራቸው፣ የሰውነት ሙቀታቸው ለውጥ ሳያሳይ ስለሚቀር እና የሚቀጥ ለው የወር አበባ መምጣት ከሚገባው ጊዜ ቀድሞ ወይንም ዘግይቶ ሊመጣ ስለሚችል እንደሆነ። በወር አበባ ዑደት ውስጥ ዘግይቶ ሊከሰት የሚችለውን የእንቁላል መፈልፈል ከመደበኛው ይልቅ ለማወቅ አለመቻሉ ዘዴውን ውድቅ ሊያደርገው እንደሚችል። በዚህም ምክንያት ያልተጠበቀ እርግዝና ሊከሰት እንደሚችል።. . .

በመጀመሪያውና በመጨረሻው የርባታ ህይወት ጊዜም አንዳንድ ችግሮች ሊከሰቱ እንደሚችሉ፣ በተለይ ወጣት ልጃገረዶችን በተመለከተ ከመጀመሪያው የወር አበባ በኋላ እስከ ሁለት ወይንም ከዚያ በላይ ላለ ጊዜ መደበኛና የተስተካከለ የወር አበባ ዑደት አለመኖር እንደሚያጋጥም። መደበኛ ዑደት ቢመሠረትም እንኳን እንደ ሰከንደሪ አምኖሪያ ማለትም ድኅረ ወር አበባ መቅረት ያሉ ያልተለመዱ ሁኔታዎች በተለይ ከአሥራ ስምንት እስከ ሃያ ሁለት ዓመት ያሉ ልጃገረዶችን እንደሚያጋጥሟቸው ይገልፃል።



ሦስተኛው መጽሐፍ ደግሞ “An A-Z of Gynaecology” የሚል ሲሆን ዶክተር ምልክት አድርጐ የሰጠው የወር አበባ መዛባት ምክንያቶች የሚለውን ርዕስ ነው። ስለ የወር አበባ መቅረት ወይንም አለመኖር የሚያብራራ ነው። ከመጀመሪያው የወር አበባ በፊትና ከእርግዝት በኋላ የሚኖረው የወር አበባ አለመኖርና መቋረጥ ጤናማ ተፈጥሮአዊ ክስተት ነው።

ፕራይመሪ ወይም ቅድመ ወር አበባ መቅረት ከጅምሩ ምንም ዓይነት የወር አበባ ሳይኖር አምኖሪያ መምጣት ከሚገባው ጊዜ ሲተላለፍ ወይንም ሲዘገይ ነው። ይኸውም የመጀመሪያው የወር አበባ መምጣት ያለበት ከአሥር እስከ አሥራ ስድስት ዓመት ዕድሜ ሲሆን ከአሥራ ስድስት አመት በኋላ ሳይጀምር ከቆየ ቅድመ ወር አበባ መቅረት ይባላል።

ሰከንደሪ አምኖሪያ ወይም ድኅረ - ወር አበባ መቅረት ደግሞ ከጤናማ የወር አበባ ጊዜ በኋላ የሚከሰት መዛባት ነው። ይኸውም አንዲት ሴት በመደበኛ ሁኔታ የወር አበባዋ እየመጣ ሳለ በመሃሉ የሚከሰት መቋረጥ ወይንም የወር አበባ አለመኖር ነው።

ለወር አበባ መቅረት ምክንያቶቹ በርካታ ናቸው። ከነዚህም ርግዝና አንዱ ሲሆን ሁልጊዜም የወር አበባ ሲቋረጥ እግምት ውስጥ መግባት የሚገባው ነው። ሌላው የሥነ-ልቦና ጭንቀት ሲሆን በተለይ ማህበራዊም ሆነ ስሜታዊ ጭንቀት ውስጥ የሚገኙ ልጃገረዶች ላይ የወር አበባ መቅረት የተለመደ ነው። ለምሳሌ ከወንድ ጓደኛ ጋር በተያያዘ የፍቅር ችግር፣ ከትምህርት መፈናቀል፣ ከቤተሰብ ያለመስማማት፣ በአደጋ ምክንያት እናት ወይንም አባትን እና ሌሎችንም ማጣት የመሳሰሉ የቤት ውስጥ ችግሮችና ሌሎችም የአዕምሮ መረበሽን የሚያስከትሉ ምክንያቶች። ከዚህም ሌላ እንደ Anorexia nervosa ያሉ ከአዕምሮ ህመም ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ የምግብ ጥላቻና ፈጣን የክብደት መቀነስ ችግሮች የወር አበባ መቅረትን ያስከትላሉ። በተጨማሪም ልዩ ልዩ የትኩሳትና የዕጢ በሽታዎች፣ በደም ውስጥ የብረትን መጠን የሚቀንሱ እንደ ደም ማነስ ያሉ በሽታዎች፣ ያልተስተካከለ አካላዊ እድገት በማህፀን በብልትና በክሮሞዞም ላይ ሲያጋጥም የወር አበባ መቅረት ሊከሰት ይችላል።. . .

አንብቦ ሲጨርስ በተምታታ ስሜትና ግራ በተጋባ የህሊና መሳከር ተዋጠ። ዶክተር አብደላም ያስነበበው ጽሑፍ በእንዳለ ላይ ያመጣውን የስሜት ለውጥ ለመገመት ትክ ብሎ ተመለከተው።

“አሎር!” በማለት በመሃላቸው የሰፈነውን ዝምታ የሰበረው ዶክተር ነው። “ካነበብካቸው ቁም ነገሮች አንፃር ምን ያገናዘብከው ነገር አለ?”

እንዳለ በዶክተር ጥያቄ ይበልጥ ግራ ተጋባ። ምን ያገናዘበው ነገር አለ?

-ለራሱ ያስተጋባው ጥያቄ ነው:: ያነበባቸው እንግዳ ሀሳቦች እርሱ አውቃለሁ ብሎ ሲከተለው ከነበረው ጋር ተጋጬበት:: ተደበላለቁበት::

"ተምታታብኝ ዶክተር! መጻህፍቱ ላይ ባሉበት ሁኔታ ብረዳቸውም ከእኔ ጉዳይ ጋር ያላቸው ግንኙነት በውል ሊጨበጠኝ አልቻለም" አለ ደረት ኪሱን እየዳበሰ::ልምድ ሆኖበት ሲጋራ ሲፈልግ እጁ ወደ ደረት ኪሱ ይሮጣል እንጂ ከጥዋቱም ሲጋራ ይዞ አልመጣም:: ዶክተር ስለገባው ከነፖኬቱ ገፋ አደረገለት::

"ጥሩ!" አለ ዶክተር እንዳለ ሲጋራውን እስኪለኩስ ጠብቆ::

"እኔ እን ብሬፍ፣ ማለት ባጭሩ ላስቀምጥልህ:: ሶሪ ስሟን አልያዝኩትም ገርልህ?" እንዲያስታውሰው በጥያቄ ተመለከተው::

"ዳርምየለሽ" አለ እንዳለ ስሟን ሲጠራ አፉን ቅር እያለው:: ከተለያዩ ለመጀመሪያ ጊዜ አፍ አውጥቶ ስሟን ሲጠራ::

"አዎ! ዳርምየለሽ:: በጥቅምት ወር ገደማ ከባድ የቤተሰብ ችግር ይገጥማትና የመንፈስ መረበሽ ያድርባታል:: ሰው ሸሽታ ብርሃን ፈርታ በጭንቀትና በሀሳብ ተወጥራ መንፈሷ ተዳከሞ አካሏ መንምኖና የህመም ስሜት ተጫጭኗት ለአሥራ አምስት ቀናት ከቤት ሳትወጣ ትሰነብታለች:: አንተ ደግሞ. . ."

"ዶክተር! ይቅርታ አድርግልኝና መቼም ልቦለድ እንደማትተርክልኝ ርግጠኛ ነኝ:: እየነገርከኝ ያለኸው ግን የዳርም የለሽን ታሪክ አይደለም" አለና አቋረጠው::

"ኮማን ሳ? የእርሷንማ ነው የምነግርህ::"

"እንግዲያው የተሳሳትክ ይመስለኛል:: እርሷ እራሷም ታመምኩ እንጂ አሁን የምትለውን ምክንያት አልሰጠችኝም" -እንዳለ ዶክተርን ሳይሆን ሩቂያን በልቡ ታዘባት:: ለዶክተር ይህን የዋሸችለት እርሷ መሆኗን ገምቷል::

"በመጀመሪያ አስጨርሰኝ እንዳለ? ታሪኩን አንተና ሩቂያ ከነገራችሁኝ እያመዛዘንኩ የወሰድኩት እንጂ ልቦለድ ወይንም ራሴ የፈጠርኩት አይደለም:: ይልቁንስ የኔ አስተያየት እና የሙያ ግምት ያለው በመለያያ ምክንያታችሁ ላይ ነው:: በመጀመሪያ አድምጠኝ:: ከዚያ በኋላ ትቃወመኛለህ" አለና ደረቱ ላይ የሸሚዙን ጠርዝ በቀኝ እጁ ጣቶች ላግ ላግ አድርጐ ቀጠለ::

"እርሷ ተጨንቃና ተሰቃይታ በነበረችባቸው በነዚያ አሥራ አምስት ቀናት ውስጥ አንተ ደግሞ የተለመደው ፍቅራችሁ ድንገት ቀዝቅዞ ዛሬ ለነገ እስክትገናኙ የምትነፋፈቁትን ያህል ሳይታሰብ ያራቃትን ምክንያት ለማወቅ በቅናትና በጥርጣሬ ትክን ብለህ ነበር:: ይቅርታ ግን ለዚህ አባባሌ:: ለነገሩ መታመሟን የገለፀችልህ ከመሆኑም በላይ በየቀኑ እየደወልክ ታገኛት ነበር:: ብታምናት ኖሮ ይኼው በቂ ነበር:: ሆኖም በስልክ እንደወትሮው ስለማታናግርህ፣ ቀጠሮ ስለማትቀበልህና ብትቀበልህም ስለምትቀር በዕምነት ታጥሮ የኖረ ልብህን ለቅሬታና ጥርጣሬ አጋለጥከው:: ጠርጣሪ መጠርጠሪያውን አያጣምና ራስህ በከፈትክለት ቀዳዳ አሉባልታ ሽው ሲልህ በደል ተሰምቶህና በእርሷ ላይ የነበረህን እምነት አጥተህ ግንኙነትህን አቋረጥክ::



በኋላም ሩቂያ ምክንያት ሆና እንደገና ስታገኛት አሉባልታውን ሁሉ ንቀህ የሰጠችህን ምክንያት አምነህ ተቀበልካት:: ከሁለት ወራት በኋላ ካንተ ማርገዟን ስትነግርህ የተውከውን እንደገና ቆጥረህ በሁለተኛ በደል መዘገብክባት:: እናም ተለያያችሁ:: አ ሞን አሺ፣ ለኔ እንደሚገባኝ ታሪኩ ባጭሩ ይኸው ነው:: አይደለም?"

"ከመጀመሪያው ምክንያት በስተቀር "

"ተወው ግድ የለም:: በሌላው ከተማመንን የመጀመሪያውን ምክንያት ትክክል ነው አይደለም ሩቂያን ጨምረን እንነጋገርበታለን:: ለጊዜው ግን ቢሆን ብለን እንውሰድና በትክክል ከባድ የቤተሰብ ችግር ገጥሟት በዚያ ሳቢያ የአዕምሮ ጭንቀት ደረሰባት ወይንም ሌላ ድንገተኛ ህመም ታመመች እንበል" ሲል እንዳለ ተቃወመው::

"እንበል ብለን የምንነጋገርበት አይደለም ዶክተር:: ይኼ እኮ መላምት የምንጥልበት ወይንም ገና የሚያጠራጥር፣ ያልተደረገ ነገር ሳይሆን ደርሶ ታይቶ ያለፈ ነገር ነው:: ጥረትህ ሁለታችንን እንደገና ለማቀራረብ ከሆነ ከንቱ ድካም ይሆንብሃል:: ለሙት ነፍስ የመዝራት ያህል:: ይቅርታ አድርግልኝና ብንተወውስ?" አለ ወደ ጀርባው ተለጥጦ::

"በፍጹም አላገኘኸኝም እንዳለ:: ሃሳቤ አንተ እንዳልከው አይደለም መፋቀርም ሆነ መለያየቱ የእናንተ ጉዳይ ነው::"

"ታዲያ ለምን አንተወውም?"

"ሴ ፖ ሞን አብገቨክቲፍ፣ የኔ ሃሳብ እርሱ አይደለም:: ይኸን ያህል ሰዓት መጽሐፍት እያገላበጥኩ ያስነበብኩህ የግንዛቤ ለውጥ እንዲኖርህ እንጂ በሀሰት አግባብቼና ገፋፍቼ ላስታርቅህ ፈልጌ አልነበረም:: በጣም አዝናለሁ! ሳ ንመ ፌ ኒ ፍርዋ ኒ ሾ፣ ታረቃችሁ ተጣላችሁ::" አለና መጻሕፍቱን እቦታቸው መለሰ::

እንዳለ ዶክተርን እንዳስቀየመው ገባው:: ዶክተር አብደላ ግልጽ ቅንና በሳል ምሁር መሆኑን ያውቃል:: ከተገናኙበት ጊዜ ጀምሮ አስቀይሞትም ሆነ ከፉ ባህሪ አይቶበት አያውቅም:: እናም ቢያንስ እስከ መጨረሻው ሳያዳምጠው መቃወም እንዳልነበረበት አመነ::

"ይቅርታ ዶክተር ምን እንደማስብና ምን እንደምልህ ግራ ገብቶኝ ነው:: ሀሳብህን ላዳምጥህ ፈቃደኛ ነኝ: ማለት የፈለግከውን ተናገር" አለ ስሜቱም አከላቱም በይቅርታ ጠያቂነት ተኮማትሮ::

"እሺ!" አለ ዶክተር የተሰማውን ቅሬታ እርግፍ አድርጐ ከመቀመጫው እየተነሳ:: "ቅድም እንዳልኩህ አነሳሴ ለኔ የታየኝን ሀቅ ለኔ የተገለፀልኝን እውነት ላሳይህ እንጂ ታረቅ አትታረቅ ልልህ ወይንም ጥፋቱን ባንተ አድርጌ እርሷን ንጹህ ለማለት አይደለም::"

"በወቅቱ በእርሷ ላይ የደረሰውን ጉዳት እኔ እንደምልህ በቤተሰባዊ ችግር ሳቢያ የመጣ የአዕምሮ ጭንቀት ወይንም አንተ አለችኝ እንደምትለው

ሌላ በሽታ ታምማ አድርገን እንውሰድ:: የማስወረዷን ጉዳይም ለጊዜው እናቆየው:: ይሁንና የሀሊና ወይንም የአካል ጉስቁልና ደረሰባት ብለን እናስብ" አለና ወደ እንዳለ አስተዋለ::

እንዳለ ቀኝ ክንዱን ጠረጴዛው ላይ አሳርፎ አገጩን እንደደገፈ ጭንቅላቱን በመነቅነቅ መቀበሉን አረጋገጠለት::

"የአዕምሮ መረበሽና ሌሎች የውስጥ ህመሞች ደግሞ ለወር አበባ ዑደት መዛባት በዋነኛ ምክንያትነት ከተጠቀሱት መንስኤዎች መሐል እንደሆኑ ካነበብከው ጋር እናገናዝብ" አለና አሁንም ንግግሩን ገታ አድርጐ አስተዋለው:: እንዳለ ኤሌክትሪክ እንደያዘው ሰው መላ ሰውነቱን ነዘረው:: መሃል ጭንቅላቱ ሲቃጠል ይሰማዋል:: ዶክተር ሊለው የፈለገው አስቀድሞ ገባው:: ሆኖም የተባለው የአዕምሮ መረበሽም ሆነ በሽታ 'እንበል' ብለው የተስማሙበት እንጂ በዳርምየለሽ ላይ በትክክል የደረሰ እንዳልነበር ሲያስብ ቀዝቀዝ አለና ራሱን ተቆጣጥሮ ቃል ሳይተነፍስ እንዲቀጥል ጠበቀው::

"ቡተዛባ የወር አበባ ዑደት ደግሞ ትክክለኛውን የእንቁላል መፈልፈያ ወቅት ለማወቅ አስቸጋሪ ነው:: ለእርግዝና ያሰብከው ሳይረገዝበት ሴፍ ፔሬድ ያልከው ደግሞ ሊረገዝበት ይችላል:: በቀጥታ ወደ ዳርምየለሽና አንተ አጋጣሚ ብንገባ በደረሰባት የአዕምሮ ጭንቀትና የሰውነት ጉዳት ሳቢያ ከዚያ ቀደም በጤንነቷ ጊዜ ትክክለኛ ቀኑን ጠብቆ ይካሄድ የነበረው ኦቭዩሌሽን ከወትሮው ቀድሞ ወይንም ዘግይቶ ሊከናወን ይችላል:: ለምሳሌ ከመጸህፍቱ ባነበብነው መሠረት ከአሥራ ሦስተኛው እስከ አሥራ አምስተኛው ቀን ባለው ጊዜ መሃል መካሄድ ሲገባው እስከ አሥራ ስምንተኛውና አሥራ ዘጠነኛው ቀን ቢዘገይ፣ አሥራ ዘጠኝን ለምሳሌ አማካይ አርገን እንውሰድ:: ሦስት ወደፊትና ሦስት ወደ ኋላ ባሉት ቀናት ውስጥ በማንኛውም ጊዜ ወሲባዊ ግንኙነት ቢደረግ የማርገዝ ዕድል ሊያጋጥማት ይችላል:: ይህም ከአሥራ ስድስተኛው እስከ ሃያ ሁለተኛው ቀን ያሉትን ያጠቃልላል:: ይህ ብቻም አይደለም:: ኦቭዩሌሽን የሚካሄድበትም ሆነ ሊረገዝ የሚችልበት ቀን ከመዘግየት ሌላ ሊሰፋም ይችላል:: እንበልና በአሥራ አራተኛው ቀን የተፈለፈለው እንቁላል ራሱ ከተለመደው የሰላሳ ስድስት ሰዓታት ዕድሜ በላይ ሳይሞት እስከ አምስትና ስድስት ቀን የመቆየት ዕድል ሊያጋጥመው ይችላል::"

"እንዴት ሊሆን ይችላል? በሳይንሳዊ ጥናት የተረጋገጠ አይደለም እንዴ?" ብሎ እንዳለ ጠየቀው:: ጥያቄ ብቻ ሳይሆን ክርክርም በሚመስል አነጋገር::

"በነገራችን ላይ ሳይንስ ምንድነው ብለህ ታምናለህ?"

"ሳይንስማ በጥናትና በሙከራ የተረጋገጠ እውነት ነው" አለ ብዙም ሳይጨነቅ::

"ሲ ትሬ ቢያን! በጣም ጥሩ! እኔ ግን ሳይንስ ማለት በጥናትና በሙከራ እያደገ የሚሄድ እውነት ወይንም ባጭር አነጋገር እውነትን መፈለግ



ነው፤ እንጂ በራሱ ያለቀለት እውነት አይደለም ብዬ ነው የማምነው:: ሁልጊዜም አዲስ አዲስ ነገር የሚገኝበት:: የቀደመው በአዲሱ እየተተካ የሚጐለብት:: በመሆኑም የምናነባቸውን ሳይንሳዊ ትንታኔና ገለፃዎች ሁሉ የመጨረሻዎቹ እውነቶች አድርገን ማየት ፍጹም ስህተት ነው:: ያን ያህል ርቀን መሄዱን እንተወውና አሁን ካስነበብኩህ ነጥቦች አንጻር ብቻ እንኳን ብንነጋገር እናንተ ትጠቀሙበት የነበረው የእርግዝና መከላከያ መንገድ የተሟላ አልነበረም:: ይኸውም ከቀን ቆጠራ በስተቀር የሰውነት ሙቀትን መለካት፣ ከማህፀን የሚመነጨውን ፈሳሽ ለውጥ መከታተል፣ ሌሎችንም አብረው የሚከሰቱ ስሜቶች ማገናዘብ እንደነበረባት አንተም ሆንክ ልጅቷ የምታውቁት ነገር የለም:: ይህ ደግሞ የዘዴውን አስተማማኝነት መጽሐፉም ላይ ከተገለፀው በታች ያወርደዋል:: በተሟላ ጥንቃቄ ተጠቅማችሁ ቢሆን ኖሮ እንኳን አስተማማኝነቱ፤ ኩእስከ የሚለውን የመጽሐፉ አገላለጽም በበኩሌ ስለማልቀበለው ዝቅተኛው ማለትም ሰባ አምስት ከመቶ ብቻ ነው ከወሊድ ነፃ የማድረግ ብቃቱ:: ሃያ አምስት ከመቶ የእርግዝና አጋጣሚ አለ ማለት ነው:: ታዲያ ዳርምየለሽን በዚህ ሃያ አምስት ከመቶ መስፈርት ውስጥ እንዳትገባ ፍጹም የሚያደርጋት የተለየ ተፈጥሮ አላት? እ?" አለና ባላሰበው ጥያቄ አፋጠጠው::

"የላትም" አለ እንዳለ ከዚያ ሌላ ማምለጫ ሰበብ ስላጣ::

"በጣም ጥሩ! ይህ እንግዲህ በማንኛዋም ጤነኛ ሴት ላይ ሊደርስ የሚችል ሲሆን የዳርምየለሽ ደግሞ ከዚህም በላይ ሊሆን ይችላል:: ሳይንሱ የወር አበባ መዛባት ችግር ያለባት ሴት ለወሊድ መቆጣጠሪያ በዚህ በናቹራል ሜተድ በተለይም በካሌንደር መጠቀም እንደሌለባት ያሳስባል:: ምክንያቱም አሁን ባነበብናቸውና እኔም በተናገርኳቸው፣ በሌሎችም የሰው ልጅ ዕውቀት ባልደረሰባቸው ምክንያቶች የእርግዝናና የማይረገዝባቸውን ቀናት ለመለየት ስለሚያስቸግር ነው:: ለምሳሌ አንዳንድ ሴቶች የወር አበባ እየታየኝ አረገዝኩ ሲሉ ይሰማሉ:: ሌሎች ደግሞ ሳያረግዙ የወር አበባቸው እስከ አምስትና ስድስት ወር መቅረቱን ይናገራሉ::ምክንያቱ ቢጠና የእያንዳንዳቸው እንደየመልካቸው ሊለያይ ይችላል:: ለዚህም ነው የወር አበባቸው ለሚዛባ ሴቶች በዚህ ዘዴ ጥልቅ አስተያየት ወይንም አንድ ዓይነት ሳይንሳዊ ማብራሪያ መስጠት የማይቻለው::"

"ግንኮ ዶክተር፣ዳርምየለሽ የወር አበባዋ የተስተካከለ ነበር" አለ እንዳለ ራሱን ነፃ ለማድረግ ሳይሆን ያሰበውን ሁሉ በጥያቄ አውጥቶ ከህሊና መከፋፈል ለመዳን::

"ያሰብከው ይገባኛል:: ተከታዩ የወር አበባ ሊመጣ ሲል ባሉት ነፃ ቀናት እንደወጣችሁ ገልፀህልኛል?"

እንዳለ በእምንታ አረጋገጠለት::

"ትሬ ቢያን!" አለና ጥቂት አሰብ አደረገ:: "ህዳር ስድስት፣ ከህዳር

ስድስት በፊት ችግሩ የደረሰባት ማለት ካንተ ጋር ሳትገናኙ የቆያችሁበትን የመጀመሪያ ቀን ታስታውሳለህ? የጥቅምቱን ማለቴ ነው::"

እንዳለ አሰላስለና ትክክለኛ ቀኑን ባያውቅም ጥቅምት አሥራ አምስት ገደማ መሆኑን ገለፀለት::

"ይሁን አካባቢው ከታወቀ ጥቅምት አሥራ እምስት ብለን እንውሰድና ኅዳር ስድስትን ደግሞ በሃያ አንደኛ ቀኗንት እንያዘው የሚቀጥለው የወር አበባ እንዲመጣ የሚያበቃው ተፈጥሮአዊ ቅድመ ዝግጅት በደረሰባት የአዕ ምሮም ሆነ አካላዊ ጉስቁልና እንበለው ተረብሾ ነበር ማለት ነው:: ይህ ከሆነ ደግሞ እናንተ የጠበቃችሁት ተለምዶአዊ አመጣጡ ለመጀመሪያ ጊዜ ቀደም ብሏል ወይንም ቀርቷል ወይንም ተራዝሟል:: በዚሁ ሳቢያ በማርገዟም በተጠበቀው ጊዜ ሊመጣ የሚገባውን የወር አበባ ለማየት ሳትታደል ቀርታለች:: ተግባባን?" አለ ዶክተር ውስጥ ውስጡን ድል እንደመታ የጦር ጀግና ደስታ እያስፈነጠዘው::

"በመጀመሪያው መዛባት አረገዘች ማለትህ ነው?" አለ የዶክተር ማብራሪያ ግልጽ ቢሆንለትም ለምን እንደሚጠይቅ ለራሱም ሳይገባው:: ዶክተር ሊሆን እንደሚችል አረጋገጠለት::

ከዚያ በኋላ ሁለቱም ዝም ዝም ሆኑ:: ዶክተር ከመቀመጫው ተነስቶ እንደቆየ ወደ መስኮቱ ተንጐራደደና ውጪውን መመልከት ያዘ:: ለእንዳለ ጥቂት የማሰቢያ ፋታ ለመስጠት የፈጠረው መላ ነው::

እንደከፋው ሰው ተኮማትረው አንገታቸውን የደፉትን የግቢው ጽጌ ረዳዎች እና ሌሎቹንም አበቦች አስተዋላቸው:: አብዛኞቹ ክረምቱን የወደዱት አይመስሉም:: ጠውልገው፣ ተበጣጥሰው፣ ዳር ዳራቸው ደርቆ መክሰም ጀምረዋል:: ጽዶቹና በአጥሩ ዙሪያ የተጠመጠመው ሀረግ ግን ከዓመት እስከ ዓመት ከእድገት በቀር ጉስቁልና አያሳዩም:: እንዲያውም ክረምት ሲመጣ ውበታቸው ይጨምራል:: ዶክተር አብደላ ክረምትና አበባ ለምን እንደማይዋደዱ ሁልጊዜም ይገርመዋል::

እንዳለ በበኩሉ በዛሬው ቀን ከዶክተር ጋር የተነጋገሩትንና ያሰነበበውን ሁሉ አንድ በአንድ በህሊናው ከልሶ ከእርሱ የበፊት እምነትና ዕውቀት ጋር አገናዘበው:: ባለማወቅ የሠራው ስህተት መኖሩም ገብቶታል:: ሆኖም ሙሉ ለሙሉ ጥፋቱን ለማመን አንድ ነገር ግልጽ ሊሆንለት እንደሚገባ አሰበ:: ዶክተር ለዚህ ሁሉ ችግር ዋነኛ መንስኤ አድርጐ ያሳመነው በዳርምየለሽ ላይ የደረሰ የመንፈስ ጭንቀት ወይንም ሌላ የወር አበባ መዛባት ችግርን ሊያስከትል የሚችል ህመም ዓይነት:: በሰውነቷ ላይ የደረሰውን ለውጥ ቢያስተውልም በውርጃ ምክንያት የመጣ መሆኑን አምኖበት የቆየ ግምት ነው::



"ዶክተር?"

ዶክተር አብደላ አስተውሎቱን ወደ እንዳለ መለሰ::

"በዳርምየለሽ ላይ መጀመሪያ የደረሰው የቤተሰብ ችግር ምንድነው?"

"ዝ ንሴፖ! ዝርዝሩን አልነገረችኝም:: ብቻ በዚያ ሳቢያ ከአሥራ አምስት ቀን በላይ በጣም ተረብሻ እንደነበርና ከዚያም ወዲህ እስካሁን በተደራራቢ ጭንቀትና ችግር መጐሳቆሏን ነው የነገረችኝ:: የቅድሙ ዓይነት መፋጠጥ እንዳይመጣ ለየብቻ ላዘጋጃችሁ ብዬ እንጂኮ ያሰብኩትን ገና አልጨረስኩም:: ቆይ እንዳውም መጣሁ::"

ብዙም ሳይቆይ ሩቂያን ይዞ ተመለሰ:: እንዳለን በሙሉ ዓይኗ ልታየው ባትፈቅድም ሁኔታዋ ከበፊቱ ቀዝቀዝ ብሏል:: ዶክተር እንድትቀመጥ አደረጋት እና በጥቅምት ወር ላይ ዳርም የለሽን ለመንፈስ ጭንቀት የዳረጋትን ምክንያት እንድታስረዳቸው ጠየቃት::

"ምን ይሠራላችኋል? ይኼ የግል ሚስጥሯ ነው" አለች ሩቂያ::

"ስለሚሠራማ ነው የጠየቅኩሽ ሩቂ" ሚስጥርነቱን ተይውና ይልቅ ንገሪን:: አስፈላጊ ከሆነም ሚስጥሩን ለመጠበቅ ቃል እንገባለን:: አለ ዶክተር::

ሩቂያ ፈቃደኛ አልሆነችም:: ዶክተር በልመናም፣ በታላቃዊ ተግሳጽም፣ በማግባባትም ተጠቅሞ ከብዙ ጥረትና ውትወታ በኋላ ቅር እያላት ፈቃደኛ ሆነች::

"አባቷ ናቸው"

"አባቷ ምን ሆኑ?" አለ ዶክተር:: እንዳለ ሁለመናውን ጆሮ አድርጐ መልሷን ጠበቀ::

"ማለቴ ያሳደጓት አባቷ ወላጅ አባቷ አለመሆናቸውን ስለሰማች" አለች ሩቂያ ለጓደኛዋ እንደ አዲስ እያዘነች::

"አይ ሲ!" አለ ዶክተር የዳርምየለሽን ችግር ገምቶ እርሱም ከልቡ በማዘን:: እንዳለም አፉ ባይናገርም ልቡ ባልጠበቀው ምክንያት ደነገጠ::

"ማነው የነገራት?" አለ ዶክተር "ማለቴ እንዴት ሰማች? እስከዚያን ጊዜስ እንዴት ሳታውቅ አደገች?" ጥያቄው የእንዳለም ነበር::

ሩቂያ ዳርምየለሽ በነገረቻት መሠረት እቤት ያሉትን ወላጅ አባቷ አድርጋ እንዳደገችና ምን ያህልም እንደምትወዳቸው፣ በምትወዳቸው የእናቷ አጐት አንደበት "ያ! እንጀራ አባትሽ" የሚለውን ቃል ስትሰማ ምን እንደተሰማትና እንዴት ሆና እቤቷ እንደደረሰች፣ ከዚያም ስትንሰቀሰቅና ከህሊናዋ ስትጣላ እንደሰነበተች፣ ከሰው ተለይታና ሁሉን ነገር ጠልታ

መውጣት፤ ወደ ቤቱ መሮጥ አሰኘው:: ማንንም ማየት ከማንም ጋር ማውራት አይፈልግም::

"የት ትሄድ?" አለው ዶክተር ድንገት ብድግ ብሎ ድምጽ አልባ ሲሰናበተው እርሱም እየተነሳ::

"ልሂድ" አለ እንዳለ 'እባክህ ተወኝ!" በሚል ተማጻኝ ስሜት ተሞልቶ::

"ኖኖ! ይኼማ ነውር ነው:: ምሳ በልተህ መሄድ አለብህ:: ስላስቸገርኩህ ግን ይቅርታ!" አለ ዶክተር ከፊቱ ቀድሞ በሩን እየያዘ::

እንዳለ በመሄዱ ከፀና ዶክተር በቀላሉ ስለማይለቀው ለማሳመን ብዙ መቀበጣጠር ሊኖርበት ነው:: መናገር ደግሞ አልፈለገም::ተመልሶ ተቀመጠ:: ዱዳ የሆነ እስኪመስለው ዝምታ ተጭኖታል::

ዶክተር ስሜቱ ስለገባው ከዚያ ወዲያ ሊያነጋግረው አልሞከረም:: ከምሳ በኋላ ወይንም ሲሸኘው መኪና ውስጥ፣ ካልሆነም ሌላ ጊዜ ያነጋግረዋል:: ሩቂያን ሠራተኛዋ ምሳ እንድታቀርብ እዘዥ ስላላት ወጥታ ሄደች::

ትኩር ብሎ ተመለከተው:: ገጽታው ተለዋውጧል:: ግንባሩ ተኮማትሮ ፊቱ ጭጋግ ለብሷል:: ንዴቱ በቀላሉ ይነበባል::

"ግን በማን?" አለና ራሱን ጠየቀ ዶክተር:: "በማን ነው የተናደደው? በእኔ? በሩቂያ? በዳርምየለሽ? ወይንስ በራሱ? መልሱን መቼም ይሁን መቼ ከራሱ ከእንዳለ አንደበት እና ሁኔታ ያገኘዋል:: ባጠቃላይ ሁኔታው ግን አዘነ::

"ስንቶች ይሆኑ?" አለ በህሊናው ድምጽ ብዛታቸው እየተሰማው::

እያፈቀራት እያፈቀረችው፣ ሳያስበው ሳታስበው ጥልቅ ፍቅር በወለደው ጥርጣሬና ተንኮለኞች በፈተሉት የውሸት ድር ተተብትበው ትንሿን ትልቅ፣ ትልቁን ትንሽ አድርገው በማሰብ ተሳስተው የተለያዩ? ቤታቸው ይቁጠራቸው:: ለምንድን ነው ንጹህ ፍቅር እንቅፋት የማያጣው?

በስስት ስለሚያዝ መሆን አለበት:: የስስቱት ያስጋል:: ስጋት ደግሞ ያባንናል:: ግራ ቀኙን መገላመጥ፣ ዙሪያ ገባውን መጠርጠር፣ ሃያ አራት ሰዓት ነቅቶ መጠበቅ ነው:: ነቅተው ካዳመጡት ጆሮ ለራሱ ይጮሃል:: ልስማ ካሉት የማይሰማ፣ ልይ ካሉ የማይታይ፣ ላስብ ካሉ የማይታሰብ ነገር የለም:: ላፈቀረ ትንሽ ይበቃዋል:: ከምንወደው፣ ከምናፈቅረው ብዙ እንጠብቃለን:: ትንሽ ስናጣ ሁሉን እንዳልነበር እናበላሻለን::

ፍቅር ብሎ ነገር! ራስ ወዳድነት ነው:: ሰው የሚያፈቅረው ራሱን



መሆን አለበት:: ለሌሎች የሚኖረን ፍቅር ከራሳችን ፍቅር ይመነጫል:: የምናፈቅረውም መፈቀርን ስለምንሻ ነው:: ከሰው፣ ከእንስሳት ከእፅዋትና ከአእዋፍ ባጠቃላይ በዙሪያችን ካሉት ቁስአዊና መንፈሳዊ ነገሮች ጥቅምና ፍላጐታችንን ያረካልንን ወይንም ደግሞ ለስሜታችንና ላስተሳሰባችን የቀረበንን፣ የተስማማንን መርጠን የምንወድበትና የምናፈቅርበት ምክንያት ራሳችንን ስለምንወድ መሆን አለበት:: ያፈቀርነውን ከማንም ከምንም ነጥለን የራሳችን ብቻ ማድረግ እንሻለና:: ሌሎች ሲነኩብንም ሆነ ሲመኙብን ከሰውነታችን አካላት አንዱ አለአግባብ ሲነካብን ከሚያመን ከሚያንገበግበንና ከሚቆጨን ባላነሰ ሁኔታ ይሰማናል:: ለዚህም ነው ያፈቀረ ልብ ስጉና ቀናኢ የሚሆነው:: መስላ በታየችው ትንሽ የነገር ፍንካች ሳቢያ ትልቅ ችግር በራሱ ላይ ይጋብዝና በፍቅር ከመደሰት ይልቅ ማዘንና መተከዝ፣ ካፈቀረው ጋር ከመሳቅና ከመስማማት ይልቅ ንዝንዝና ግጭት ያበዛል:: ከዚያ ሲያልፍም ቀለል ሲል ለመለያየት ከበድ ካለም ለራሱም ሆነ ለተፈቃሪው ጥፋት መንስኤ ይሆናል::. ሠራተኛዋ ከፊቱ ስትጀበር የሃሳብ ዋናው ተቋረጠ:: -ዶክተር አብደላ::.

## 57

የአሮጌው ዓመት ጭለማ ክረምት ማለፉን፤ አዲሱ ዘመን አዲስ ብርሃን ይዞ መምጣቱን፤ ሰማይ ማልቀሱን፣ ምድር መራሱን አቁመው፣ አድማስ ፈገግታ ማሳየቱን ሳያስተውሉ፤ ፍጥረት ለምልሞ፣ አበቦች ፈንድተው ውበት መዘመሩን ሳያገናዝቡ መስከረምን አልፈው ጥቅምትን ጀምረዋል። ዳርምየለሽ፣ ወይዘሮ ብዙና መላው ቤተሰቡ።

በእንቁጣጣሽ ሳይከበር እንደዋዛ ማለፍ፣ በመስቀልም መደገም የተጨነቀና ያሰበ አልነበረም። የሁሉም ስጋት በቤተሰቡ ላይ እያንዣበበ ያለው አደጋ ነው። በተለይም የወይዘሮ ብዙ ሳይታሰብ እንደዚያ መታመም ልጆቻቸውን እና ባለቤታቸውን አደናግጧል።

አቶ ባህሩ እንደወትሯቸው ሁሉ የዘመን መለወጫን ከቤተሰባቸው ጋር ለማሳለፍ በግና ዶሮ፣ እንቁላልና ቅቤ ጭነው ነበር የመጡት። ይሁን እንጂ ባለቤታቸውና ዳርምየለሽ አልጋ ይዘው ሲያገኟቸው ክፉኛ ደነገጡ። ወደ ሥራቸው ተመልሰው ለመሄድም አልፈለጉም ነበር። በልጆቻቸው ውትወታና ጉትጎታ፣ ቤተሰቡ በዚያ ችግር ላይ ወድቆ የእርሳቸው ከሥራ መቅረት መታከሚያ እንኳ ጠፍቶ ለበለጠ ጉዳትና ችግር መጋለጥ እንደሚሆን እምነው ከፈቃዳቸው ስምንት ቀን አሳልፈው ሄዱ። ዳርምየለሽ መውለዷን ወይዘሮ ብዙ የታመሙበትን ሚስጥር ሳይሰሙ።

♣ ♣ ♣

ወይዘሮ ብዙ ሆስፒታል ከገቡ አንድ ወር ከሦስት ሳምንት አልፏቸዋል። በተደረገላቸው የሥነ-አዕምሮ ህክምና ክትትል፣ በእውናቸው ከሚያስጮሃቸውና ከሚታዩአቸው አስፈሪ መናፍስት ቀስ በቀስ ቢገላገሉም ውስጥ ውስጡን የሚሰማቸው ጭንቀትና መረበሽ አልለቀቃቸውም። አሁንም ፍርሃት ፍርሃት ድንግጥ ድንግጥ ያደርጋቸዋል። በእንቅልፍ ልባቸው መቃዠቱንም አልተዉም። ራሳቸውን መቆጣጠር እንደጀመሩ ከሚደረግላቸው የመድሃኒት እርዳታ ይበልጥ ዶክተር ገብረወልድ በየጊዜው ደጋግመው የሚለግሷቸው አንድ ምክር ከልባቸው ገብቷል።

ዶክተር ገብረወልድ በሙያው የበሰሉ የሆስፒታሉ ስመጥር



ሳይኪያትሪስት ናቸው። የወይዘሮ ብዙነሽን ጤንነት ለመመለስ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ። በየቀኑ ይጎበኙአቸዋል። እንደ ሀኪም ሳይሆን እንደ አንድ የቅርብ ዘመድ ስለራሳቸው ህይወት፣ ስለቤተሰባቸውና ስለሌሎችም ጉዳዮች የሚሰማቸውን ሁሉ እንዲናገሩ በዘዴ ያግባቡዋቸዋል። ወይዘሮ ብዙም የዶክተሩ ቅርበትና መግባባት የህክምና ዘዴ ሳይሆን በልጃቸው ጓደኛ ወንድም በዶክተር አብደላ ምክንያት አደራቸውን ለመወጣት የሚያደርጉት ውለታ ስለሚመስላቸው ተዝናንተው ነው የሚያነጋግሯቸው። በልባቸው እያመሰገኑ።

የዶክተር ገብረወልድ ትህትና፣ የሚያወሩላቸውን ሁሉ በቁም ነገር ማዳመጥ፣ በወይዘሮ ብዙ መከበርንና ተቀባይነትን አስገኝቶላቸዋል። የየቀኑ ምክራቸውና ማበረታቻቸውም ለወይዘሮ ብዙ ህሊና አዲስ ሰላም አዲስ ርጋታን ይፈጥራላቸዋል። ካጠገባቸው ባይለዩአቸው ይወዳሉ። በጥቅሉም እግዚአብሔ ር ለምህረት ምክንያት አድርጎ የላካቸው ቅዱስ ሰው እንደሆኑ እስከማመን ደርሰዋል። አዕምሮአቸውን ሲረብሽና ሲያስጨንቃቸው የቆየው ሃሳብ ሁሉ ገና የዶክተር መምጫ ሰዓት ሲደርስ ከላያቸው መሸሽ ይጀምራል። ደሞ ሲሄዱለት ተመልሶ ሊመጣባቸው።

ይኸንኑ ችግራቸውን ለዶክተር ገብረወልድ ሲነግሯቸው የሰጧቸው ማሳሰቢያ አለ። "ውስጥ ውስጡን እንድ የሚያስጨንቅምና የደረሰብዎ ችግር እለ ማለት ነው። ይኼን ደግሞ ከእርስዎ በስተቀር ማንም ሊያውቀውና ሊያገኝልዎት አይችልም። ከሕመምዎ ለመዳንና ጤንነትዎ እንዲመለስ ከፈለጉ ይኼንን ችግርዎን አውጥተው ሊነግሩኝ ይገባል። ይደርሳል ብለው የሚሠጉበት እና የሚያስፈራዎት ነገር ካለ፤ ካለበለዚያም ሚስጥር ብለው እንዳይወጣብዎትና እንዳይታወቅብዎት የደበቁት የካሁን ቀደም ችግር፤ በልጅነትዎም ሊሆን ይችላል ካለ፤ ብቻ ማንኛውንም ይሁን የሚያሳስብዎት እና የሚያስጨንቅዎትን ጉዳይ ያውጡትና መፍትሔ እንፈልግለታለን። . . ."

ምን ብለው ያውጡት? እንዲያውም ለዶክተር ገብረወልድ የልባቸውን ካወሩላቸው በኋላ መለስ አድርገው ሲያስቡት ያስገርማቸዋል። ያን ያህል ለምን እንደሚዘከዝኩላቸው አይገባቸውም። የቀራቸው ነገር ቢኖር የዳርምየለሽን ልጅ እንዴት እንደገደሉትና በዳርምየለሽ ጠያቂነት ወጥሮ ሲያስጨንቃቸው የከረመውን የአባቷ ማንነት ሚስጥር ማውጣት ነው። እርሱንም አንዳንዴ ሊያመልጣቸው ይልና መልሰው ይይዙታል። በተለይ ዶክተሩን ሲያዩ 'ተናገሪ! ተናገሪ!' የሚል አንዳች ብርታት ይሰማቸዋል። አንዳንዴ ደግሞ ህንፃው እስኪንቀጠቀጥ ጮኸው ሚስጥራቸውን መለፈፍ ያምራቸዋል። ሁሉም ግን ከህሊናቸው አልፎ በአፋቸው ተሰምቶ አያውቅም። መጨረሻው ራስ ምታትና ቅዠት፣ በቁም መባነንና መደንገጥ፣ ፍርሃትና ጭንቀት ነው። ሽብር ሲያደርጋቸው በእውን የማያስታውሱት አስፈሪና አስደንጋጭ ነገር ሁሉ ይመጣባቸዋል። አሁን አሁን ዶክተር ገብረወልድ በሚያስረዷቸው

መሠረት የችግራቸው ምክንያት እየገባቸው ነው:: አንዳንዴ መንፈሳቸውን ወጥሮ ሊፈነዳ የደረሰ ጭንቀታቸውን ዘርግፈው እሪይ ማለት ይመኛሉ:: ግና እንዴትና ምን ብለው? የዘወትር የጭንቀታቸው ጭንቀት እየሆነ መጣ:: በዚያ ሁኔታ ላይ እንዳሉ ነው አማራጩን ሳያስቡ በዶክተር ገብረወልድ ምክር መሃል ያገኙት::

ዶክተሩ የተለመደ ጉብኝታቸውን በማካሄድ በመሳሪያና በውይይት የወይዘሮ ብዙን ለውጥ ከገመገሙ በኋላ የተለመደ ማበረታቻና ማጽናኛቸውን "እግዜር ይማርህ!" በሚል የተለመደ መሰናበቻቸው ጀመሩ::

"ስሞኑን እንደመከርኩዎ ችግርዎን ለእግዚአብሔር ይንገሩ" እርሱ ይምርዎታል:: ታዲያ እግዚአብሔር ምህረቱን ሲልክ ምክንያት ፈልጎ ነው:: በፈለገው መንገድ ይመጣል:: ሰው ሰውን አያድንም:: የእግዚአብሔር ፈቃድ ካልተጨመረበት እኔ እርስዎን ሳክም አልችልም:: እርሱ ግን እኔን ምክንያት አድርጎ ያድንዎታል:: እና ከልብዎ ይዘው የሚያብሰለስሉትን ሁሉ ይልቀቁት፣ይተንፍሱትና ዳግመኛ ላለመጨነቅ ይርሱት:: ዘወትር እንደማየው ምንም ዓይነት የውስጥም ሆነ የውጪ ደዌ በምርመራ ሊገኝብዎት አልቻለም:: በሽታዎ ያለው ከመንፈስዎ ነው:: ያ ደግሞ ከራስዎ እስካልመጣ ሊታወቅ አይችልም:: እኛ የምናየው ነገር ቢኖር የማይደበቅ የሰውነትዎን መመንመንና ክብደት መቀነስ፣ ፊትዎ ላይ የሚነበበውን የሀዘንና የጭንቀት ስሜት ብቻ ነው:: ጭንቅላትዎ ውስጥ ያለውንማ እግዚአብሔር ነው የሚያውቀው:: እና ጨርሶ እንዲምርዎ ሁሉን አውጥተው ይግለጹት:: ለኔ እማይነገር ከሆነብዎ ደግሞ አይጨነቁ:: ግድ ለኔ አይደለም:: ለማንም ይሁን ብቻ ከእርስዎ ሌላ ለሚያምኑት አንድ ሰው አፍረጥርጠው ይንገሩት:: ይውጣልዎ:: ወይንም ደግሞ ማድረግ እየፈለጉ ፈራ ተባ እያሉ የሰነብት ጉዳይ ካለ ያድርጉትና ይለይለት:: ከፈሩም ርግፍ አድርገው ይተውት:: ዞሮ ዞሮ እርሰዎ ስለተጨነቁ ሳይሆን ሁሉም በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው:: . . ." ብለው በሰፌው ከመከሯ ቸውና ካደፋፈሯቸው በኋላ እንደገና ተሰናብተዋቸው ወጡ::

ይህን መሰሉ የዶክተር ገብረወልድ ምክርና ማደፋፈሪያ የተለመደ ቢሆንም ለወይዘሮ ብዙ አዲስ ስሜት ያስረፀባቸው ሀሳብ በህሊናቸው ጉልቶ ሲመላለስ ሰነበተ::

". . . ለማንም ይሁን ብቻ ከእርስዎ ሌላ ለሚያምኑት አንድ ሰው አፍረጥርጠው ይንገሩት:: ቢችሉ ጭንቀትዎ ለሚመለከተው ሰው:: . . .ሁሉም በእግዚእብሔር ፈቃድ ነው::"

የቤት ጉዳቸውን ለዶክተር ገብረወልድ መዘክዘኩ ከብዷቸው ሲያመነቱ ሳለ ዶክተር የሰጧቸው ፍንጭ በተለይም ፈውሳቸውም በእግዚአብሔር እጅ



መሆኑን ደጋግመው ያረጋገጡላቸው በፈጣሪ ላይ ያላቸውን እምነት አጠ ንክሮላቸዋል::

ከእግዚአብሔር የተሰወረና ከእርሱም በላይ የሚያስፈራ የሚያስጨንቅ እንደሌለ ተሰማቸው:: እንዲያውም ለዚያ ሁሉ ያበቃቸው የእርሱን ታላቅነትና ሃያልነት መርሳታቸው መሆኑ ታያቸው:: ሁሉን ለእርሱ ሰጥተው ቢሆን ኖሮ እንደፈጠረ ያወጣቸው ነበር:: ለልጃቸው ሲሉ ወደ መጽሐፍ ገላጭ ከሄዱበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ያሳለፉትና የደረሰባቸውን ሁሉ አስታወሱ:: ከፈጣሪያቸው መጣላት የጀመሩት 'አንተ ታውቃለህ' ማለት ትተው ወደ ደብተራ የሄዱ ጊዜ ነው:: ከፈጣሪው የተጣላ ምን መላ አለው? ተረስቶና ተቀብሮ የኖረው የዳርምየለሽ አባት ጉዳይ ቢያስጨንቃቸው ከዚያ ወዲህ፤ በጨዋነቷና በጉብዝናዋ ያኮራቻቸው፣ መውለድ እንደሷ ያስናቻቸው ልጃቸው ብታረግዝ ከዚያ ወዲህ፤ በጉድ ላይ ጉድ ተደማምሮ ሁለተኛ ስም ሊያስጣቸው፣ የሰይጣን መንፈስ አድሮባቸው መቅኖ ያሳጣቸውና በሃጢአት ላይ ሃጢአት እየጨማመሩ ከእግዚአብሔር መንገድ የራቁት 'እግዚአብሔር ያውቃል' 'ወላዲት አምላክ ታውቃለች' ማለት ከተውባት ከዚያች ርኩስ ቀን ጀምሮ መሆኑን ያስታውሱና ፈጣሪያቸውን ምህረት በመለመን ያሳርጋሉ::

አንዳንዴ መንገዱን የመሯቸውና ያሳሳቷቸው እማማ ሸዋ መሆናቸውን ካሰቡ በኋላ ሙት ወቃሽ እንዳይሆኑ ይቅርታን ከፈጣሪ ለምነው ጥፋቱን ወደራሳቸው ያጠቃልላሉ::

ደጋግመው የሠሩት ሃጢአት ተሰምቷቸውና ራሳቸውን ወቅሰው ለፀፀታቸው ማካካሻ ለሃጢአታቸው ማስተሰሪያ እግዚአብሔር በሚፈቅደውና በሚያዘው መሠረት ንስህ ገብተው ሊታረቁ ወሰኑ:: ከዚያ በፊት ግን ማድረግ የሚገባቸው ነገር እንዳለ አሰቡ:: ከብዶና ቀፍፎ ቢያስፈራቸውም ከፈጣሪያቸው ከመጣላት እይብስምና ሊጋፈጡት ቆረጡ::

# 58

በሰውም ሆነ በፈጣሪ የአራስ ወጉ ባይደርሳትም፣ እህቶቿና ወንድሟ የበሽተኛን ያህል እንክብካቤ አልነፈጓትም። አባቷ ለዓመት በዓል ያመጡት ሙክት በዓሉን በዓል አድርጐ ቤተሰቡን በደስታ ባይሰበስብም ወገቧን ጠግኖ ሰውነቷን ለማበርታት ጥሩ አጋጣሚ ሆኖላታል። በተለይ ኑንሽና አሰናቀች ድስት በጣዱና ሰሃን ባለቀለቁ ቁጥር ያለፍላጐቷም ቢሆን እያስጨነቁ በላይ በላዩ የሚያጐርሷት ምግብ ሰውነቷ መለሰ ብሎ በቶሎ እንድትጠነክር ረድቷታል። ያልተጠገነና ያልጠነከረ ነገር ቢኖር የህሊናዋ ቁስል ብቻ ነው።

አሁንም ስለአባቷ ታስባለች። አሁንም ስለ እንዳለ ፍቅርና በደል ታስባለች። ጥያቄ፣ ፍቅር፣ ጥላቻ፣ በቀል፣ ይቅርታ። በዚያ ላይ የእናቷ በእርሷ ምክንያት በሽታ ላይ መውደቅ የቱን ይዛ የቱን ረስታ መኖር እንደምትችል ግራ እንዳጋባት ነው።

በተለይ ደግሞ ስሞኑን ሩቂያ እና ምኗንም የማያውቀው ወንድሟ ዶክተር አብደላ የእንዳለን ጉዳይ በማንሳት የሚወተውቷት ከመጠን በላይ ሲረብሻት ነው የሰነበተው። ለሩቂያ ያላት የጓደኝነት ፍቅር፣ ከእርሷም አልፎ ወንድሟ እናቷ ከታመሙ ጊዜ ወዲህ የሠራላቸው ውለታ እርሷንም እቤቷ ድረስ እየተመላለሰ የጠየቃት። ከሁሉም በላይ ደግሞ ለእንዳለ ያላት ጥልቅ ፍቅር፣ አሻፈረኝ ብላ ለመጽናት እንቅፋት ሆነውባት ከራሷ ስትጣላና ስትስማማ ነው የሰነበተችው።

በወንድሟ አሳማኝ ትንታኔና በራሷም ማገናዘቢያ በእንዳለ ላይ የነበራትን ጥላቻ ያነሳችው ሩቂያ፣ ራሱም ዶክተር አብደላ፣ በፀፀት ተንገብግቦና ተቃጥሎ እንዲያማልዱት ለሚማፀናቸው እንዳለ ጉትጉታ ሳይሆን ስለ ንጹህ ፍቅር መቃናት የሰብአዊ ስሜታቸውን ግዴታ ለመወጣት ዳርምየለሽን ወጥረው ይዘዋታል።

እንዳለ ከእርሷ ለመለየት ምክንያት የሆነውን የተሳሳተ አመለካከትና አሁን ስህተቱ ሲገባው የደረሰበትን ፀፀት አንድ በአንድ ዘርዝረው ነግረዋታል። ከእርሷም ሌላ ሴት እርም ብሎ መቅረቱንና እስካሁን ማንንም አለመያዙን አረጋግጠውላታል። የመጀመሪያው ዕለት አሻፈረኝ ብላ ብታመርም እያደር እምቢ ለማለት ያላት ምክንያት በጥያቄና መልስ እየላላና የልቧ ጥልቅ



ፍቅር እየጐላ «ላስብበት» የሚል ተስፋ እንድትሰጣቸው አስገደዳት። እንዲያ መርረውና ከርረው ያለፉት የመከራ ወራት ከልቧ የተከሉት የጥላቻና የበቀል ችግኝ ቀስ እያለ መክሰም ጀመረ።

"አየሽ? ፍቅር ስንክሳር ነው። ፍቅር እየተጠሉም መውደድ ነው። እየተካዱም ማመን ነው። ፍቅር ብድር ወይንም እፀፋ የሚፈልግ ውለታ አይደለም። እንዲያ ከሆነማ በሌላ መፈቀርን መሻት እንጂ ለራስ ሌላውን ማፍቀር አይሆንም። ለፍቅር ተመጣጣኝ ምላሽ ከጠበቅንማ ፍቅር ለሌላ የምንለግሰው ሳይሆን ራስ ወዳድነት ይሆናል። ፍቅር እንደ ውለታ እንካ በእንካ ወይንም ፉክክር አይደለም። ፍቅር አንዳንዴም መበለጥ፣ አንዳንዴም መጐዳት፣ መሞትም ነው። ሰላምና ደስታን እንደሚሰጠን ሁሉ። እውነተኛ ፍቅር ቂም የለውም። እውነተኛ ፍቅር ለራስ ሲሉ ማፍቀር ነው።. . . እና አንቺም በርግጥ ከልብሽ ታፈቅሪው ከነበረ፣ እንኳንስ ሳያውቅ ያደረሰብሽን /ሥራዬ ብሎ የፈጸመብሽ አይመስለኝም/ ለዚያውም ራሱ ጥፋቱ ገብቶት እና ፀፀት ተሰምቶት ይቅርታሽን እየለመነ።. . .የእኛም አመጣጥ እንደገና ተፋቀሩ ልንልሽ ሳይሆን ስህተቱ ከምን እንደመጣ ተረድተሽ ይቅርታ እንድታደርጊለት ብቻ ነው። ሌላው የሁለታችሁ ስምምነትና ውሳኔ ነው።. . ."

እምቢታዋን ያሸነፈ የዶክተር አብደላ ንግግር። ደጋግሞ ህሊናዋን የሚቆረቁር።

"ግን እኮ እኔም ግራ ገብቶኝ ነበር።" ትላለች ለራሷ የእርግዝናዋን ሁኔታ ስታስብ። ሊሆን የሚችልባቸውን መንገዶች ከዶክተር አብደላ እስከተረዳችበት ጊዜ ድረስ እንዴት ልታረግዝ እንደቻለች ለራሷም ያልተፈታ እንቆቅልሽ ሆኖባት ነበር። . . . ታዲያ እንዳለስ በምን መንገድ ሊያውቅ ይችላል? እርሷ ያየችው ከእርሱ በቀር ወንድ አለማወቋን ነው። መተማመናቸውን ተማምናም ነው አለቀኑ የመጣባትን እርግዝና ሳትደብቅ የነገረችው። ቢያምናት ምን ነበረበት?

ከእርሱ ከተለየች ለብቻዋ ስትጋፈጥ የከረመችውንም ችግር ታስታውስና በተለይ በልጇ መሞት ክፉኛ ታዝናለች። ያም ቢሆን ግን ከእንዳለም ጋር ሆና ሊደርስ ይችል ነበር። እርግዝናውን እያግዛት። ልጁንም ቢሆን እግዜርም ገደለው እንደምትጠረጥረው እናቷ፣ ሊያስጥልላት አይችልም። ፍቅራቸው እንደገና ማበብ ከቻለ ሊስመሰላ የምትተካው ነው። ለዚያውም እንደመጀመሪያው ሳይፈለግ ተረግዞ ለችግርና ለመለያየት ምክንያት የሚሆን ሳይሆን በትዳርና በደስታ የታጀበ።

ህሳቧ በቂምና በይቅርታ መሀል እየዋለለ እነ ዶክተር የሰጧትን ከእንዳለ የተላከ ደብዳቤ ደጋግማ ታነበዋለች። "አስብበታለሁ" ያለቻቸው እለት ነበር የሰጧት። የተፃፈው ግን ከዚያ በፊት ነው። የመጀመሪያው ንዴትና እምቢታዋ እስኪረግብ ሆን ብለው እንዳዘገዩት ገብቷታል። ለምን ያህል ጊዜ እንደሆን

ባታውቀውም ደጋግማ ታነበዋለች።

"ከማንም ከምንም በላይ ንጽህት ለሆንሽው ውድ ፍቅሬ፣ 'ፍቅሬ' ስልሽ የአሁኑን ሳይሆን የፊተኞቹን ቅዱስ ቀናት በማሰብ ነውና እንዳትታዘቢኝ። መልሼ ላስበው፣ ልስማው የሚከብደኝን በደል ፈጽሜብሻለሁ። ይቅርታ የማይገባኝ የጨካኞች ሁሉ ጨካኝ እንደሆንኩብሽ ይገባኛል። ጭካኔዬ ግን ካለማወቅ የመጣ የደንቆሮ ጭካኔ መሆኑን ተረድቻለሁ። ዳግመኛ ፍቅርሽን ለመለመን ድፍረት ያንሰኛል። ይቅርታሽን ግን አትንፈጊኝ። እንደቁርባን የሚጥሙ ንጹሃን ከናፍርሽን ሳይሆን እግሮችሽን ለመሳም ፍቀጂልኝ። ከዚያ በላይ አላስቸግርሽም። ይቅርታሽን ብቻ። ብዙ እሚናገር ምላስ የለኝም። ብዙም ለመጻፍ ይቸግረኛል። ቋንቋዬ ፀፀት፣ ብዕሬም እንባ ሆኗል። ከዚህ ደብዳቤ ጋር የላኩልሽ ካሴት ከፊል ስሜቴን ይዟልና ስለእኔ ሳይሆን ስለ ፍቅር አምላክ ብለሽ በትዕግሥት አድምጪልኝ።

የምህረትሽ ለማኝ
እንዳለ ተመስገን"

ከደብዳቤው ጋር የላከላት ካሴት በልዩ ትዕዛዝ ያስቀዳው የቆየ የአለማየሁ እሸቴ ዘፈን ነው። ሙሉ ክሩ አንድ ዘፈን ብቻ ነው።

"አንዱን አካል ፍቅር መለየት ገንጥሎት
አለሁ በግማሹ ደስታን ሀዘን ጥሎት።
ያስታራቂ ያለህ እርዱኝ አባካችሁ
ብቸኛዋን ፍቅሬን አምጡልኝ ይዛችሁ።
በደስታ ሀዘን በሳቅ ፈንታ ለቅሶ
የመረረው ፍቅር በእንባ ተለውሶ።
ማሪኝ ብዬሻለሁ
እሞትብሻለሁ
ሰው ሆኖ ስህተትን የማይሠራ የለም
የአንድ ቀን ጥፋቴን ማሪኝ ተይ ግዴለም።
በደሌን አረሱተሽ ማርኩህ በይኝ ፍቅሬ
በናፍቆት ሰንሰለት እንዳልኖር ታስሬ።
ማሪኝ ብዬሻለሁ
እሞትብሻለሁ።
ቆዳዬ ተገፍፎ ይሁንልሽ ጫማ
ስጋዬም ይደገም ላንቺ ከተስማማ።
አጥንቴን ይብረደው ራቁቴን ልሂድ
ካንቺ የበለጠ አላገኝም ዘመድ።
ማሪኝ ብዬሻለሁ
እሞትብሻለሁ።"



# 59

ተስፋ በተሞላ ስሜታቸው ይሁን በራሱ ተፈጥሮ ዛሬ ብሩህና ደማቅ ቀን ነው። ለእንዳለ፣ ለዶክተር አብደላና ለሩቂያ። ዕሁድ ጥቅምት . . . ቀን . . . እንዳለና ዳርምየለሽ እንደገና የሚገናኙበት ቀን። ካለፈው ዕሁድ ጀምሮ ሁሉም በጉጉትና በናፍቆት፣ ቀናቱን ብቻ ሳይሆን ሰዓታቱንም እንደሩቅ ዘመን እያሰሉ የጠበቁት።

ዶክተርና ሩቂያ ተመላልሰው በመወትወት ዳርምየለሽን ለእንዳለ ይቅርታ እንድታደርግለት ቃል አስገብተዋታል። ቀጠሮአቸውም ለዛሬ ከጧቱ በአራት ሰዓት በዳርምየለሽ ቤት ነው። ዶክተር ከታረቁ በኋላ ለዛሬ ምሽት ደህና ቦታ ራት ሊጋብዛቸው አስቧል። ሩቂያም በበኩሏ የእንኳን ደስ አላችሁ ካርድ ገዝታ ለሁለቱ ፍቅረኞች ለመስጠት በየስማቸው አዘጋጅታለች።

እንዳለ ስሜቱ ተከፋፍሎበት ሲደሰትና ሲጨነቅ ነው የሰነበተው። የዳርምየለሽን ዓይን ለማየትና ይቅርታዋን ተቀብሎ በፀፀት የተቃጠለ ህሊናውን ለማቀዝቀዝ የመጓጓቱን ያህል እንዴት ብሎ ከፊቷ እንደሚቆምና ምን ብሎ እንደሚያናግራት ጨንቆታል። ለነዶክተር የሰጠቻቸው ቃል የምህረት እንጂ 'የፍቅር እንደገና' አለመሆኑን ሲያስብ ስጋትና ጭንቀት ያንግብግበታል።

"ከይቅርታ በኋላስ?"

በሠፈርና በመሥሪያ ቤት እንደሚያውቃቸው ማንኛቸውም ዓይነት ሴቶች ሰላምታ ለመለዋወጥ? ስጋት ላይ የጣለው ጉዳይ ነው።

ዳርምየለሽን ማፍቀር እንጂ በሩቅ እያየ መኖር እንደማይችል ያውቀዋል። ለዚህ ለዚህ ንጽህናዋን ሳይረዳ እንደጠላት፣ ከዳችኝ ብሎ እንደተሳሳተ ቢኖር ይሻለው ነበር።

ለአራት ሰዓት ቀጠሮ አብረው ለመድረስ ቀደም እንዲሉ የተነጋገሩት አሥራ አምስት ደቂቃ ቢሆንም አራዳ ቡና ቤት አጠገብ የተገተረው ገና ሦስት ተኩል ሳይሞላ ነው። ዓይኖቹ በስተግራ እስከ ደጐል አደባባይ ፊት

ለፊት ደግሞ እስከ ቸርችል ጐዳና መታጠፊያ ቢጫ ፔንተ ፍለጋ እንዳንጣጠሩ ናቸው። ሰዓቱ ያለወትሮው ባለበት የሚቆጥር እስኪመስለው አልገፋ ብሎታል። ላይነጋ በመንቃቱ እቤት ተቀምጦ መቁነጥነጡ ሰልችቶት ነው ያለሰዓቱ የወጣው። ጊዜውን የገፋ መስሎት ከመርካቶ በእግሩ መጣ፤ እዚህ ሲደርስ ግን የሚፈልገው ሰዓት ገና ብዙ ይቀረዋል። ጫማውን አስጠረገ። ገና ነው። ቡና ቤት ገብቶ ሻይ ጠጣ። አሁንም ገና ነው። ከአሥራ አምስት ደቂቃ በላይ ይቀረዋል። በትዕግስት እዚያው ተቀምጦ ሊያሳልፈው አልቻለም። ወጥቶ ቆመ። ዓይኖቹ እየተንከራተቱ ልቦናው በሀሳብ መወዝወዙን ተያያዘው። የባጥ የቆጡን ያስባል። ጊዜን በሀሳብ ለመግደል።

ተዘበራርቀው ከመጡበት ሀሳቦች መሀል ሀብቴ ዝናቡና ዕኩይ ሙከራውም ነበሩበት። የዚያን ቅዳሜ ቀን ገጠመኙን አስታወሰ። ቢሳካለት ኖሮ ሊያደርስበት የነበረውን አካላዊና ሥነልቦናዊ ለውጥ አሰበና እንዳአዲስ ዘገነነው። የእሥር ቤት አዳሩንና በማግስቱ ከተናኜ ጋር የነበረውን ቀጠሮም አሰበ።

“እንኳንም ራሴን ያላረክስኩ” አለ የሃሳቡን በሀሳቡ እያደነቀ። ለቀጠሮው መፍረስ ምክንያት የሆነው በሀብቴ ዝናቡ ላይ ባደረሰው ጉዳት መታሠሩ እንደነበር አሰበና “ይኼ ውሻ ጠሱን እንዳመጣ ወሰዳት” ብሎ ሳቀ። በልቡ።

በዳርምየለሽ ጉዳይ የሀብቴን አስተያየት ገና ከጅምሩ ባይወደውም ለመለያየታቸው ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደነበረው የገባው ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ነው። ሁሉን አገናዝቦታል። እንዲተዋት በቀጥታ በመወትወት ሳይሆን እንከኗ እንዲታየው መንገድ በመምራት እና ጥርጣሬን አስጀምሮት በመቅረት የረቀቀ ተንኮሉን እንዴት እንደሸረበበት ገብቶታል።

አስቀድሞ ልቡ በጥርጣሬ ባይሞላ ኖሮ ያን ያህል ጨክኖ ዳርምየለሽን ለችግር የሚያጋልጥ ውሳኔ ላይ አይደርስም ነበር። ከኔ ነው ብሎ ባያምን እንኳን ጽንሱን እንድታስወግድ ከረዳት በኋላ በማትወቅሰው ሁኔታ ሊሰናበታት ይችል ነበር።

ስለሀብቴ ዝናቡ ሲያስብ ከሁሉም በላይ የሚገርመው ነገር ቢኖር ያን ያህል ለምን ሲፈታተነው እንደኖረ ነው። በበኩሉ እንኳንስ ያን ያህል ተንኮል ለመሥራት የሚያነሳሳ፣ ቅር ሊያሰኝ የሚችል የአንድ ቀን ጥፋት እንኳን አድርሶበት አያውቅም። በጓደኝነት መልክ ቀርቦት ሲርቀው አልርቅ እያለ ግድ ተጣበቀውና በጣፈጠ ፍቅሩ ላይ መርዝ ነስንሰበት። ያም አልበቃህ ብሎት ጉምዛዛውን የብቸኝነት ህይወቱን ጨርሶ ለማምረር ከሸሸበት ተከትሎ ለህሊናው የቀፈፈ ጉዳት ሊያደርስበት ሞከረ። አልተሳካለትም እንጂ።



«ከሀጢአቱ ነፃ ለመሆን የከፈለው መስዋዕትነት» አለ እንዴት አድርጐ እንደጣለውና የገዛ ሠንጢውን እንደሰካበት እያስታወሰ። የዚያን ዕለቱን የሀብቴ ዝናቡ ጉዳት ከገዛ ሃጢአቱ ነፃ ለመውጣት የከፈለው ዋጋ አድርጐ ነው የሚመለከተው። ለእርሱና ለዳርምየለሽ እንደገና መገናኘት ምክንያት ሆኗልና። ከተናኜ ጋር ወጥቶ የዳርም የለሽን ንጹህ ፍቅር ከማርከስ ጠብቆታል። ባይሞከረው አይወጋውም፤ ባይወጋው አይታሰርም፤ ባይታሰር ቀጠሮው አይፈርስም፤ ቀጠሮው ባይፈርስ ወደ ዶክተር ቤት አይሄድም፤ ባይሄድ ከሩቂያ ጋር አይገናኝም፤ አይጋጭም። ያ ባይሆን ደግሞ የመለያየታቸውን ሚስጥር ተረድቶ ዛሬ በጉጉት ልቡ ተሰቅሎ ለሚጠብቀው እርቅ አይበቃም ነበር።

ሀብቴ ዝናቡ ለተንኮል ያዘጋጀው መስናክል ራሱን አደናቅፎት ለእነርሱ ያልታሰበ የመገናኛ ድልድይ ፈጠረላቸው። የተጐዳ ዕለት ሆስፒታል ገብቶ ጥቂት ቀናት ቢቆይም ከዚያ ወጥቶ የት እንደደረሰ አይታወቅም። በመሥሪያ ቤትም ሆነ በሠፈር እዚህ ቦታ አየሁት ወይንም እንዲህ ሆኗል የሚል የለም። የሚታወቅ ነገር ቢኖር ከሆስፒታል ሳይወጣ ጉዳዩን ለያዘው መርማሪ ፖሊስ እንዳለን በተጠያቂነት እንደማይፈልገው ቃል መስጠቱና ከሆስፒታል እንደወጣ መጥፋቱ ብቻ ነው። ምናልባትም እንዳለን ሊበቀለው ፈልጐ እንዳደፈጠ ወይንም ድርጊቱ አሳፍሮት ወደ ክፍለ ሀገር እንደኮበለለ የተለያዩ የግምት ወሬዎች ይናፈሳሉ።

ልዩ ልዩ ሞዴልና ስም ያላቸው በርካታ መኪኖች በዓይኖቹ ሥር እንደሚያልፉት ሁሉ፣ ልዩ ልዩ ይዘትና ትዝታ ያላቸው በርካታ ሀሳቦች በህሊናው ሥር እየተመላለሱ ቀሪ ጊዜውን አጫረሱትና ጊዜው ደርሶ የዶክተር አብደላ ፔንተ ብቅ ስትል ሁለመናው አንድ ሆኖ ስዓቱን አስተዋላት። ለሩብ ጉዳይ አንድ ደቂቃ ቀርቷታል።

# 60

የዛሬ ሰንት ዓመት መሆኑ ነው።

ቀኛዝማች ከፍያለው የእህታቸው የወይዘሮ ጥልፏን የመጀመሪያ ልጅ ተሾመ ማመጫን ከገጠር ያመጡና ከልጆቻቸው ጋር እያስተማሩ ያሳድጉታል። እርሱም በትምህርቱ ጉብዞ ሁለተኛ ደረጃ እንደደረሰ ከአሥረኛ ክፍል አቋርጦ ራሱን ለመቻል የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስተማሪነት ይቀጠራል። እያስተማረ አንድ ሦስት ዓመት እንደሠራም፣ ራሱን ለመቻል ያለውን ፍላጎት የተረዱት ቀኛዝማች በቅድስት ማርያም ወረድ ብሎ ከነበራቸው ሠፊ ይዞታ መሃል ቤት ያልነበረበትን ከአንድ ሺህ ካሬ ሜትር በላይ ቦታ ሰጡትና የእርሳቸው ድጐማ ታክሎበት የራሱን ቤት ሠርቶ በሥራቸው ከመተዳደር ወጣ። ሥራ እንደጀመረ ያወቃትንና በኋላም በፍቅር ልቡ ጥፍት ያለላትን ወይዘሪት ለማግባት የቤት ዕቃውን እና አንዳንድ ቅድመ ሁኔታዎች በማዘጋጀት ላይ ሳለ እርሱንና ታናሽ እህቱን ያለ አባት ተቸግረው ያሳደጉአቸው እናቱ ሞቱ። ከእርሱ የቀረበ ረዳትና አይዞሽ ባይ የሌላት እህቱን ወደ አዲስ አበባ ለማምጣት ተገደደ። በእናቱ ሀዘን ምክንያትም የጋብቻ እቅዱን ለአንድ ዓመት አዘግይቶ ከእህቱ ጋር መኖሩን ተያያዘው።

ያን ጊዜ ብዙነሽ ማመጫ አማርኛዋና ዘርገፍገፍ ያለው አለባበሷ በከተሜ ዓይን ገራገር ከሚያስመስላት በቀር ላያት የምታጓጓ በፍቅር የምትወጋ የአሥራ ሰምንት ዓመት ልጃገረድ ነበረች። ሊፈነዳ እንደተቃረበ የአበባ እንቡጥ ጥብቅብቅ ብላ ያማረች። ገና ከገጠር የመጣች መሆኗን ቢያውቁም እንኳ ሰንትና ሰንት ሰለጠንን ባይ ጐረምሶች ያስቸግሯት ነበር። አንድ አፍታ ለገበያም ይሁን ቀኛዝማች ከፍ ያለው ቤት ለመሄድ ወጣ ካለች በአድናቆት ፈዝዞ የሚያስተውላት፣ አልፋው ስትሄድ እየዞረ የሚመለከታት ወይንም በርቀት ዓይኖቹን ጣል አድርጐ የሚከተላት፣ የዓይኑ ሽፋል እስኪረግፍ የሚጠቅሳት፣ የማንባሩ ሽብሽብ እርጅና እስኪመስልበት ቅንድቡን የሚሰቅልላት፣ ሌላውም ሌላውም የእርምጃዋን ያህል ቁጥሩ በርካታ ነው። እንዳላየ ተከላትራና እንገቷን ደፍታ እርሷም በኩራት ትሰልላቸዋለች።አዘውትረው ከሚከታተሏትና ከተላካ ለትዳር ካልሆነም ለፍቅር ከሚመኟት መሀል ዳለቻማ ሳሪያን ኮት ከቬል ሱሪ ጋር የሚለብሰው ሪዛሙና ዓይነ ውሃው ሞኛሞኝ የሚመስለው ባህሩ ፍሰሀ አንዱ ነበር። ከልብሱ በስተቀር ነገረ ሥራው ሁሉ የእርሷ ቢጤ



ባላገር ስለሚመስላት እንኳንስ ፊት ልትሰጠው ለመከራውም ያበሽቃት ነበር። በኋላ ላይ ስማይ መሬቱ ሲደፋባት እና አማራጭ ሲጠፋባት ከነጉዷ ተቀብሎ ከማንም ይልቅ አይዞሽ ሊላት።

በታላቅ ወንድሟ ማበድ ምክንያት በደረሰባት የመተዳደሪያ ዕጦትና በማህፀኗ በያዘችው እኩይ ፅንስ መዳበር የተነሳ ልትወጣው የማትችለው ችግር ወጥሮ ሲይዛት፣ ነብሳቸውን ይማርና የቀኛዝማች ሚስት ወይዘሮ አይቼሽ ዘንድ ሄዳ በሴት ልጆቻቸው እየተማፀነች አለቀሰችባቸው። እርሳቸውም አባብለውና አጽናንተው እህልና ገንዘብ ከደጎሟት በኋላ ጠላ እየሸጠች ለዘለቄታው ራሷን እንድትረዳ አማከሯት። አቋቋሟትም።

ያን ጊዜ ነው እንግዲህ ጣሳ ሰው አይመርጥምና ባህሩ ፍሰሃ በገዛ ቤቷ ስተት ማለት የጀመረው። ጠላ የለም ወይንም አለቀ ካልተባለ በስተቀር በቀን ሁለት ሦስት ጊዜ ተመላልሶ ይመጣል። አንዳንዴ ሂሳብ ሲከፍል ከጠጣበት በላይ የሚሆን መልስ ያለፍላጐቷ ትቶላት ይሄዳል። አራት ኪሎ ነዳጅ ማደያ አብረውት የሚሠሩ ጓደኞቹንና ሌሎችንም ሰዎች ሰብስቦ እያመጣ በመጋበዝ ገበያዋን አሟሟቀላት። ከቀን ወደ ቀን ፊቷ እየተፈታለትና እየተግባቡ መጡ። ጠላ በሌለበትም ቀን ጐራ ብሎ አጫውቷትና ሰላም ብሏት መሄድ ጀመረ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ታዲያ እርሷ የምትሰጋውና የምትፈራው ጉዳይ ነበር። የፍቅርም ሆነ የጋብቻ ጥያቄ እንዳያነሳባት። የፈራችው አልቀረም፤ አንድ ቀን ጠላ በሌለበት መጣና እንደወትሮ ካጫወታት በኋላ እንደሚያፈቅራት አነሳባት። ሲያፈቅራትም ለዕለት የሥጋ ፍላጐት ሳይሆን ለዘላቂ የትዳር ዓላማና ለቁም ነገር መሆኑን ገለፀላት። እርሷ ግን ጥያቄውን ልታሟላ የማትችልበት ምክንያት እንዳላት ገልፃ ፊቃዷን ነፈገችው። ባንድ ቀን አልተረታም። ደጋግሞ ወተወታት።

እርሷም ልታሳርፈው ብላ ከሌላ ያረገዘችውና አባት የሌለው የሦስት ወር ቅሪት እንዳላት ፍርጥ አድርጋ ነገረችው። የሚያግደው አልሆነም እንጂ። እሺ ካለችው ለልጇም አባት ሆኖ እንደሚያገባት በመሃላ አረጋገጠላት። ማተቧን ይዞ ማተቡን ይዛ ላይከዳት ላትከዳው ተማማሉ። ፊርማ የለ ሽማግሌ፤ በማግሥቱ የሸቦ አልጋውን ከልብሱ ሳጥኑ ጋር ተሸክሞ ገባ። ባልና ሚስት።

የብዙነሽ ሆድ እየገፋ ሲሄድ 'ጉድ' ያለ ሠፈርተኛም ሆነ የሩቅ ሰው አልነበረም። ከጋብቻቸው በፊት ከእርሱው እርግዛ እንደነበርና እንደተጠቃለሉ ተናፈሰ እንጂ። ሁለቱም ያለ ቅሬታ አውርተው የሚያስወሩት ይኼ ንኑ ነበር። ከእነርሱ በስተቀር ብዙነሽ ከባህሩ ያለማርገዟን በቀጥታ የሚያውቅ ቢኖር ወይዘሮ አይቼሽ ብቻ ነበሩ። ከዚያ ካለፈ ከባልና ሚስት የሚደብቅ ነገር የለምና ቀኛዝማች ከፍ ያለው። ይልቁንም የቅርብ የሩቁ ተመልካች

ጉም ጉምታና 'ወይ ጉድ!'ያሰኝ የነበረው ወሬ፣ ምስኪኑ ቤንዚል ቀጂ ያበደው ወንድሟን ቤትና ንብረት ለመውረስ ምንም ተቀናቃኝ የሌላት ልጅ አግብቶ ኩተከራያት ኩሽና ታህል ቤት ወደ ትልቅና የተደራጀ፣ በአጥር የኮራ ቤት መግባት ነበር፡፡ 'የእንትንም ገድ አለው' ተባለለት፡፡

ለማትፈልገው ጋብቻ ያስገደዳትን ሚስጥርና የሚስጥሩን ተዋናይ የምታውቀው ግን እርሷ ብቻ ነበረች፡፡ ባህሩ፣ወይዘሮ አይቼሽና ቀኛዝማችም ቢሆኑ ከሌላ ማርገዟን እንጂ ያ ሌላ ሰው ማን እንደሆነ አያውቁም፡፡ እርሷና ፈጣሪ ብቻ፡፡

"እኔና ፈጣሪ ብቻ! ሌላ ማንም የሚያውቅ የለም፡፡"

"ምኑን እማዬ?" አለች ዳርምየለሽ በዝምታ ተውጠው የቆዩት እናቷ ድንገት ባወጧቸው ቃላት ግራ ተጋብታ፡፡

"ጉዴን ነዋ ልጄ! ሚስጥሬን" አሉ አልጋቸው ላይ ግድግዳውን በመደገፍ ጉልበታቸውን ሰብሰብ አድርገው እየተቀመጡ፡፡ ዳርም የለሽ ውስጧ እየታመሰ በጉጉት ጠበቀቻቸው፡፡

"አሁን ታዲያ ሳስበው ከሰው እንጂ ከፈጣሪ እንዳልደበቅኩት ገባኝ፡፡ ደግምም እኮ እርሱው ቢያዝብኝ እንጂ ፈልጌ ወይንም የፈጣሪን መንገድ ስቼ አይደለም፡፡ ከእርሱ የሚሰወር ምን አለ፡፡ታዲያ በምድር የደበቅኩትን በሰማይ ሳልዘልቅበት ከንቱ መድከሜ ለምንድነው?ቆሜ ያልተመቸኝን ነብሴስ ለምን ትንገላታ? 'በምድር ያልዘሩትን በሰማይ አያጭዱትም' ይላሉ መምሬ ክፍሉ፡፡ ያለ አባትሽ 'የሱ ልጅ ነሽ' ብዬ እንዳታለልኩሽ ህይወቴ ብታልፍ የሰማይ ቤት መንገዴን መዝጋት ይሆናል፡፡ እግዜሩም ይቅር አይለኝ፡፡ ንስሃዬን ሳላወርድ በሃጢአት እንደታጠብኩ ቢጠራኝ ምን አይቶ ይምረኛል? አንቺን ዛሬ እንድትመጪ የፈለግሁሽም ለዚሁ ነው" አሉና እንደገና በሃሳብ ሰመጡ፡፡ እንዴት ብለው ይንገሯት?

ዳርምየለሽ ሁለት ልብ ሆነች፡፡ አንድ ልቧ የአባቷን ማንነት አውቆ መንፈሷን ከረበሸው የህሊና ጥያቄ ለመገላገል ጓጓ፡፡ ሌላኛው ደግሞ እስካሁን ደብቀው ያኖሩት አባቷ ምን እንከን ቢኖረው ይሆን ብላ ሰጋች፡፡

"ለዐይንና ለጆሮ የሚከብድ አንዳች ዓይነት የተፈጥሮ ጉድለት ይኖርበት ይሆን? ወይንስ ይቅርታ የማይገባውና አስቃቂ በደል ፈጽሞባት? ወይንስ ከእኔ አላረገዝሽም ብሎ ክዷት?"

ወዲያው በእርሷና በእንዳለ መሃል የደረሰው ሁሉ ላንዳፍታ ታወሳት፡፡ እነርሱ ግን እንደ እናቷና አባቷ የእርሷን ዕድሜ ያህል አልተጨካከኑም፡፡ ስህተታቸው ገብቷቸው ሊታረቁ ነው፡፡

"ይኼኔ እቤት መጥተው እየጠበቁኝ ነው" ብላ አሰበችና ሰዓቷን



ተመለከተች፡፡ ስድስት ሰዓት ከሰባት ደቂቃ ያሳያል፡፡ ቀጠሮአቸው መፍረሱ ተሰማት፡፡ እንዳሰበችው ቶሎ መመለስ አልቻለችም፡፡ ከእንግዲህ ምን ያህል ሰዓት መቆየት እንደሚኖርባት አታውቅም፡፡

"ብቻ አንዱን ሀሳቤን ቡተገላገልኩ እንጂ የእነርሱ ሌላም ቀን ሊሆን ይችላል" አለችና በልቧ ተዝናንታ ከእናቷ ጋር ለመዋል ወሰነች፡፡

"ታዲያ ንገሪኛ እማዬ?" አለች ጭንቀትን የሚያስነብቡት የእናቷ ዓይኖች ትክ ብለው ሲመለከቷት እርሷም ጭንቅ እያላት፡፡

"ልነግርሽማ ነው ልጄ! ምን ብዬ እንደምነግርሽ ከበደኝ እንጂ"

"እንደፈለግሽ አርገሽ ብትነግሪኝ ግድ የለኝም፡፡ ምንም አትጨነቂ፡፡ ለልጅሽ እንጂ የምትነግሪኝ እኔ ባዕድ አይደለሁ፡፡ ለዛውም ስለ ራሴ፡፡ ለእናት ከልጇ በላይ የምትደፍረውና የምትዝናናበት የለም" አለች ጭንቀቷን ዋጥ አድርጋ በማግባባት፡፡

"እሱስ ውነትሽን ነው ልጄ፣ ነገሩ ለመድፈርም ለማውራትም የሚመች አይደለም እንጂ፡፡"

እናትና ልጅ ተፋጥጠው ዝም እንዳሉ በርካታ ስኮንዶች በደቂቃ እየተጠቃለሉ አለፉ፡፡

"አንድ ቀን" አሉና ዝምታቸውን ሰብረው በሚያልፉ ሰከንዶች ላይ ቃላትን ማሳረፍ ጀመሩ፡፡ ዳርም የለሽ በዝምታዋ እንደፀናች ጠበቀቻቸው፡፡

"አንድ ቀን፣ ገና እንደአበደ ስምንተኛው ቀን ገደማ ነው፡፡ ውጪ ውሎ ለዓይን ያዝ ሲያደርግ መጣ፡፡ መቼም የጀመረው ሰሞን የቤቱ አልቀረ የየቡና ቤቱን ሰልክ እያነሳ ሲፈጠፍጥ ሲደበድቡት፣ ሲታሰር እንደገና ማበዱን አውቀው ሲለቁት፡፡ እኔም እየተከተልኩ ሳለቅስና ስለምን መከራዬን ነበር ያየሁት፡፡ በኋላ ላይ ሁሉም አውቀው ገና ሲያዩት ስልካቸውን መጠበቅና ማስጣል እስኪጀምሩ፡፡"

"ማን ነው እሱ?" አለች ዳርምየለሽ ግራ ገብቷት፡፡

"አጉትሽ ነዋ ይኸው ተሾመ"

ዳርምየለሽ እናቷ በጤናቸው መሆኑን ተጠራጠረች፡፡ አባቷን ሊነግሯት ጀምረው ስለ በሽተኛው አጉቷ ማውራታቸው ከህመማቸው የመጣ መዘባረቅ ስለመሰላት ልታርማቸው አልሞከረችም፡፡ ይልቁንም ከልቧ እያዘነችላቸው ጆሮዋን ሰጠቻቸው፡፡

"እኔም ታዲያ ከአራት ኪሎ አካባቢ ርቆ እንደማይሄድና ከሰልክ በስተቀር ሰውን እንደማይተናኮል ለመድኩትና 'እንዲህ ሆነልሽ' ካላሉኝ ተከትዬው መዞሩን የተውኩበት ሰሞን ነበር፡፡ እና ሲመጣ ትንሽ ደግሞ አጠጥተውት ነው መሰለኝ ይለፈልፋል፡፡"

"ምስራቅ . . . ምስራቂና" እያለ መጣ፡፡ በሩን ከፊት ሳደርግለት

‘ምስራቂና’ አለና ተጠመጠመብኝ”:: ‘ብዙነሽ ነኝ’ እያልኩ በማልቀስ ላስለቅቀው ታገልኩኝ:: ላመልጠው አልቻልኩም:: እንቆ ያዘኝ” አሉና እንባቸው ተንቆርዞ ዝም አሉ::

“ከዛስ?” አለች ምን ማለታቸው እንደሆነ ለመገመት ከብዷት::

“አነቀኝ አልኩሽኮ! ከዚያማ አንቺ ተፈጠርሽ” አሉ ፍርጥ አድርገው::

“ምን?” አለች በጥፊ እንደተመታ ሰው ጆሮ ግንዷ እየነደደ:: “ምን?. . . ምን?. . . ምን?” ደግሞ ደጋግሞ ጥያቄዋ ለራሷ ደወለባት:: - በህሊናዋ::

“እና አባቴ ማን ነው ልትይኝ ነው?”

“ነገርኩሽ እኮ! ይኸው ነበር ሃያ ሦስት ዓመት ከሆዴ ቀብሬው የኖርኩት የቤት ጉድ” አሉና በረዥሙ ተነፈሱ:: የዛሬን ብቻ ሳይሆን ሃያ ሦስት ዓመት የሳቡትን ሁሉ ያስወጡ ይመስል:: አሁን የቀራቸው ለመምሬ ክፍሉ አንድ በአንድ ዘክዝከው ንስሃ መግባት ነው:: ነብሱን በእጃቸው ስላሳለፉት ህፃን ሳይቀር ሃጢአታቸውን ከተናዘዙ በኋላ ይቅር ቢላቸው ወላዲት አምላክ፣ ጭንቅ አማላጅቷን ይዘው ይማፀኑታል:: -ፈጣሪያቸውን::

ዳርምየለሽ የምታየውም የምታስበውም የሰማችውም ተደበላለቀባት:: እንደ ቅዠት ሁሉ ተጠራጠረችው:: እውን መሆኑን ልቧ ሲነግራት የእናቷን ጤንነት ተጠራጠረች::

“ሃሎ?” እያለ ከፊቷ ድቅን አለ:: ሊፋቅ፣ ሊሠረዝ፣ ሊታረም የማይችል፤ መሆን ሳይኖርበት የሆነ ነገር:: በሀይማኖትና በባህል የተወገዘ:: ፀያፍነቱ ለአካባቢ ለቤተሰብና ለራስ የሚዘገንን እርኩስ አጋጣሚ::



# 61

የክፍሉ በር በቀስታ ከውጭ ሲቆረቆር ገና አልተረጋጋችም ነበር:: ቅስሟ ስብር ብሎ በጉኗ ተራመደችና ከፈተችው::

“ሀኪም ያለ መሰሉኝ? አለ ዶክተር አብደላ ክራቫቱን በቀኝ እጁ እያፍተለተለ:: መልስ አልሰጠችውም:: ዓይኖቿ ከእርሱ ጀርባ አልፈዋል:: ከሩቂያ አጠገብ::

ስታየው ከውስጧ አንዳች ነገር የተቀሰቀሰ መሰላት:: ከልቧ የተቀሰቀሰው ያ አንዳች ስሜት ከደሟ ጋር ተሠራጭቶ መላ አካሏን ሲወረው ተሰማት:: እምትለውም እምታደርገውም ጠፍቷት ዓይኗን እንደ ተከለችበት ቆማ ቀረች::

“ስትቀሪ ጊዜ እዚሁ መጣን”አለ ዶክተር ወደ ጐን ገለል እያለ:: ሁኔታዋ አስገቶታል:: “እሷም እንደ ሩቂያ ስድብ ልታወርድበት ይሆን?” አለ በልቡ::

እንዳለ ከእርሷ ተቃራኒውን የኮሪደሩ ግድግዳ እንደተደገፈ ከጭንቀቱ ጋር ቆሞአል:: ሲመጣ እንደነበረው እግሯ ላይ መውደቅ አሰኘው:: ምህረት በሚሻው ስሜቱ:: አፍቃሪ ልቡ ደግሞ አንገቷ ላይ ተጠምጥሞ ናፍቆቱን ሊወጣ ተመኘ:: ለሁሉም ግን ድፍረት አልነበረውም:: ሁኔታዋ የፍቅር ይሁን የጥላቻ ሊገባው አልቻለምና::

ዳርምየለሽ እንደ ሀውልት ፀቆመችበት ዓይኖቿ ዕንባ ማፍለቅ ጀመሩ:: ከዕንባዋ ጋር በገጿ ላይ መነበብ የጀመረው የመረታት ስሜት እንዳለን እንዲንቀሳቀስ ብርታት ሰጠው:: የእርሱም ዓይኖች በዕንባ እየተሞሉ:: ከበሩ ወጣ ብላ እጆቿን ስትዘረጋ ዶክተር ከኋላዋ ዘጋው:: እናቷ እንዳያዩ::

እርሱም ይቅርታ ለመጠየቅ እርሷም ምህረት ለመስጠት የሚናገሩበት አንደበት አልነበራቸውም:: ልቦቻቸው ይተዋወቃሉ:: ዕንባ ብቻ ነበር ለጊዜው ያገኙት መግባቢያ:: ሩቂያ በዕንባ፣ ዶክተር ለብ ባለ ፈገግታ እንዳጀቧቸው ተቃቅፈው እና ተደጋግፈው አነቡ:: የየልባቸውን እያሰቡ::

"ሙ-ሽ-ራ-ዬ
ሙ-ሽ-ራ-ዬ
የወይን አበባዬ:: . . ."
ሳለፈው ሁሉ መደምሰሻ ህሊናው ያዜመለት ዜማ::

"እና እባቴ ማን ነው ልትይኝ ነው?"

"ነግርኩሽ እኮ ይኸው ነበር ሃያ ሦስት ዓመት በሆዴ ቀብሬው የኖርኩት የቤቴ ጉድ:" ህሊናዋ ደግሞ ደጋግሞ የሚያቃጭልባት:: የሚደውልባት::

"ሃሎ?" እያለ ፊቷ ሳይ ድቅን አለ::-ተሺ ስልከኛው::

♣ ♣ ♣

# የምወደው ጥቅስ

"አሁን ማንም አይደለሁም፤ አሁን ምንም የለኝም፤ ነገር ግን የፈጀውን ጊዜ ይፍጅ እንጂ...ሰው እሆናለሁ ሁሉም ነገር ይኖረኛል::"

ለአስተያየትዎ
ፖስታ 60015
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

# የሚስማማዎትን የቤተሰብ ምጣኔ ዘዴ ያውቃሉ?

## በመርፌ የሚሰጥ የእርግዝና መከላከያ ዘዴ (DMPA)

⇨በጣም አስተማማኝና በጤና ላይ ጉዳት የማያመጣ ነው::
⇨በየሦስት ወሩ አንድ ጊዜ በመርፌ ይሰጣል፤ በመሆኑም በዘዴው መጠቀምዎ በሌሎች ዘንድ አይታወቅም::
⇨በማንኛውም የመውለጃ ዕድሜ ክልል የሚገኙ ሴቶች፤ ልጅ ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም፤ ሊጠቀሙበት ይችላሉ::
⇨ጡት የሚያጠቡ ሴቶች ከወሊድ በኋላ ከስድስተኛው ሣምንት ጀምር መጠቀም ይችላሉ::
⇨በወር አበባ አመጣጥ ሂደት/ሁደት መካከል ቀላል የደም ብልጭታና መፍሰስ ሊያመጣ ይችላል:: በዚህ ዘዴ ከአንድ ዓመት በላይ ከተጠቀሙ በአብዛኛው የወር አበባ መቅረትን ሊያስከትል ይችላል:: መጠነኛ የክብደት መጨመር ወይም ቀላል የራስ ምታት ሊኖር ይችላል::
⇨ተጠቅመው የሚያቋርጡ ሴቶች ማርገዝ ቢፈልጉ ከአራት ወር እና ከዚያ በላይ ሊወስድባቸው ይችላል::
⇨የማህፀን ዕጢ እና ከማህፀን ውጭ እርግዝና እንዳይፈጠር ለመከላከል ይረዳል::

## ኮንዶም (CONDOM)

⇨ኤድስን ጨምሮ ሌሎች በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎችን እና እርግዝናን ይከላከላል::
⇨በርካታ ወንድና ሴት ጥንዶች ኤድስንና ሌሎች በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎችን በአስተማማኝ ለመከላከል ኮንዶምን ከሌሎች የቤተሰብ ምጣኔ ዘዴዎች ጋር በጣምራ ይጠቀሙባቸዋል::
⇨በኮንዶም ከመጠቀም በፊት ስለ አጠቃቀሙ መረዳትና ጥቂት መለማመድ ያስፈልጋል::
⇨ኮንዶምን ሁልጊዜ በትክክል መጠቀም ወጤቱን አስተማማኝ ያደርገዋል:: ነገር ግን ሁልጊዜ በትክክል ካልተጠቀሙበት አስተማማኝ አይሆንም::

⇨ጥቂት ወንዶች በኮንዶም ግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈፀም ግንኙነት ያደናቅፋል፣ ወሲባዊ ስሜትን ይቀንሳል፣ ያሳፍራል፣ ወይም ምቾት አይሰጥም የሚል አስተያየት አላቸው፡፡

## በቀዶ ህክምና ዘዴ ሴቶችን ማምከን (TUBALLIGATION)

⇨ሴቶች ተጨማሪ ልጅ ላስመፈለጋቸው አረገጠኛ ሲሆኑ የሚገለገሉበት ዘለቄታዊ የእርግዝና መከላከያ ዘዴ ነው፡፡ ሆኖም በዚህ ዘዴ ለመጠቀም አስቀድሞ በጥንቃቄ ማሰብና መወሰን ያሻል፡፡

⇨እጅግ በጣም አስተማማኝ ነው፡፡

⇨በቀላል የቀዶ ሕክምና ሊከናወን የሚችል ከመሆኑም በላይ ሙሉ ማደንዘዣ መስጠት ሳያስፈልግ የቀዶ ሕክምና የሚደረግበትን አካባቢ ብቻ በማደንዘዝ ሊከናወን ይችላል፡፡

⇨የረዥም ጊዜ ተዛማጅ የጤና ጉዳት የለውም፡፡ ቀዶ ሕክምናው ከተደረገ በኋላ ለአጭር ጊዜ ምቾት የማጣት ወይም መጠነኛ የሕመም ስሜት ሊኖር ይችላል፡፡

⇨ከቀዶ ሕክምናው በኋላ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ላይ የብቃት ማነስ ወይም የስሜት ለውጥ አያስከትልም፡፡

## ተፈጥሮአዊ የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎች (NATURAL METHODS)

⇨ሴቶች በወር አበባ አመጣጥ ሂደት/ዑደት ሊያረግዙ የሚችሉበትን ወቅት ጠንቅቀው ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡

⇨ሴቶቹ ሊያረግዙ የሚችሉባቸውን ቀናት በጥንቃቄ ካወቁ በእነዚህ ቀናት የግብረ ሥጋ ግንኙነት አለመፈፀም፡፡ ይህ ካልተቻለም ወንዱ ወሲባዊ እርካታ ከመድረሱ በፊት ግንኙነት ማቋረጥ ወይም በኮንዶም መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

⇨በተፈጥሮአዊ ዘዴዎች በአግባቡና በትክክል ከተጠቀሙ አስተማማኝ ነው፡፡ ይሁንና አስተማማኝ የማይሆንበት ሁኔታ እንዳለም መታወቅ አለበት፡፡

⇨ወንድና ሴት ጥንዶች የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሳያደርጉ ለረዥም ጊዜ መቆየት አስቸጋሪ ሲሆንባቸው ስለሚችል በተፈጥሮአዊ ዘዴ በአስተማማኝ ሁኔታ ለመጠቀም የሁለቱ ጥንዶች መግባባትና መተባበር ያስፈልጋል፡፡

⇨በአካል ላይ የሚያደርሰው ምንም ዓይነት ጉዳት የለም፡፡

⇨አንዳንዶቹ ተፈጥሮአዊ ዘዴዎች ትኩሳትና የማህፀን በሽታ ሲኖር ወይም ከወሊድ በኋላና ጡት በሚያጠቡ ጊዜ ለመጠቀም አያመቹም፡፡

## በላይኛው ክንድ ቆዳ ሥር የሚቀበር የእርግዝና መከላከያ ዘዴ (NORPLANT)

⇨ይህ የእርግዝና መከላከያ ዘዴ በላይኛው ክንድ ቆዳ ሥር ከሚቀበሩ ስድስት ትናንሽ ካፕሱሎች የተዘጋጀ ነው፡፡

⇨እጅግ አስተማማኝ ሲሆን ለአምስት ዓመት እና ምናልባትም ከዚህ ለረዘመ ጊዜ ያገለግላል፡፡

⇨በማናቸውም የመውለጃ ዕድሜ ክልል የሚገኙ ሴቶች፤ ልጅ ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም፤ ሊጠቀሙበተ ይችላሉ፡፡

⇨በላይኛው ክንድ ቆዳ ሥር የተቀበሩትን ስድስት ትናንሽ ካፕሱሎች አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ማስወጣት ይቻላል፡፡ ካፕሱሎቹ እንደወጡ ወዲያው ማርገዝ ይቻላል፡፡

⇨ጡት የሚያጠቡ ሴቶች ከወሊድ በኋላ ከስድስተኛው ሣምንት ጀምሮ መጠቀም ይችላሉ፡፡

⇨በወር አበባ አመጣጥ ሂደት/ዑደት መካከል ቀላል የደም መፍሰስ፣ የደም ብልጭታ ወይም የወር አበባ መቋረጥና ቀላል የራስ ምታት ሊኖር ይችላል፡፡

⇨የደም ማነስ በሽታና ከማህፀን ውጭ እርግዝና እንዳይፈጠር ለመከላከል ይረዳል፡፡

## በማህፀን ውስጥ የሚቀመጥ የእርግዝና መከላከያ ዘዴ “ሉፕ” (IUD)

⇨መጠኑ አነስተኛ ሲሆን በሞያው ልዩ ስልጠና በወሰዱ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ሰጪዎች በማህፀን ውስጥ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡

⇨ለረዥም ጊዜ የሚያገለግል አስተማማኝ ዘዴ ሲሆን በማያስፈልግ ጊዜ ማስወጣት ይቻላል፡፡

⇨**TCU 380A(IUD)** የተባለው የሉፕ ዓይነት ቢያንስ ለአስር ዓመት በማህፀን ውስጥ በመቆየት እርግዝናን ሊከላከል ይችላል፡፡

⇨በማህፀን ውስጥ በተቀመጠ የመጀመሪያ ወቅት የወር አበባ መብዛት እና መራዘም እንዲሁም መጠነኛ ምቾት ማጣት ሊያስከትል ይችላል፡፡

# ከፕሮጂስቲን ብቻ የተሰራ የሚዋጥ የእርግዝና መከላከያ ኪኒን (POPS)

⇨ከወሊድ በኋላ ከስድስት ሣምንታት ጀምሮ የወሊድ መከላከያ እንክብል መጠቀም ለሚፈልጉ እና ለሚያጠቡ እናቶች ተስማሚና የተሻለ አማራጭ ነው::

⇨ጡት በሚያጠቡበት ወቅት በጣም አስተማማኝ የእርግዝና መከላከያ ዘዴ ነው::

⇨ጡት በማያጠቡበት ጊዜ ይህንን ዘዴ ከተጠቀሙ በወር አበባ የአመጣጥ ሂደት/ሁደት መካከል ቀላል የደም ብልጭታና የደም መፍሰስ ሊከሰት ይችላል::

⇨ተገቢው ጥንቃቄ ሳይደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ቢፈፀም እንደ አጣዳፊ የእርግዝና መከላከያ ዘዴ መጠቀም ይቻላል::

# በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወቅት ብቻ የሚያገለግሉ የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎች

⇨ፀረ የወንድ የዘር ፍሬ፣ የማህፀን በር ቆብ እና የማህፀን በር ከዳን የሚባሉት፣ ሴት ልጅ በራስዋ ተቆጣጥራ አሰፈላጊ ሲሆን የምትጠቀምባቸው የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎች ናቸው::

⇨የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈፀም በአስፈለገ ጊዜ ከዘዴዎቹ አንዱን በመምረጥ ከግንኙነት በፊት በብልት ውስጥ እንዲቀመጥ ማድረግ ይገባል:: ነገር ግን ግብረ ሥጋ ግንኙነት ከጀመሩ በኋላ አቋርጦ የመከላከያ ዘዴዎቹን ለመጠቀም መሞከር ሳልተፈለገ እርግዝና ሊዳርግ ይችላል::

⇨የመከላከያ ዘዴዎቹን በየጊዜው በትክክል ከተጠቀሙባቸው ውጤቱ አጥጋቢ ይሆናል:: ነገር ግን አንዳንድ ሴቶች የመከላከያ ዘዴዎቹን ሁልጊዜ በትክክል ስለማይጠቀሙባቸው ውጤቱ አስተማማኝ አይሆንም::

⇨ዘዴዎቹ አንዳንድ በግብረ ሥጋ የሚተላለፉ በሽታዎችን ሊከላከሉ ይችሉ ይሆናል::

⇨በእነዚህ ዘዴዎች መጠቀም ለፈኛ በሽታ የመጋለጥ አጋጣሚ ይፈጥራል::